
# ላንዳፍታ

በፍቅር፥በሰላም፥በአንድነት
ተከባብሮ ለመኖር
መደማመጥ፥
መቻቻል

መስከረም ፲፱፻፹፯
፫ኛ ዓመት ቁጥር ፫
$2.75
ኢትዮጵያዊ የቤተሰብና የመዝናኛ መጽሔት በአማርኛ
በየሁለት ወር የሚታተም




እንቁጣጣሽ
መቱ ያምጣሽ!!

# LANDAFTA

Ethiopian Cultural Bi-monthly Amharic Magazine
(Amharic is the official language of Ethiopia)
September, 1994 Vol. 3. No.3

## በዚህኛው እትም

ከፍተኛ ተቃውሞ የገጠመው የሽግግር መንግሥቱ መሪ የአሜሪካ ጉብኝት

❖ በቅርብ ከኢትዮጵያ የደረሱን ዜናዎች

❖ ኑሮ በአሜሪካ

❖ አዳምና ሔዋን አላለልኝ ይሆን ዕጣዬ

❖ ልብ ወለድ የላጤው ኑዛዜ የዴብራ ጦስ

# የኢትዮጵያ መንደር





## ETHIO VILLAGE

### CAFE & RESTAURANT

**3462 N. Clark St.**
**Chicago, IL 60657**
**(312) 929-8300**

CATERING AND CARRY OUT AVAILABLE



**ቀይ ወጥና ዝግኑ ዶሮ ወጥ አልጫው፤**
**አትክልት ከሥጋ ጋር ምንቸት አብሽ ክትፎው።**
**የአበሻ ዳቦና ቆንጆ የማር ጠጅ፤**
**ሽታው ግቡ ይላል ሳይገቡ ከደጅ።**
**ቆርጠው በሩን ከፍተው ገባ ሲሉ ገና፤**
**አገር ቤት የገቡ ያስመስላልና።**
**የሰኞ ዕለት ዱለት የበግ ወጥ ፍትፍቱ፤**
**ረቡና ዓርብ ዕለት የጾም በያይነቱ።**
**በስምንት ዓመት ልምድ የሙያ ክምችት፤**
**ፍጹም ኢትዮጵያዊ በሆነ ዝግጅት፤**
**ኢትዮ ቪሌጅ ይምጡ ሲያሻዎት መደሰት።**

# ማውጫ CONTENTS


2 ከአዘጋጁ

4 ሰላምታ ከወደ አገር ቤት (ወረቃየሁ)

6 የአንባብያን–ደብዳቤዎች

8 እንዲህ ሆነ
የሽግግሩ መንግሥት መሪ የአሜሪካን ጉብኝት
ዜናዎች ከኢትዮጵያ
(ከኢትዮጵያ ወኪል)

16 ጥንቅር ከዚህም ከዚያም

17 እንዳው አንድ ጥያቄ አለኝ!

19 ልብወለድ
የላጤው ኑዛዜ (አንዱዓለም)
የዴብራ ጦስ (ገረሱ)

25 ኑሮ በአሜሪካ
በአዲስ ዓመት አዲስ ተስፋ
ባለፉት ሁለት ወራት
የአትላንታ ቅድስት ማርያም ቤ/ክ
ላንዳፍታን በሞቅታ (ጣጤው)

32 አዳምና ዋን
አላለልኝ ይሆን (ትዝታ አለብኝ)
ዕጣዬ (አብረኸት)

39 ባላገርና ፖለቲካ (ከአለፈው የቀጠለ)

41 የአበው ቅርስ

44 እስፖርት
የዘንድሮው ውድድርና ዝግጅቱ

46 ቢስቁም ባይስቁም


47 ጨዋታና ሰንጠረዥ




የአቶ መለስ ጉብኝት ተቃውሞ ሰልፍ



የአትላንታ ቤተ ክርስትያን ምረቃ



የዘንድሮው እግር ክስ በዓል

የሽፋን ፎቶ፤ በአሜሪካ የተወለዱ ኢትዮጵያውያን ህጻናት


"ላንዳፍታ" የግል መጽሄት ናት። የሚወጡ ጽሁፎች በሙሉ የአዘጋጆቹን አመለካከት ወይም እምነት ያንጸባርቃሉ ማለት አይደለም። ጽሁፎቹን በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን ሆነ በተመሳሳይ መንገድ በከፊልም ሆነ በሙሉ አባዝቶ ለማሰራጨት የጸሃፊውንና የአዘጋጁን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል። በተለይ የገጠመኝና የፈጠራ ድርሰት ጽሁፎች ህጋዊ መብታቸው የተጠበቀ መሆኑን እንገልጻለን።

© COPYRIGHT LANDAFTA 1994

ላንዳፍታ
መስከረም ፲፱፻፹፯
፫ኛ ዓመት ቁጥር ፫
LANDAFTA
September, 1994 V. III - No. 3

አዘጋጅና አሳታሚ
መኮንን ገሠሠ

**Publisher/Editor**
*Mekonnen Gessesse*

**Editorial Advisors**
*Dr. Abera Molla*
*Haile Demissew*
*Solomon Melesse*
*Dawit Deres*
*Zelleke Nigatu*
*Girma Zegeye*
*Abera Sisay*

**Distribution**
Atlanta, GA
California Mart
Sweet Auburn Grocery
Chicago, IL
Ethio-Village Rest.
Tesfaye B. (Hoddo)
Yeshi Gessesse
Daton, OH
Rainbow Cafe
Denver, CO
Tibeb Taye
Dallas, TX
ET. Beauty Supply
L.A., CA
K RAH Market
Oak Land, CA
Albo-African Shop
San Jose, CA
St. Claire news Stand
Seatle, WA
Addis Cafe
St. Louis, MO
A & Z Liquor
St. Paul, MN
Merkato
Tampa, FL
Ibex Ethiopian restaurant
Washington D.C.
Addisu Gebeya
Family Food Market
Merkato Market
Nini Market
Indian Super Market
Windsor, Ontario
Tewodros Zewdu

Landafta
P.O.Box49301
Atlanta, GA30359
Phone/Fax (404)728-9122

# ከአዘጋጁ

## እንኳን ከዘመን ወደ ዘመን በሰላምና በጤና አሸጋገራችሁ።
## መጪውም ዘመን የሰላም፤ የጤናና የብልፅግና ይሁንላችሁ!!

እንቁጣጣሽ በያመቱ ያምጣሽ! ብለን አዲሱን ዓመት በአዲስ ተስፋ ልንቀበለው ነው። አዲሱ ዓመት በአገርም እዚህ ውጪም ላለነው ኢትዮጵያውያን የደስታ፣ የጤናና የብልጽግና እንዲሆን ምኞታችንን እንገልጻለን። ዓመት አልፎ ዓመት ሲተካ አዲስ ተስፋና አዲስ ዕቅድ ማቀድ የተለመደ ነውና ይኸው ተስፋችሁ ለምልሞ በተግባር እንዲታይ ምኞታችንን እንገልጻለን።

በውጭ አገር ለተወለዱ ኢትዮጵያውያን ህጻናት ምንም እንግጫ ይዘው በየደጃችን ባይገኙም አዲሱን ዓመት የደስታና የተስፋ እንዲሆንላቸው በመመኘት የጥቂቶቹን ፎቶ በሺፋናችን ላይ አውጥተናል። የቤተሰብ ቋንቋቸውን የሚማሩበትም ሁኔታ የሚመቻችበትንም ሁኔታ በዚሁ አጋጣሚ ሳንጠቁም ልናልፍ አንፈልግም። ለዚህም በየቦታው የቋንቋ ትምህርት ቤቶች እንዲስፋፉ ምኞታችንን እንገልጻለን።

በዚህኛው እትም እንደከዚህ በፊቱ የአገር ቤት ዜናዎችንና ቋሚ አምዶቻችንን ይዘን ቀርበናል። የሽግግር መንግሥቱን መሪ የአሜሪካን ጉብኝት በመጠኑ ያገኘነውን ዘገባም አቅርበናል። በአትላንታ ከተማ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ምዕመናን የተገዛውን ቤተክርስቲያን ምረቃም በዓይናችን ያየነውን አቅርበናል። ባለፉት እትሞች የተጀመሩትን የገጠመኝ ታሪኮችም ቀጥለናል። ሁሉ አለ። እንግዲህ አንባቢዎቻችን መጽሄቷ የበለጠ አገልጋይነቷን የምትቀጥልበትን አስተያየቶቻችሁን እንዳትነፍጉን እንላለን።

## የ1987 ዓ ም የቀን መቁጠሪያ

በጥሩ ሁኔታ በከለርና በግራፊክስ አሸብርቆ አጽዋማትንና በዓላትን የሚገልጽ የ1987 ዓ ም የቀን መቁጠሪያ አዘጋጅተናል። የፈረንጆቹንና የኛን አቆጣጠር በትክክል ያሳያል። በውብ ሰንደቅ ዓላማችን ያሸበረቀ ነው። ዋጋው $5 ብቻ ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ የፖስታ አገልግሎት ይላክሎታል።
በስጦታም ለመላክ ከፈለጉ እናደርስሎታለን

Send $5.00 payable to LANDAFTA. 1987 Eth. Calendar.

የላንዳፍታ መጽሄት ዝግጅት ክፍል
LANDAFTA
P.O.Box 49301
Atlanta, GA 30359
(404) 728-9122

*Landafta is an independent magazine published bi-monthly in Amharic.*
*Views expressed do not necessarily represent that of its editors and advisors.*



## እስቲ አንቺ መስከረም !

እፈራለሁ እንዳትሆኚ
        እንዳለፉት መስከረሞች፣
ዘመን ከፍተው ወራት መርተው
ልብ አድምተው ህዝብ አጥፍተው
        እንደሄዱት ያንቺ ዓይነቶች።
ዘንድሮ እንኳን ቀና ብለሽ
ህዝባችንን ቀና አድርጊው፤
        የሠላም ወር መጣሁልህ
        እንባህ ይድረቅ በቃህ በይው።
እንደአበባሽ ትኩስ ሽታ
        ዘመኑንም ደግ አድርጊው፤
ስቃይ የለም ሞትም ሞቷል
        . . . ጠፍቷል በይው።
በቄጤማሽ በለምለሙ
        መራርቂና ቸብ አድርጊው፤
እንዳለፉት ሃያ ዓመታት
        ምስኪኑን ህዝብ አታሣቂው።
ከፊት ሆነሽ ወራት መርተሽ
ሰላም ደስታ እንዲታደል
        የኖህ እርግብ ገድ ወፍ ሁኚው።
        ውብ መስከረም ቀደምት ወራት
የአበቦች መፈንጠቂያ፣
የወራቶች በር መግቢያ።
        ፍሬዎች ልጆችሽን፣
        ቀሪ ወራት ያጀቡሽን፤
ገድ ፍኖት ሁኚላቸው
አንቺ ቀንተሽ ቀኝ አርጊያቸው።

# እንቁጣጣሽ

# በያመቱ

# ያምጣሽ !



# አዲሱ ዓመት
# የሰላምና የጤና
# የብልጽግና ይሁንላችሁ !

ግጥም – ግርማ ዘገዬ

# ሰላምታ ከወደ አገር ቤት

## እንደምን አላችሁ?

እንደምን አላችሁ? ኑሮና ብልሃቱስ እንዴት ይዞአችኋል? እኛ ደህና ነን። እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነን። የበጋውን ሀሩር ጨርሰን አጥንት ሰርስሮ የሚገባውን የክረምት ብርድ ተያይዘነዋል። ክረምቱን ለመውጣት ላይ ታች እንላለን። ደህና ቀን ቢጤውን ያገኘ እርቧን ከጎኑ ሽጦ በቆሎውን ገዝቶ እያንቶሸቶሸ ክረምቱን ይገፋል። ያም ያልሆነለት ላጤ ድራፍቱን ጨልጦ፣ ትንሽ ጂን፣ በአናቱ ፉት ብሎ ብቻውን ተኮራምቶ ያድራል። የሆነለት የሞላለት ደግሞ በቶዮታ፣ በፔጆ፣ በመርሴዲስ እየፈሰሰ አስፋልት የቋጠረውን ውኃ በመንገደኛው ላይ እየከለበሰ ይከንፋል። ሽው ይላል። ቀን ጥሎት መንገድ ላይ የወደቀው ደግሞ ድሪቶውን ተከናንቦ ላስቲክ ደርቦ (ምናልባትም በባዶ ሆዱ) የሐምሌ ዶፍ ይወርድበታል። እንዳንዱም አሥር ሳንቲም ከፍሎ በዲሪቶው የተነከረለትን ቤንዚን እየሳበ ቢርቢራ እንደበላ አሣ ሰማይ ምድሩ ዞሮበት መሃል መንገድ ላይ በደረቱ ተገልብጦ ያድራል። አንዱን ዱር አዳሪ ጠይቄው በስሙኒ ደህና ይነከራል ብሎኛል። ጠዋት ሲረፋፍድ አዲስ ምልምል ወፈ – ሰማይ ፖሊሶች እየረጋገጡ ቀስቅሰው ያባርሩታል። ዝናብ የጠገበ ዲሪቶውን ጠቅልሎ ወደሚጠፋበት መጥፋት አለበት።

እኛ ዘንድ ሰሞኑን የየመንደሩ ኩታራ ሁሉ ለቡሄ ዋዜማ ሆያ ሆዬ እየጨፈረ ፍራንክ አንጡ ብሎ ሲያስቸግር ሰነበተ። . . . ወደቀላው ደግሞ አዋሽ ሞልቶ ወዳጆቹን በግንድ አንጠላጥሎ አከረመ። የመንግስት መ/ቤቱም ቅነሳ የሚሉት ወረርሽኝ ገብቶ አዳሜ ነፍሱ ከስጋው የመለየት ያህል በጭንቀት ተዘፍቆ ከረመ። አሁንም ገና አለየለትም። የመንግሥት ሠራተኞች የነበሩ ብዙ ጨዋ ሰዎች "ኢኮኖሚ በሚያሻሽለው" የቅነሳ ፕሮግራም ከመሰንበቻው ከየስራ ገበታቸው እየተገፈተሩ ይወጣሉ። ቀሪ ዘመናቸውን እንዴት ያሳልፉታል? የራሳቸው ጉዳይ! በምን ገቢ ራሳቸውን ያስተዳድራሉ? የራሳቸው ችግር! የሚጠይቅም የሚመልስም አይገኝም። ደህና ደህናው ጉበዝ ስንቱ አባውራ ከስራው ተመንግሎ "ድድ ማስጫ" ተጐልቶ ለብቻው ሲነጋገር ይውላል። ቅነሳው በቂ ጥናት ተካሂዶበታል። እየተካሄደበትም ነው። . . . እያንዳንዱ ሰራተኛ በልቡ ያለው በሆዱ የያዘው ተዳሷል። ቻርተሩን የጐሪጥ ያየዋል። ወይስ እጁን ዘርግቶ ተቀብሎታል? በደንብ ተመዝኗል። ከእነማን ጋር ይወጣል ከእነማን ጋር ይገባል? ይገመገማል። የዘር ግንዱ ምንድነው? ይጠናል። በየትኛው ድርጅት ታቅፏል? ይጣራል። በድርጅት ያልታቀፈ ከሆነ ምክንያቱ ይመረመራል። ለምን አንዱ ድርጅት አልገባም?. . .ጥሩ ጥያቄ ነው። – የወቅቱ የዲሞክራሲ ሂደት ያልጣመው አገር ወዳድ ነኝ ባይ ቢጤ ወይም ትምክህተኛ ሊሆን ይችላል።የጐሳ ፖለቲካ ቆፍንኖት ቀን የሚጠብቅ የሆዱን በሆዱ የያዘ ጉበዝ ወይም ቢመቸው ጫካ የሚገባ ባይመቸው ደግሞ የልቡን ደብቆ ይዞ እየገዘገዘ የሚኖር ሊሆን ይችላል . . . በሆዱ ምን እንዳለ፣ በልቡ ምን እንደያዘ ለማወቅ – ሽንኮራ አደል ተቀምሶ አይታይ ወይ x-ray አይነሳ ነገር! ያለው ብቸኛ ዘዴ ከስራ መንግሎ የእንጀራ ገመዱን መበጠስ . . . ሆዱን ደርግሞ ዘግቶ በሆዱ ያለውን ማየት . . . ፍቱን መፍትሄ!!

ይኸ አንጀት አርስ የአፍሪካ ፖለቲካ እንዲህ የዋዛ አይደለም። ለፕሮፌሰር አሥራት ደህና ማረፊያ ተበጅቶላቸዋል። አበራ የማነአብ በእጅ ገብተዋል። ዮሴፍ መርሻም ወደ ማዘዣ ጣቢያቸው አልተመለሱም። አብርሃም ያየህ በዩጋንዳ ዕሥር ቤት ተከርችመዋል። ለተቀሩትም የሚሆን ይፈለጋል። አፈር በስኳር እየተበጠበጠ የተገኘችን ጌትነት ለመንጠቅ? እንዴት ተቀልዷል! የእኚህ ፕሮፌሰር ነገር ከፉጦስ እንዳያመጣ ቢያሰጋም እንግዲህ ምን ይደረግ? . . . ፍ/ቤት አቀረቡአቸው፣ ሃምሳ ሁለት ጊዜ አመላለሱአቸው፣ እስር ቤትንም አስሞከሩአቸው፣ ፍንክች ያሉ አይመስልም፣ የሰለቻቸው አልሆኑም። አገር ለቀውም ዞር ማለት ሳይታያቸው ቀረ። . . . እንግዲህ ምን ይሁን? – ሁለት ዓመት አከናንቦ ትንሽ ቀን እፎይታ ከማግኘት በቀር! አማካሪ ነኝ የሚለው ፈረንጅ ሁሉ ተቻቻሉ፣ እንዲህ ሁኑ፣ እንዲህ አድርጉ ይላል። "በለው በለውና አትለውም ወይ!" እየተባለ ያደገ የአባ ደፋሩ ልጅ እንዴት ሆኖ ከባላንጣው ጋር ተቻችሎ ይኑር? . . . አባቱን የገደለ የእደንጓሬ ንፍሮ ነበር። ልጁም ያለ እርሱ አይጣፍጠውም ይላል የወላይታ ሰው!

ለመሆኑ እናንተስ እንዴት ናችሁ? ይሄ የሰሞኑ የላፋዬት ፓርክ ውሎ እንዴት አደረጋችሁ? በገዥዎቻችን ላይ ያወረዳችሁት ቡጢና ዱላስ የምንድን ይሉታል? የምር አልገባንም። ዱላ ለሸክላ ብቻ ነው። የሚከፋው ይቅመሱት ነው ወይስ ጥፋት ተገኝቶባቸው ቅጣት መሆኑ ነው? ቀን የጎደለበት የእኔ ቢጤ ሁሉ "እፋረዳለሁ" ስለሚል በተቀጡበት ጉዳይ ደግመን እንዳንወቅሳቸው ቅጣቱ ለየትኛው ጥፋት እንደሆነ ለይተን ብናውቀው ደግ ነው። ፈረንጆቹስ ቢሆኑ ሺህ አጀብ ከፊት፣ ሺህ አጀብ ከኋላ ቢያደርጉላቸው ወይም ካላጡት ነገር አንድ ብረት ለበስ ወይም ታንክ ለመጓጓዣ ቢመድቡላቸው ምን አለበት ነበር? እናንተም ታርፉት ነበር። ወይ ነዶ? የአባይን ልጅ ውኃ ጠማት አሉ። በቸር ይግጠመን!

የናንተው ወርቃየሁ

# ይሆን እንመስላለን !!



የጥቁር አንበሳን ሆስፒታል ታውቂት የለ?
አጥሩ ዙሪያ ይኸው ጎጆዋችንን ቀልሰናል።



የአውቶቡስ ፌርማታዎች ጥቅልል ብለን እናድራለን።
ጧት እስኪያባርሩን ድረስ።

# የአንባብያን ደብዳቤዎች

ይድረስ ለላንዳፍታ መጽሄት አዘጋጅ፤ በልዑል እግዚአብሄር እንዲሁም በእናቱ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ለሚጠበቀው ጤንነታችሁ እንደምን ከርማችሁዋል። መጽሄታችሁን አንድ ሁለቱን አንብቤአለሁ። ጥሩ ነው። በዚሁ ቀጥሉ። እንግዲህ ለመጽሄታችሁ እንግዳ ስለሆንኩ በሚገባ እንደምትቀበሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ።

በአትላንታ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን እግዚአብሄር ድከማችሁን ቆጥሮ የእራሳችሁ ለሆነ ቤተክርስቲያን ስላበቃችሁ ምስጋና ይግባው። ትብብራችሁ ድንቅ ነው። ለሌላው መሠረት የምትሆኑ ናችሁ። እግዚአብሄር መጨረሻውን ያሳምርላችሁ ዘንድ የሱ ፈቃድ ይሁን። በሌላ አካባቢ ለሚገኙ ወገኖቻችሁ የሀሳብ ድጋፍ በመስጠት ሌላውም የራሱ የሆነ ቤተክርስትያን እንዲያገኝ በጸሎታችሁ አስቡን። ሌላው ከአባ ገብረመስቀል መኩሪያ ጋር ያደረጋችሁትን ቃለ መጠይቅ አይቼ በጣም ተደሰትኩ። በሰው አገር ላይ ህዝባቸውን ሰብስበው እንዲያስተምሩ እሳቸውን ለሰጠን እግዚአብሄር ክብር ምስጋና ይግባው። ከዚህ ሌላ ስለኢትዮጵያ ህዝብ ሰላም ምን እንደሚሉ በተጠየቁት ጥያቄ ላይ የሰጡት መልስ በጣም አርኪ ነው። አባታችን አባ ገብረመስቀል እንዳሉት ከሁሉም በላይ የእኛ እርስ በርስ መዋደድና መስማማት ትልቅ መሠረት ነው። ይህንንም በማስመልከት ከቅዱስ መጽሀፍ ውስጥ ልጠቅሰው የምወደው አለኝ።

*“ ማንም እግዚአብሄርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሀሰተኛ ነው። ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዙአብሄርን እንዴት ሊወድ ይችላል? እግዚአብሄርን የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትዕዛዝ ከእርሱ አለችን።”*

*የመጀመሪያዪቱ የሃዋርያው የዮሃንስ መልዕክት*

*ም ፬ ቁ ፳ እስከ ፳፩*

እንግዲህ ለኢትዮጵያችን የሚበጃት እኛ ሕዝቦቿ ፍቅርን ሳንነፋፈግ በንስሃ ተመልሰን በጾም በጸሎት ራሳችንን ዝቅ አድርገን ለእግዚአብሄር ትዕዛዝ ተገዝተን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ብንማጸነው ለኢትዮጵያችን የሚያስፈልጋትን ሁሉ ያደርግልናል። እሱ ሁሉን ማድረግ የሚችል ቸር ፈጣሪ ነውና። እኛ ህዝቦቾ እግዚአብሃርን በጣም አስቀይመነዋል። እንደኛ ኃጥያትና በደል ሳይሆን እንደሱ ቸርነት ለኢትዮጵያ ምድራችን ፍቅርን፤ አንድነትንና በረከትን ያድልልን ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁን። እንግዲህ ደህና ሁኑልኝ ላንዳፍታዎች። ይህች ጽሁፌ ሚዛን ደፍታ ከወጣችልኝ በሚቀጥለው የምላችሁ ይኖረኛል።

ትንግርት ነኝ ከሳንዲያጎ

ትልቅ ምስጋና ለባሮ ባንድ ብዬ ደብዳቤዬን ብጀምርስ። እንደምን ከረማችሁ ላንዳፍታዎች። ከአገር ቤት የመጡ በፎቶግራፍ የተቀነባበሩ እውነታዎች ማውጣት ከጀመራችሁ ጀምሮ የአንባቢውን ፍላጎት አርክቶታል እላለሁ– የነጣጤውም መልዕክት ፈገግ እያሰኘ ትምህርት እየሰጠን ነው በርቱ። በእስፖርቱ ውድድር ጊዜ የሆነውንና እኔ የተሰማኝን እጠር አድርጌ ባቀርብላችሁ ምን ይመስላችኋል? ዋሺንግተን ኮን ንሽን ሴንተር ተደርጎ በነበረው የሙዚቃ ዝግጅት ታዋቂ ድምጻውያን ጥላሁን ገሠሠ፤ ንዋይና ሌሎችም እንደሚገኙ ስለተነገረ ቦታው በህዝብ ብዛት ተጣቦ ነበር። ከጤና ኢንሹራንስ ዋጋ በላይ የሆነ የመግቢያ ዋጋ ከፍለን መቀመጫ reserved ነው ተባለ። የተገኘነውን እንግዶች የሚያስተናግደን አጣን።
የዓለምፀሃይ ወዳጆ ውብ ግጥም ተነቦ ካለቀ በኋላ በዚሁ አገር ራሳቸውን አሰባስበው የተደራጁ የባህል ጓዶች ጣዕም ያለውን የአገር ባህል ሙዚቃ ካሰሙን በኋላ ለዚህ ጽሁፌ መነሻ የሆነውን የባሮ ባንድን ተከተው ተለዩን። እንድኮራባቸው ያደረጉኝ ባሮዎች Jump Jump እያሉና አንዴ አፍሪካ፤ አንዴ እዚሁ እየሄዱ ተመልካቹን አዝናኑት። ከሁሉ የገረመኝ ምንም የገንዘብ ክፍያ ሳይጠይቁ ውድ ወገናቸውን ለማስደሰት ያደረጉት መሆኑ ነው። ባሮዎች ዝግጅታቸውን ጨርሰው ከመድረክ እንደወጡ ይመጣሉ የተባሉት “ዝነኞቹ” የውሃ ሽታ ሆኑ። የተመልካቹ ጩኸት በማየሉ ባሮዎች እንደገና የህዝቡን ኀዘንና ኡኡታ በመስማታቸው ተመልሰው ገብተው jump jump እያሉ ህዝቡን አረጋጉት። መቼም “ዝነኞቹ” በገንዝብ ምክንያት ስምምነት ስላልነበረ ነው ያልተገኙት የሚባል ነገር ካለ ልሰማው አልፈልግም። የፌዴሬሽኑ ተወካይ ባሮዎች ድጋሚ እየተጫወቱ እያሉ አቋርጠው የዕድር መዝገብ የሚያህል ወረቀት ይዘው መድረክ ላይ ይወጣሉ። ማስተዋወቅም ይጀምራሉ። ሙቀትና ብስጭት ያለበት ተመልካችም “ሌባ ሌባ” በማለት ጩኸቱን አሰማ። እነ ጥላሁንም ተሰልፈው ገቡ። የነጥላሁንም ተወካይ ስህተቱ የነሱ እንዳልሆነ ተናግሮ ፌዴሬሽኑን አጋፈጠ። አንድ አምስት ጨዋታ ያህል እንደተጫወቱ ያው የፌዴሬሺኑ ሰው ይሁን ሌላ ወጥቶ የሎተሪ ቁጥር ብሎ ተናገረ። አሸናፊው ወደ መድረክ ለምን እንዳልተጠራ ይገርመኛል፤ ካለ ማለቴ ነው።

እንግዲህ ለዚህ ምሽት ተሳክቶ ረብሻ ሳይነሳ መፈጸም የባሮ ባንድ ያደረገውን አስተዋጽዖ ደጋግሜ ላድንቅ። ጩኸትና ረብሻ ሲበዛ ተሯሩጠው የራሳቸውን መሣሪያ መልሰው እንዲያውም ጥላሁን ሲዘፍን ደራም ይዘው በማጀብ፣ ምንም ሳይከፈላቸው ነው ይህ ሁሉ፤ “ዝነኞቹ” እንደ አሰሪ ባሮዎች

እንደሠራተኛ ተሯሩጠው በክራቫት ያበዱት የፌዴሬሽን ሰዎች በቦታውም ሳይኖሩ፤ እና ይህን ለፈጸሙት የባሮ ባንድ አባላት ደግሜ ደጋግሜ ኪነታዊ ባህሪያቸውን በማድነቅ ባመሰግናቸው ምን ይመስላችሁዋል። ከተነጠቅነው $25 ብር እነሱ ምንም ያልተካፈሉት ተሻሉን። ሌሎቹማ በገንዘቡ ላይ ሲቦጫጨቁ ጉድ አድርገውን ነበር።
በሉ እስቲ የዓመት ሰው ይበለን ደግሞ።

ብርሃን አብርሃም (ዋሺንግተን ዲሲ)

✉ ላንዳፍታዎች እንዴት ይዞአችሁዋል። ጥረታችሁ አስደስቶኛል። በርቱ ልበልና እባካችሁ ይህችን መልዕክት ለወገኖቼ አስተላልፉልኝ።

እንግዲህ መቼም በውጭ አገር በስደት የመኖራችን ሁኔታ እየገፋ ሄዷል። የፖለቲካ ሰዎቻችንም ተስማምተው አስማምተውን ወደ አገር የመመለሳችን ነገር ህልም እየሆነብኝ መጥቷል። እዚያም ባንሄድ እዚህም ተስማምተን እንዳንኖር የሚያደርጉ ሁኔታዎችም እየታዩ ናቸው። ከፋፋይ ሆነው አገር አስገንጥለው ኢትዮጵያን ከምድረገጽ ሊያጠፉት የተነሱትን ጠላቶቻችንን መቼም ለይተናቸዋል። እኔ የቸገረኝ ጉዳይ ቢኖር እኛ ብቻ እናውቃለን፣ እኛ የምንለውን ብቻ ተቀበሉ የሚሉን የራሳችን ሰዎች መስማትና ማየት ነው ያስጠላኝ። ሁሉ ቦታ ላይ ግትር የሆነ አቋም በማንጸባረቅ የሚቀርብላቸውን ገንቢ አስተያየት መቀበል የማይፈልጉ በ"ego" የተወጠሩ አንዳንድ አዋቂ ነን ባዮችን እባካችሁ ምከሩልን። አንድ ሰው እኮ በሁሉ አዋቂ ሊሆን አይችልም፤ ሌላው ሰው ደግሞ በሁሉም ነገር ደንቆሮ ሊሆን አይችልም። ታዲያ ከመደማመጥና እውነትን ለማመን ከመዘጋጀት መቻል ላይ ነበር አዋቂነት።

እኔ አዋቂና አላዋቂው ውሉ እየጠፋብኝ ሄዷል። መናናቅ ባለበት ቦታ ሁሉ መደማመጥ አይኖርም። እኔ ብቻ ነኝ አዋቂ የሚል ባለበትም ቦታ ሥራ አይሠራም፣ የሰውም ትብብር አይገኝም። ስለዚህ እባካችሁ በሉልን። እንደማመጥ፣ እንናናቅ። ሰው ከኑሮ ብዙ ይማራል። እዚህ ሰው አገር ያለው ወገናችን በኑሮ ብዙ ተምሯል እውቋል። ስለዚህ ሃሳብ ሊናቅ አይገባም። በአንድ የትምህርት ዓይነት ዶክተር ስለተባለ ደግሞ በሁሉም ዓለም ላይ ባለው ነገር ሁሉ ሊቅ ሊሆን አይችልም። ይህችን ቀላል ሀቅ ለመዋጥ ደግሞ ብዙ ዕውቀት አይሻም። "እኔ የማውቀው አለማወቄን ነው" ያለውን ፈላስፋ ፈለግ እንከተል እላለሁ።

አውግቸው (ከአትላንታ)

✉ ይድረስ ለአትላንታዎች፤
ወንዱም የሥራ ልብሱን ቀይሮ፤ ገላውን ሽታ ባለው ሳሙና ተጣጥቦ፤ የክት ሸሚዙንና ሱሪውን ተኩሶ፣ ጫማውንም ወልውሎ፣ ጸጉሩን ተበጣጥሮ፤ ሴቶችም እንዲሁ በየበኩላቸው ውድ ቀሚስ አውጥታ፤ ሽቶዋን አርከፍክፋ ወደ አበሻ ፓርቲ ይኬዳል። $15 ወይም $20 መግቢያ ከፍለን፣ የሲጋራው ጪስ ዓይናችንን እቃጥሎ እንባ እንባ እያለን እስከስታውን ከዘመዶቻችን ጋር እናቀልጠዋለን። ዕድለኞቹ ከፍቅረኞቻቸው ጋር ይሉታል። ውብ ውብ ሴቶችም እንደ ጠረጴዛ አደራደሩ ተፈነጣጥረው ተቀምጠው ወንዶችም ወደየመጠጡ መሸጫ ቦታ ላይ ተሰባስበው ይታያሉ። መጠባበስ የሚባል ነገር የለም። ሴቷም እያማራት፣ ወንዱም እየከጀለ ብቻ ለወንድ ጓደኛው "ያቺ የእገሌ እህት ቆንጆ አይደለችም?" በመባባል እንደተፋጠጡ ብቻ ሰዓቱ ገስግሶ ዝግጅቱ ይፈጸማል። ወንዱም የሁለት ሰዓት እንቅልፉን ለሽሾ በጠዋት ሲነሳ ሴቷም ቀሚሷን ለመመለስ ወደ ሱቅ ትኳትናለች። ሁለቱም በአዕምሮአቸው "ኤጭ ምን እንዳው $15 ወይም $20 ብሬን ከስሬ በዋዛ በማለት ሁለተኛ አበሻ ፓርቲ አልሄድም፣ ለዚህ ለዚህ ቤቴ ቁጭ ብዬ ቲፕ እልሰማም።" እያሉ ዝግጅቱንና የአበሻ ፓርቲ ሲኮንኑ ይሰማል። ታዲያስ አትላንታዎች ምን ትላላችሁ? እውነት ወይስ ውሸት? ከሌላ እስቴት ለዕረፍት አትላንታ መጥቼ የታዘብኩት ነው።

ፋሲካና አክሊሉ (ኬንተኪ)

## ውድ አንባብያን

በደብዳቤዎች አምድም ሆነ በሌሎች አምዶች የሚጻፉ አስተያየቶችም ሆነ ጥያቄዎች የጻፉት ሰዎች አመለካከትና አስተያየት እንጂ የላንዳፍታ መጽሄት ዝግጅት ክፍል አመለካከት ተደርጎ መወሰድ የለበትም። አስተያየቶቻችሁን ላኩልን።

እንዲህ ሆነ

# የሽግግር መንግሥቱ መሪ በአሜሪካ ጉብኝታቸው ወቅት ከፍተኛ ተቃውሞ ገጠማቸው

የኢህአዴጉ መሪ አቶ መለስ በቅርቡ በአሜሪካን ዋና ከተማ በዋሺንግተን ዲሲ ጉብኝት ማድረጋቸው ታውቋል። ጉብኝቱ በአሜሪካ መንግሥት ግብዣ ይሁን በራሳቸው ጥያቄ የተደረገ መሆኑ በይፋ የተገለጸ ነገር የለም። August 10, 1994 ረቡዕ ዕለት ዋሺግተን እንደገቡ የሚነገርላቸው አቶ መለስ በነገታው □ሙስ ዕለት ፕሬዚዳንት ክሊንተን ለአጭር ጊዜ እንዳነጋገርዋቸው የስቴት ዲፓርትሜንት ጋዜጣዊ መግለጫ ገልጿል። የአጭር ጊዜ ንግግራቸውም የኢትዮጵያን ዴሞክራሲ በተመለከተ እንደሆነ ይኸው መግለጫ በደፈናው አስቀምጦታል። የአቶ መለስን መምጣት የሰሙ በዋሺንግተንና አካባቢው የሚኖሩ ብዙ ኢትዮጵያውያን □ሙስ ዕለት ከጠዋት ጀምረው በዋይት ሃውስ አካባቢ መፈክሮች በመያዝና በማሰማት ተቃውሞአቸውን አሰምተዋል። ከሰልፈኞቹ አካባቢ በተገኘው ዜና መሠረት አቶ መለስ በሁዋይት ሀውስ ይገኛሉ ተብሎ የተጠበቀው ጠዋት ሆኖ ሳለ የመጡት ከሰዓት በኋላ እንደሆነ ይነገራል። በዚህ ጊዜ ውስጥና በተጨማሪ መሪው ወደ ቤተመንግሥቱ በሚገቡበት ወቅት በኢህአዴግ አገዛዝ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ድምጻቸውን ከፍ በማድረግ ማሰማታቸው ታውቋል። በዚሁ ወቅት ቁጥራቸው ከመቶ ያልበለጡ የአቶ መለስ ደጋፊዎች በአካባቢው ሰልፍ ማድረጋቸው ተስተውሏል። ከአንዳንድ ምንጮች በተገኘው ዜና መሠረት የአቶ መለስ ደጋፊ ሆነው የተሰለፉት የኤርትራ ተወላጆች መሆናቸው ተወስቷል። ለአቶ መለስ ደጋፊ ኤርትርያውያን የተሰጠው የመሰለፊያ ቦታ አማካኝ እንደሆነና ለተቃዋሚዎቹ የተፈቀደው ቦታ እንደነገሩ እንደሆነም ይወራል።

ከሁዋይት ሃውሱ ጉብኝት በፊት አቶ መለስ ከንግድ ወኪሎች ጋር ያላቸውን የምሳ ላይ ጋዜጣዊ መግለጫ ለማከናወን 16ኛና ኤል መንገድ ላይ ወዳለው University Club ሲደርሱ በአካባቢው ይጠብቋቸው በነበሩ ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ተቃውሞ የገጠማቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። አቶ መለስንም በተቃዋሚቹ ከሚወረወረው ቲማቲምና እንቁላል ለማዳን ጸጥታ አስከባሪዎች እንደ ሸፋፍኗቸው የታየ ሲሆን የኢህአዴጉ መሪና አጃቢዎቻቸው ከቲማቲሙና እንቁላሉ ዝናብ ለመዳን ወደ ክለቡ በሩጫ እንደከነፉ በቦታው የነበሩ ሰዎች ይናገራሉ። ከዚሁ በተጨማሪ በአሜሪካ የሽግግሩ መንግሥት አምባሳደር ብርሃኔ፤ አቶ መስፍን ሥዩም፤ ዶክተር ሙላትና አቶ መኮንን አፅብሀ የተባሉ የጸጥታ አስከባሪ ከአካባቢው በተቃዋሚዎቹ ሳይታዩ ለመሄድ በታክሲ ሆነው ከግቢው ከወጡ በኋላ የትራፊክ መብራት ሲይዛቸው በመብራቱ አካባቢ የነበሩ ኢትዮጵያውያን የመኪናቸውን በር በመክፈት እነ አምባሳደር ብርሃኔን እንደደበደቡ የተስትዋለ ሲሆን በዚህ ወቅት ሁለት ኢትዮጵያውያን በፖሊስ ተይዘው ከተወሰዱ በኋላ ሰኞ August 15 ቀን ፍርድ ቤት ቀርበው እንደተለቀቁ ታውቋል።

የሐሙስ ዕለቱ ሁኔታ በዚህ መልኩ ሲያልቅ ዓርብ ዕለት ተቃዋሚ ሰልፈኞች በሁዋይት ሃውስ አካባቢ በድጋሚ ተሰልፈው ተቃውሞአቸውን እንዳሰሙ ታውቋል። በዚሁ ዕለት የሁዋይት ሀውስና የእስቴት ዲፓርትሜንት መውጫ በሮች ሁሉ ላይ ተቃዋሚዎች እንደነበሩ ለማወቅ ተችሏል። አቶ መለስም ከእስቴት ዲፓርትሚንት ሴክሬተሪ ዋረን ክርስቶፈር ጋር በስቴት ዲፓርትሜንት ጽ/ቤት መገናኘታቸው ታውቋል። ዋረን ክርስቶፈር መለስ ዜናዊን ለሥራ ባልደረቦቻቸው ሲያስተዋውቋቸው "ወጣት ከሆኑ የአፍሪካ መሪዎች አንዱና በአገራቸው ላይ ጥሩ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ያሉ መሪ . . . " በማለት እንዳሞካሹዋቸው ተወስቷል። "እንደፈለግን የምናዛቸው ወጣት . . " ማለታቸው ነው ሲሉ አንዳንድ የአሜሪካንን የውጭ ፖሊሲ የሚከታተሉ የፖለቲካ ሰዎች ይህንን የክርስቶፎርን ሙከሻ በትዝብት አስቀምጠውታል።

ሰኞ August 15 ጠዋት የተያዙት ሁለት ግለሰቦች ፍርድ ቤት የሚቀርቡበት ቀን ስለነበረ ብዙ ኢትዮጵያውያን በፍርድ ቤቱ እንደተገኙ ተስተውሏል። በዚሁ ዕለት አቶ መለስ ከምሽቱ 6:00 P.M. ላይ በኢትዮጵያ ኤምባሲ ለዓለም ባንክና ለአሜሪካ ባለሥልጣኖች የራት ግብዣ አደረጉ። በዚሁ ወቅት መፈክሮችን የያዙ ብዙ ኢትዮጵያውያን በኤምባሲው አካባቢ በመገኘት ከፍተኛ ተቃውሞ አሰምተዋል። በወቅቱ ከተያዙት መፈክሮች ጥቂቶቹ የሚከተለውን መልዕክት የያዙ ነበሩ፤-

"U.S. side with the Ethiopian People!"
"Meles is lieng to you!"
"No human rights no Peace!"
"Free Asrat!"
"Free Abera!"

ግብዣው ከምሽቱ 9:20 p.m. እንዳለቀ ሲነገር አቶ መለስ ሌሊቱኑ ዋሽንግተንን እንደለቀቁ ይወራል።

አቶ መለስ ዜናዊ በተጨማሪ በቻነል 5 የቴሌቪዥን ጣቢያ ለአጭር ጊዜ ኢንተርቪው እንዳደረጉ ታውቋል። በዚሁ ኢንተርቪው ላይ "በኢትዮጵያ ሰላም አለ ወይ? ሰዎችን እርስ በርስ ልዩነት አድርግዋል ይባላል፤ ይህ የሚያራምዱት ፖለቲካ ሰዎችን በዘር አይከፋፍልም ወይ ?" ተብሎ ከጣቢያው ለቀረበላቸው ጥያቄ "በኢትዮጵያ ሰላም አለ፤ ሰዎችንም አለያየሁም፤ እኔ የማደርገው ህዝብን የሚያገናኝ እንጂ የሚለያይ አይደለም።" እንዳሉ ፕሮግራሙን የተከታተሉ ሰዎች በትዝብት ይናገራሉ።

የተቃውሞውን ሰልፍ ያዘጋጀውና ያስተባበረው ለዚሁ ተግባር ከተቃዋሚ ኃይሎች ተውጣጥቶ

የተቋቋመው ጊዜአዊ አስተባባሪ ኮሚቴ መሆኑ ታውቋል። በዚህ ኮሚቴ ላይ የተወከሉት ድርጅቶች የመላው አማራ ድርጅት፤ ኢድኅቅ፤ መድህን፤ የደቡብ ህዝቦች አንድነት ግንባርና የአንድ ኢትዮጵያ የሬዲዎ ጣቢያ እንደሆኑ ተነግሯል። ብዙ ኢትዮጵ ያውያን ይህንን የተቃዋሚ ኃይሎች ትብብር በስፋት እንዲቀጥል ምኞታቸውን ገልጽዋል።




ፕሬዚዳንት መለስ ዝናዊ ወደ አሜሪካ ሲመጡ
ጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ አሸኛኘት ሲያደርጉላቸው





የተቃውሞ ሰልፍ በነጩ ቤተ መንግስት ፊት ለፊት



ምስጋና ለሺክ ፎቶ (ሁነኛው አበጀ)

## የፕሬዚዳንት መለስ የአሜሪካን ጉብኝት (በአገር ውስጥ ያሳደረው ስሜት)

የሽግግር መንግስቱ ፕሬዚዳንቱ መለስ ዜናዊ በአሜሪካ ስላደረጉት ጉብኝትና በዚያም ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ስለገጠማቸው ተቃውሞ በግል ሚዲያዎች ሰፊ ዘገባዎች ቀርበዋል። ፕሬዚዳንቱን ተከትለው የሄዱት ሪፖርተሮች አሜሪካን እንደደረሱ ለፕሬዚዳንቱ የተደረገውን የድጋፍ ሠልፍ አጉልተው ሲዘግቡ ሰንብተው ነበር። ከፕሬዚዳንት ቢል ክሊንተን ጋር ያደረጉትንም ውይይት ለሁለት ሰዓት የተካሄደ ነበር በማለት ከዋሽንግተን ዲሲ በቀጥታ ሪፖርት አድርገዋል። የመንግሥት ሚዲያዎችም አሁን ያለው የአሜሪካና የኢትዮጵያ ግንኙነት በቀ.ኃ.ሥ. ዘመነ መንግስት ከነበረው የበለጠ መሆኑን ለማሳየት ሰፊ ዘገባዎችና ሀተታዎችን አቅርበዋል። ይሁን እንጂ በየምሽቱ የሚተላለፈው የአሜሪካን ድምፅ ሬዲዮ የአማርኛ ክፍል በኋይት ሀውስ ቤተመንግስት የተደረገው ውይይት ለሃያ ደቂቃ ብቻ እንደነበር ከሥፍራው ሪፖርት አድርጓል። የተቃዋሚዎችና የድጋፍ ሠልፉን ብዛት የተካሄዱበትን ሁኔታ ገልጿል።

በሽግግር መንግስቱ ልዑካን ቡድን ላይ የድብደባ ጥቃት እንደደረሰም በአሜሪካን ድምፅ ሬድዮ የተደመጠ ሲሆን ሰኞ ዝርዝር ዜናውን ያተመው አንድ የግል ጋዜጣ ከመደበኛው የመሸጫ ዋጋ አራትና አምስት እጥፍ ተሸጧል። በልዑካን ቡድኑ ላይ የድብደባው ጥቃት እንደደረሰ የመንግሥት ሚዲያዎች ትኩረታቸውን በግዮን ሆቴል እየተደረገ በነበረው የአምባሳደሮች ስብሰባ ላይ አድርገዋል። ከቅዳሜ ጀምሮ በነበሩት ተከታታይ ቀናት የፕሬዚዳንቱ የአሜሪካ ጉብኝት በዜናም ሆነ በሀተታ መልክ እምብዛም አልቀረበም። የግል ሚዲያዎች ግን በሰፊው ዝርዝር ሪፖርት ያቀርቡ ነበር። ከፕሬዚዳንቱ ቀደም ብሎ የድጋፍ ሰልፍ የሚያስተባብር ቡድን አሜሪካን መግባቱን የዘገቡ የዜና ምንጮች የተለመደው የኢሕአዴግ የቆረጣ ስልት ሊኖር ይችላል ሲሉ የድጋፍ ሠልፉን ገምተው ነበር። እንደ አንዳንድ የፖለቲካ ታዛቢዎች ግምት የድጋፍ ሠልፉ ተቃውሞውን ከማለዘብና ከፕሮፓጋንዳ ጠቀሜታ የሚበልጥ ፋይዳ ሊኖረው እንደማይችልም ተገምቶ ነበር።

ፕሬዚዳንቱ አዲስ አበባ እንደደረሱም ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ በጉብኝታቸው ከጠበቁት በላይ መርካታቸውን ገልፀው በልዑካን ቡድኑ ላይ ስለደረሰው ድብደባ ግን ጋጠ-ወጦች (ሆሊጋንስ) የፈፀሙት ነው ብለዋል። የተቃዋሚዎችን ማንነት ለማጋለጥም ጠቀሜታ ያስገኘ ነበር ብለውታል። የልዑካን ቡድኑን መደብደብ አንዳንድ ወገኖች ከግል ስሜት አንፃር የረኩበት ቢሆንም ምናልባት በአገር ውስጥ ባሉ ተቃዋሚዎች ላይ መንግሥት የበቀል እርምጃ ሊወስድ ይችላል የሚሉ ወገኖችም አሉ። በአጠቃላይ ግን ፕሬዚዳንቱ ከአሜሪካ ጉብኝታቸው ለምንጊዜም ሊረሳ የማይችል ጠባሳ እንደሚኖራቸውናከዚህም ትምህርት እንዳገኙ ብዙዎች ይስማሙበታል። ከዚህ ውጭ መንግሥት በሚያራምዳቸው ፖሊሲዎች ላይ በቅርብ ጊዜ ለውጦች አይጠበቁም። ድብደባው ከደረሰባቸው የልዑካን አባላት መካከል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አቶ መሥፍን ሥዩም ከነሐሴ 13 ቀን 1986 ዓ.ም ጀምሮ በዚምባብዌ ይፋ የሥራ ጉብኝት በማድረግ ላይ ናቸው። ጉብኝታቸው የቀድሞውን ፕሬዚዳንት ዚምባብዌ አሳልፋ እንድትሰጣቸው ከማድረግ ጋር የተያያዘ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል። ስለፕሬዚዳንቱ ጉብኝት የሽግግር መንግሥቱ የተወካዮች ም/ቤት የሚያውቀው ነገር የለም ተብሏል።

## የኢትዮጵያ አየር ኃይል አውሮፕላን ተጠለፈ

ነሐሴ 10 ቀን 1986 ዓ.ም ሁለት የአየር ኃይል አብራሪ መኮንኖች L-39 የተሰኘ የበረራ መለማመጃ አውሮፕላን ይዘው ወደ ሳውዲ አረቢያ ኮበለሉ። ጠላፊዎቹ ከደብረዘይት አየር ኃይል በመነሳት አገር ውስጥ መጠነኛ በረራ ካደረጉ በኋላ ወደ ሳዑዲ አረቢያ መዲና አምርተው በነዳጅ እጥረት የተነሳ ከሪያድ 40 ኪሎ ሜትር ርቀት በአሸዋማው ሜዳ ላይ ማረፋቸው ታውቋል። አብራሪ መኮንኖቹ በአየር ኃይሉ ውስጥ በተዋጊነት ጭምር የተሰለፉና በኋላም በመምህርነት ለረጅም ዓመታት ያገለገሉ እንደነበር ተገልጿል። ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘ በኋላም ለአብራሪነት የተመለመሉትን የኢሕአዴግ ሠራዊት ምልምሎችን ሲያሰለጥኑ እንደነበረ ተጠቅሶ በአዲሶቹ ምልምሎች ብቃትና ችሎታ ግምገማ ላይ በነበራቸው አቋም ምክንያት ከመከላከያ ከፍተኛ ባለስልጣኖች ጋር ተጋጭተው እንደነበረም በተጨማሪ ተገልጿል።

## የቀድሞ ባለስልጣኖች ለፍርድ ሊቀርቡ ነው

በደርግ የሥልጣን ዘመን በአገርና በሕዝብ ላይ ወንጀል ፈጽመዋል ተብለው በቁጥጥር ስር የሚገኙት የቀድሞ መንግስት ባለስልጣኖች ከመስከረም ጀምሮ ለፍርድ እንደሚቀርቡ የሽግግር መንግስቱ ልዩ አቃቤ ህግ አስታውቋል። ባለስጣኖቹ ለፍርድ የሚቀርቡት በሶስት ምድብ ተከፍለው ሲሆን በፖሊሲ አውጪነትና በአስፈፃሚነት በወንጀል እንደሚከሰሱ ከተሰጠው መግለጫ ለመረዳት ተችሏል። በአሁኑ ጊዜ በዚምባብዌ በጥገኝነት የሚገኙት ኮ/ል መንግሥቱ ኃ/ማርያምም በሌሉበት ጉዳያቸው ለፍ/ቤት እንደሚቀርብ ተገልጿል።

## የሽግግር መንግሥቱ ጦር ወደ ሩዋንዳ ተንቀሳቀሰ

በሩዋንዳ የተፈጠረውን የርስ በርስ ዕልቂት ለማቆም ኢትዮጵያ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የምታወጣው የሰላም አስከባሪ ኃይል ሩዋንዳ ገብቷል። የፈረንሣይን ጦር ይተካል የተባለው ይህ ሠራዊት ከሁለት ወራት ያላነሰ ወታደራዊ ሥልጠና ማጠናቀቁን የመከላከያ ሚኒስትሩ በሸኙቱ ሥነ ሥርዓት ላይ አስታውቀዋል። ሚኒስትሩ በዚሁ ወቅት እንደገለጹት ጦሩ ከኢሕአዴግ ድርጅቶች በብሄራዊ ተዋጽኦ ላይ በመመሥረት የተመረጠ መሆኑን ጠቅሰዋል። አያይዘውም ያልሰለጠነ የአርሶ አደር ሠራዊት ለአለም አቀፍ የፀጥታ ማስከበር ሥራ ብቁ አይደለም በማለት የተሳለቁና ያፌዙ ወገኖች መኖራቸውን አውስተው በሳምንታት ጊዜ ውስጥ ለግዳጅ ብቁ ኃይል ለማዘጋጀት መቻሉን አስረድተዋል።

በሌላ በኩል ወደ ሩዋንዳ የተላከው የሰላም አስከባሪ ኃይል የኢትዮጵያ ሠራዊት አይደለም በማለት የኢትዮጵያ ጦር ኃይል መፍረሱንና የአገሪቱን ብሄራዊ የመከላከያ ሠራዊት የማቋቋሙ ተግባር ገና ያልተፈታ ጥያቄ መሆኑን የሚገልጹ በርካታ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል። በተያያዘ ሌላ ዜና የኤርትራ መከላከያ ሠራዊት የሆነው የሻዕቢያ ጦር ወደ ሩዋንዳ መምጣት የለበትም ሲል አንድ የሩዋንዳ አርበኞች ግንባር ቃል አቀባይ አስታውቋል። የሩዋንዳ አርበኞች ግንባር የኤርትራን ሠራዊት በብሄራዊ ሠራዊትነት እንደማይቀበለውና ይልቁንም የሽፍታ ቡድን መሆኑን በመግለጫው ጠቅሶ ይህን ሠራዊት መቀበል ሉአላዊ ክብርን ማስነካት ይሆናል ብሏል። የኤርትራ ጦር በሰላም አስከባሪ ኃይል ለመሰለፍ ጥያቄ ማቅረቡንና መሰናዶዎችንም ጨርሶ የሚንቀሳቀስበትን ጊዜ እየጠበቀ መሆኑም ታውቋል።

## የመንግሥት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ማፈራረሱ ቀጥሏል

የሽግግር መንግሥቱ የሚያካሂደውን የመዋቅር ማስተካከያ ፕሮግራም (Structural Adjustment Programme) በተጠናከረ ሁኔታ እንደሚገፋበትና በርካታ የመንግሥት ተቋሞች ሊታጠፉ እንደሚችሉ የሽግግር መንግሥቱ ባለሥልጣኖች ስለዚሁ ጉዳይ በተካሄደ ስብሰባ ላይ አስታውቀዋል። የመዋቅር ማስተካከያ ፕሮግራሙ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ብዙ ሠራተኞች ከሥራ ሊባረሩ እንደሚችሉ የገለፁት እነዚሁ ባለስልጣኖች ፕሮግራሙን በአፋጣኝ በሥራ ላይ ከማዋል ሌላ አማራጭ የለም ሲሉ ተደምጠዋል። መንግሥት ከሥራ ሊቀነሱ የሚችሉትን ሠራተኞች ቁጥር ባይጠቅስም የsafety net programme መቀየሱን አስታውቋል። አንዳንድ ምንጮች በመዋቅር ማስተካከያ ፕሮግራሙ ሥራ አጥ ሊሆኑ ይችላሉ የሚሏቸውን ሠራተኞች ቁጥር 80,000 እንደሚደርስ ይገምታሉ። ተዘጋጀ ስለተባለውም የsafety net programme አጥጋቢ ያልሆነና በቂ ጥናት ያልተካሄደበት ሲሉ ብዙ ወገኖች አይቀበሉትም። ይልቁንም ደግሞ የቀድሞ ሠራዊትን መልሶ በማቋቋም ረገድ የተከናወነው አጥጋቢ ያልሆነ ተግባር ከሥራ በሚፈናቀሉት ሠራተኞችም ላይ ሊደገም እንደሚችል በመስጋት መንግሥት ለፕሮግራሙ ያለውን ታማኝነት እነዚሁ ወገኖች ይጠራጠራሉ።አንድ ከፍተኛ የሽግግር መንግሥቱ ባለስልጣን ሰሞኑን በሰጡት መግለጫ በመንግሥት መ/ቤቶች ውስጥ ካሉት ሠራተኞችና ባለስልጣኖች መካከል 75% አማሮች ናቸው ሲሉ የተናገሩትን መሠረት በማድረግ የሥራ ቅነሳውም በጎሳ ላይ የተመረኮዘ ሊሆን ይችላል በሚል ዕምነት ከፍተኛ ስጋት አሳድሯል። እስካሁን በተወሰዱት የመዋቅር ማሻሻያ ፕሮግራሞች ከግልገል ግቤ፣ ከባህር ትራንዚት፣ ከኪራይ ቤቶች፣ ከጭነት ማመላለሻና ከሕዝብ ማመላለሻ ኮርፖሬሽን ከ6ሺ ሠራተኞች በላይ ተፈናቅለዋል።

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን በአለም ባንክና በአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ግፊት የሚካሄድ ነው ባለው የመዋቅር ማስተካከያ ፕሮግራም ምንም ተሳትፎ እንደሌለውና እንደማያውቀው ገልጦ በአስቸኳይ እርምት እንዲደረግበት ጠይቋል። ይህ ባይሆን ግን የኢትዮጵያ ሠራተኞች የራሳቸውን አማራጭ ለመውሰድ ይገደዳሉ ሲል ዝቷል። ይህ አማራጭ ምን ሊሆን እንደሚችል ግን በውል አልገለጹትም። በኮንፌዴሬሽኑ ሥር ከሚገኙት ፌዴሬሽኖች መካከል የምግብና መጠጥ ሠራተኛ ማኅበራት ፌዴሬሽን ይህንን አቋም በመቃወም የበኩሉን መግለጫ አውጥቶል። ሁኔታው ወደ መከፋፈል ሊያመራና የመላውን ሠራተኛ ትግል ሊያዳክም እንደሚችል ተገምቷል። የኢትዮጵያ የሠላምና የዲሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ም/ቤትም ዜጎችን ከሥራ በማፈናቀል ለረሃብና ለእርዛት እየዳረገ ነው ሲል

የሽግግር መንግሥቱን ኮንኗል። እያይዞም ከከፋ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ውድቀት አገርን ለማዳን ኢትዮጵያውያን ሁሉ ተባብረው እንዲታገሉ ጥሪ አቅርቧል። በመዋቅር ማስተካከያው ፕሮግራም ከተዘጉት መ/ቤቶች መካከል በመከላከያ ኢንዱስትሪ ሥር የነበሩት የጦር መሣሪያ ፋብሪካዎች ይገኙበታል። የእነዚህ ፋብሪካዎች የውስጥ ዕቃና በቀላሉ ሊተኩ የማይችሉ መለዋወጫዎቻቸው ወላልቀው መወሰዳቸውን የፋብሪካዎቹ ሠራተኞች በምሬት ይናገራሉ። በሌላ በኩል በአዲስ አበባ የሚገኘው የጥይት ፋብሪካ በራሱ ገቢ የሚተዳደር ኢንተርፕራይዝ ሆኖ በቦርድ እንዲመራ ተደርጓል። ይህንን ሁኔታ ከመከላከያ ኢንዱስትሪዎች ባሕርይ ጋር የማይጣጣም ነው ሲሉ ለጉዳዩ ዕውቀት ያላቸው ወገኖች ይተቻሉ። ፋብሪካዎቹ የፍጆታ ምርቶችን ሊያመርቱ የሚችሉ እንደመሆናቸው እንዲዘጉ መደረጉ ለዝርፊያ ማመቻቸት ነው የሚሉ ወገኖችም አልታጡም። በቅርቡ ቁጥሩ እጅግ ሊበዛ ይችላል ተብሎ በሚጠበቀው የሥራ አጥ ወገኖች መካከል በርካታ ነጋዴዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ተገምቷል። በመርካቶና በፒያሣ ከሁለት መቶ በላይ ሱቆች መታሸጋቸውንና ወደፊትም እንደማይከፈቱ መገለጹን መነሻ በማድረግ ይህ ግምት ተሰጥቷል።

## የአሜሪካን ፒስ ኮር ወደ ኢትዮጵያ ሊመለስ ነው

የአሜሪካ የሰላም ጓድ (ፒስ ኮር) በቅርቡ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው እንደሚመጡና በኢትዮጵያ መንግሥት ፍላጎት መሠረት በተለያዩ ዘርፎች እንደሚደለደሉ የሽግግር መንግስቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታውቋል። በ1968 ከኢትዮጵያ ለቀው እንዲወጡ የተደረጉት የአሜሪካን የሰላም ጓድ ተመልሶ መምጣት ሲ.አይ.ኤ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የተጠናከረ የስለላ ተግባር ለማከናወን እንጂ አገሪቱን የሚጠቅም አይደለም የሚሉ ወገኖች አሉ። ይልቁንም በመዋቅር ማስተካከያ ፕሮግራም በርካታ ዜጎች ከሥራ እየተባረሩ ባሉበት ወቅት የሠላም ጓዱ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ መደረጉን ለአሜሪካ ሥራ አጦች የሥራ ዕድል እንደመፍጠር ይቆጠራል ሲሉ ተቃዋሚ ወገኖች ይተቻሉ።

## የጤና ጥበቃ ሚኒስትሯ ከስራ ተባረሩ

የሽግግር መንግሥቱ የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ዶ/ር አዳነች ኪዳነማርያም ከአለፈው ሐምሌ ወር ጀምሮ ከሥልጣናቸው መነሣታቸውን መንግሥታዊ ያልሆኑ የዜና ምንጮች ዘግበዋል። የኢሕአዴግ ታማኝና ጠንካራ ደጋፊ ናቸው የሚባሉት የጤና ጥበቃ ሚኒስትሯ ከሥልጣን ስለመሰናበታቸው ከመንግሥት ምንጮች የተሰጠ ዜና ባይኖርም የታመኑ ምንጮች የሚኒስትሯን በጡረታ መገለል ዘግበዋል።

ዶ/ር አዳነች ኪዳነማርያም በሥልጣን በቆዩባቸው ዓመታት በርካታ የሕክምና ባለሙያዎችን አፈናቅለዋል ተብሎ ከፍተኛ ስሞታ ሲቀርብባቸው ቆይቷል። ኢሕአዴግ ሥልጣን ሳይዝ በፊት በሰሜን ክፍለሃገራት የመድሃኒት ስርጭት አድርጓል በሚል መነሻነት ከጤና ጥበቃ በጀት 11 ሚሊዮን ለኢሕአዴግ እንዲከፈል መፍቀዳቸውንና ይህም ውሳኔያቸው ትክክል ነው ብለው በግትር አቋም መግለጫ መስጠታቸውም በብዙ ዜጎች ዘንድ ጥላቻ ሳያተርፍባቸው አልቀረም። በተመሳሳይ ሁኔታ በቅርቡ ከሥልጣን የሚባረሩ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖች እንደሚኖሩም አንዳንድ ምንጮች ይገምታሉ።

## የኤርትራ ወታደራዊ እብጠት ለጎረቤቶችዋ ሊያሰጋ ይችላል ተባለ

የአዲሲቷ ነፃ ሀገር ኤርትራ መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ በማካሄድ ላይ ያለው የወታደራዊ ኃይል ማጠናከር ዘመቻ ለጎረቤቶቿ ለኢትዮጵያና ለሱዳን አስጊ ሊሆን እንደሚችል አንድ የዜና ምንጭ ዘግቧል። ኤርትራ ከታወቁ የአረብ አገሮች የውትድርና ኮሌጆች በተመረቁ መኮንኖች የሚመራውን የመከላከያ ኃይሏን በእስራኤል በመረዳት የቀድሞውን የጎሪላ ጦር በዘመናዊ መልክ በማደራጀት ላይ ትገኛለች። በቀድሞ የኢትዮጵያ ከፍተኛ የአየር ኃይል መኮንኖችና ቴክኒሽያኖች አማካይነት የኤርትራን አየር ኃይል ለመገንባት ከፍተኛ እንቅስቃሴ በመደረግም ላይ መሆኑ ተገልጿል። ሁለተኛ አብዮታዊ ሠራዊት የሚባለውን የቀድሞ የኢትዮጵያ ጦር ከባድ መሣሪያዎችና በትግሉ ዘመን ከተለያዩ ሀገሮች በዕርዳታ ያገኘችውን የጦር መሣሪያዎች ያካበተችው ኤርትራ ወታደራዊ እብጠት ለጎረቤቶቿም ሊያሰጋ እንደሚችልም ተገምቷል።

በሌላ በኩል ከ48 ሚሊዮን ብር በማያንስ ወጪ ኤርትራውያንን በብሄራዊ ውትድርና ፕሮግራም ለውትድርና እያሰለጠነች መሆኑንም የዜና ምንጮች ዘግበው አዲሲቱ ነፃ ሀገር ኤርትራ ወደፊት አምባገነናዊና ጠብ ጫሪ ልትሆን እንደምትችል ያመለክታል ሲሉ ታዛቢዎች ይናገራሉ።

## ዴር ሡልጣንና የግብጾች ጥያቄ

ኢትዮጵያ በኢየሩሳሌም በሚገኘው የዴር ሡልጣን ገዳም ያላትን የባለቤትነት መብት ለመንጠቅ ግብፅ ጥያቄ ማቅረቧንና በታሪክ ላይ የተመሠረተ ሕጋዊ ክርክር በመደረግ ላይ መሆኑን ጉዳዩን የሚከታተሉት ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ገልፀዋል። ብፁዕነታቸው እንደገለጹት ዴር ሡልጣን ገዳም የአምልኮ ሥፍራ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ርስትም ጭምር ነው ካሉ በኋላ የግብፆች ጥያቄ ፖለቲካን

ተንተርሶ መቅረቡንና የእስራኤል ጠ/ሚኒስትር እያዩት መሆኑን ጨምረው ገልፀዋል። የሽግግር መንግሥቱ ፕሬዚዳንት አቶ መለስ ዜናዊ በዚህ ጉዳይ ላይ እስከመጨረሻው ማንኛውንም ጥረት እንደሚያደርጉ በአሜሪካ ጉብኝታቸው ወቅት ቃል የገቡ ቢሆንም መንግሥታቸው ይህን ጉዳይ እስከመጨረሻው ሊከራከርበት ስለመፈለጉ ብዙ ወገኖች ይጠራጠራሉ። በተያያዘ ዜና ግብፆች በዴር ሡልጣን ላይ ባቀረቡት የይገባኛል ጥያቄ ጋር በተገናኘ ጉዳይ ብፁዕ አቡነ ጳውሎስ ፓትሪያርክ ዘኢትዮጵያ ወደኢየሩሳሌም መሄዳቸው ተዘግቧል። ስለፓትሪያርኩ ጉዞ ከመንግስት ምንጮችም ሆነ ከጽ/ቤታቸው የተሰጠ መግለጫ ባይኖርም እስራኤል አገር እንደደረሱ በጠና ታመው ህክምና ሲደረግላቸው እንደነበር የግል ሚዲያዎች ዘግበዋል። እርሳቸውም ወደ አዲስ አበባ በተመለሱበት ወቅት ይህንኑ አረጋግጠዋል። ጳጳሱ ከግብፅ የኮፕቲክ ቤተክርስቲያን ዕውቅና ለማግኘት ሲሉ ግብፆች በዴር ሡልጣን ላይ ያነሱትን የይገባኛል ጥያቄ ሳያስተናግዱ እንደማይቀሩ ስጋት አለ።

## በተለያዩ አካባቢዎች ግጭቶችና የጦር መሣሪያ ፍልሚያዎች

በጉንደር፣ በሰሜን ሸዋ፣ በጐጀምና በደቡብ ኢትዮጵያ ልዩ ልዩ አካባቢዎች ውስጥ ሕይወት የጠፋባቸው በርካታ ግጭቶች መደረጋቸውን የተለያዩ የግል ሚዲያዎች ዘግበዋል። ከጥቂት ወራት በፊት ከደብረብርሃን ከተማ ወህኒ ቤት እስረኞችን ለማስለቀቅ ከተወሰደው እርምጃ ወዲህ በሰሜን ሸዋ ቆላማና ጅረታማ አካባቢዎች የሽግግሩ መንግሥት ጦር በብዛት መስፈሩንና የተጠናከረ አሰሳዎችን በማድረግ ላይ መሆኑ ተረጋግጧል። በዚሁ አካባቢ በተደረገ የመሣሪያ ፍልሚያ ሸፍቶች ናቸው ያላቸውን መደምሰሱን መንግሥታዊ ምንጮች አስታውቀው ጉዳዩን የመአህድ እጅ እንዳለበት ጠቁሞ ነበር። ከአካባቢው በሚደርሰው መረጃ መሠረት መንግሥት መአህድን ለማጥፋት በሚያደርገው ጠንካራ እንቅስቃሴ ብዙ ዜጎች መተፈናቸውንና ቄአቸውን እንዲለቁ መገደዳቸውን ለማወቅ ተችሏል። ፕሮፌሰር አስራት ከታሰሩም ወዲህ ይህ ሁኔታ ተጋግሎ ሰንብቷል። ከተቃዋሚ ኃይሎች ጋር የሚደረጉትን ግጭቶች የግል ሚዲያ ፈጠራ ናቸው በማለት መንግሥት አነስተኛ ትኩረት የሰጠ ቢመስልም የተቃዋሚ ኃይሎች ወታደራዊ እንቅስቃሴ አለ በተባለበት ቦታ ሁሉ ሲንቀሳቀሱ የሚታዩት ብዛት ያላቸው የኢህአዴግ ሠራዊት አባሎች የጉዳዩን አሳሳቢነት እንደሚያመለክት ይገምታሉ። በጉንደርና በጐጃም እንዲሁም በደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች በተመሳሳይ ሁኔታ ከባድ መሣሪያዎችን የታጠቀና በተጠንቀቅ የሚንቀሳቀስ የኢህአዴግ ሠራዊት መታየቱንና የህዝቡም ሰላማዊ ኑሮ መታወኩን ከአካባቢው የሚደርሱ መረጃዎች ይጠቁማሉ። መንግሥት ሰሞኑን በሰጠው መግለጫ በአዋሳና በአካባቢው የጦር መሣሪያ ታጥቀው የሚንቀሳቀሱ ሽፍቶችን ለመያዝ አሰሳ ማድረጉን ይፋ አድርጓል። ይህ ሁኔታ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች ሊኖር ይችላል ተብሎ የሚሰጋውን የተቃዋሚዎች እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ሳይሆን እንዳልቀረ ተገምቷል። በብዙ ከተሞችም አፈናና እንደወጡ መቅረት የዕለት ተዕለት ክስተት ሆኗል።






# Addisu Gebeya አዲሱ ገበያ

## We Carry Large Selection Of Ethiopian Foods & Spices

***We have everthing you need to prepare an Ethiopian Feast !***

| DESCRIPTION | QTY(lb) | Price |
|---|---|---|
| 1. Berbere | 1/2 | 3.99 |
| 2. Miten Shiro | 1/2 | 3.50 |
| 3. Aja | 1/2 | 3.50 |
| 4. Mitmita | 1/2 | 3.50 |
| 5. Awaze | 1/2 | 3.99 |
| 6. Butter Maker | 1 | 13.99 |
| 7. Tef | 1 | |
| 8. Mekelesha | 1 | 13.50 |
| 9. Kik | 1 | 0.49 |
| 10. Bakela | 1 | 1.79 |
| 11. Miser | 1 | 0.89 |
| 12. Kinche | 1 | 0.39 |
| 13. Telba | 1 | 1.25 |

NAME__________
ADDRESS__________
__________
CITY__________
STATE_____ ZIP_____
Tel. (   )__________

**WE DO MAIL ORDER**

Please Include $5.50 For Shipping And Make Your Check Or Money Order Payable To: Addisu Gebeya

- JEWELRY
- VIDEOS
- CASSETTES
- REKEBOTE (ረከቦት)
- COFFEE
- ETHIOPIAN ARTS
- ETHIOPIAN DRESS

AND MUCH MORE

2202 18th St. N.W.,
Washington, DC 20009
202 •986 •6013 / 23

# ኢትዮወርድ EthioWord

የተሟሉና የማይቀጠሉ የሞዴት ፊደላት፣ አጻጻፎችና አቀራረቦች ቦታዎቻቸውን እንደጠበቁ ብዙ የዊንደውስ ፕሮግራሞች ውስጥ በቀጥታ በግዕዝ ለመጻፍ • ወደ እና ፔጅሜከር ለማዛወርና እዚያም ለማረም • ለገቢ ወጪ፣ ለደረሰኝ፣ ለፎርሞች... • Type *Ethiopic* in dozens of *Windows* applications with our complete (world font) characters and alphabets with pop-up on-screen keyboard. • Import/export and edit in *Microsoft Word.* • ኢትዮዊን ከፊደል መለጠፊያና ኢትዮወርድ ጋር

**ሞዴት ModEth $400.00**
The scientific *Ethiopic* publisher for DOS

$280.00 ብቻ

FAST • EASY TO USE • PERFECT AND

የኢትዮጵያ ኮምፒዩተሮችና ሶፍትዌር
Ethiopian Computers and Software
9781 W. Fremont Pl., Littleton, CO 80123, USA
Tel.: (303) 972-2186 • Fax: (303) 973-4342

*The pioneers of Ethiopic (Geèz) computing since 1982.*


ሞዴት፣ ኢትዮእስኬለር፣ ኢትዮዊንና ኢትዮወርድ የአብሻ የንግድ ምልክቶች ናቸው።
ModEth, EthioScaler, EthioWin and EthioWord are trademarks of ABSHA Ltd.

ሀናና ብንያም
የልብስ ስፌትና ዲዛይን

## H & B TAILORING

Alteration & Dressmaking

Fashion Designer



**ወለላ ወርቁ**

የተለያዩ የአገር ባህል ልብሶች እንሸጣለን።

ከብር የተሰሩ የአንገት ጌጦችም አሉን።

ጎብኙን!!

431 North Indian Creek Rd.
Suite E
Clarkston, GA 30021
Phone: (404) 296-2766



ኢንተርናሽናል ፊልምና ቪዲዮ
International Film & Video

**ታደሰ አስራት**
**Tadesse Asrat**

የጋብቻ ሥነ ሥርዓትን
ክርስትናን ልደትን እንዲሁም ቤተሰብዎን
በቪዲዮ ለማስቀረጽ ከፈለጉ

I F V



በስልክ ቁጥር
(404) 377-4058 ይደውሉልኝ።

ከኢትዮጵያ የመጡ ቪዲዮ ቴፖችን ወደ አሜሪካን ሲስተም በተጨማሪ የአሜሪካን ቪዲዮ ቴፖችን ወደ ኢትዮጵያ ሲስተም መቀየር ይቻላል።


*Notice to*

## ETHIOPIAN REVIEW READERS

*in Atlanta*

*The monthly issues are available at the following locations:*

**1. Sweet Auburn Grocery**
*210 Auburn Ave.*
*Atlanta, GA*
*Phone: (404)577-6756*

**2. Terrific Package Store**
*1901 Cheshire Bridge Road*
*Atlanta, GA*
*Phone: (404)872-4294*


EXECUTIVE BROKERS
REAL ESTATE

ጊፍቲ ታማክሎ
GIFTY TAMAKLOE

When buying or selling a home
call GIFTY TAMAKLOE

Assumptions
HUD & Foreclosures
Resales
Down Payment Assistance

New Homes
NQNE - No Credit Check
Some bankruptcies OK

**ጊፍቲ ታማክሎ**
**ቤት ለመግዛት ወይም ለመሸጥ**

*For Professional, Caring, Dependable & Determined Service*

4319 Covington Highway, Suite 312
Decatur, GA 30035
Office: (404) 288-3366
FAX: (404) 288-3360
Voice Mail: (404) 871-6209

# ጥ ን ቅ ር
# ከዚህም ከዚያም

● ሹክሹክታ

"ጥሪ የተደረገላቸው ሳይሆን ተጠርተው አሜሪካ የሄዱትና ለ20 ደቂቃ ነጩን ቤተ መንግሥት የረገጡት ፕሬዚዳንታችን የዛሬ አስር ዓመት በቀን ሶስቴ መብላት የሚችል ሕዝብ ለመፍጠር መሻታቸውን ቃል ገቡ። ሕዝቡ በቀን ሁለቴ እንዲበላ አድርገነዋል ብለው በተናገሩ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሶስተኛው ማዕድ በጉጉት ሲጠበቅ ምነው ወደ አስር ዓመት ወሰዱት? ተስፋ የሰጡ እየመሰላቸው ተስፋ ማሳጣታቸውን አልተገነዘቡምን? ግን እኛም እሳቸውም አሥር ዓመት አብረን ስለመቆየታችን የተፈራረምነው ውል አለ?

● "ዕርዳታ ማስተባበሪያ ስንቱን ተኩላ ተሸክሞት ነው የኖረው? አንዴ በደቡብ፣ ሌላ ጊዜ በምሥራቅ ይህን ያህል በቆሎ፣ ይህን ያህል ስንዴ ሰርቆ ሸጠ፣ እከሌ የሚባል የኮሚሽኑ ሰራተኛ ተያዘ ይባላል። ሲሰርቅ የተገኘውስ ተያዘ። ሳይታይ የሚዘርፈውስ? ከለማኝ ከሚቀማ ለማኝ አምላክ ይሰውር ቢባልም እስከመቼ በጅብ ሥጋ እየጫኑ መኖር ይቻላል?
(ጠማር)

● አብዮት ልጁን ትበላለች?

ከግንባር ቀደም "የሁለተኛ አብዮት" ልጆች መካከል ዶ/ር አዳነች ኪዳነማርያም ይገኙሉ። ከትጥቅ ትግሉ ሜዳ እየተከሱ ባይመጡም እነዚያ አስራ ሰባት ዓመት የፈጀባቸውን እሳቸው በሶስት ዓመት ለማካካስ ሳይሞክሩ አልቀረም። "የድል አጥቢያ አርበኞች" -- እዚሁ ከእኛ ጋር የቆዩት -- በጫካ ከቆዩት ጋር ለመስተካከል ብዙ ጥረዋል። የውሸት ጩኸት ጮኸዋል። የዕለት ጥቅም ያገኙ፣ ሥልጣን ላይ የቆዩ መስሎአቸው ፖለቲካውን አተራምሰውታል። ዶ/ር አዳነችም "ማንም ሰው ሊተካ ይችላል (ኢንዲስፔንሴብል አይደለም) ይሉ ነበር። በወርቃማ ፊርማቸው ስንቱን ሐኪም ወደ ጋምቤላ፣ ወደ ጡረታ፣ ወደ ስንብት ሲሉት ከርመው ከርመው በመጨረሻ የእሳቸውም ተፈርሞ ደረሳቸው። "አብዮት ልጇን ትበላ ጀመር? ማነው ባለሳምንት?
(ጠቢያ)

● "ይኸ ወደ ሰማይ ቢደረደር ፎቅ ሊሰራ የሚችለው የእርዳታ ገንዘብ ተሰብስቦ ከምን እየገባ ነው? እውነት ዕርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን መዋቅሩን እስኪያሻሽል ድረስ እህል አይገዛም? ረሃብተኛው አይመገብም? ወይንስ ረሃቡንም እንደነፍጠኞችና ትምክህተኞች ድንበር ከልሎ መጠበቅ ይቻላል?

በሰማይ በምድር ገስግሶ ረሃቡ ቤተመንግሥት የገባ ዕለት ነው ጉድ! . . . ይሄ የለሰለሰ አንጀት፣ የደነደነ አንገት፣ ያለጠለጠ ጉንጭ ጉድ እንዳይፈላበት!

● "ፕሮፌሰር አሥራት ወ/የስ፣ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም፣ ፕሮፌሰር አየናቸው እጅጉ፣ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ፣ ሟርት አያድርገውና ከእኔ በፊት ቢሞቱ በሐውልታቸው ራስጌ የሚፃፍ አንዳንድ ቃል (Epitaph) ይኖረኛል። እኔ እቀድማቸዋለሁ ብዬ እንጂ ለፕሮፌሰር ጀማል አብዱልቃድር፣ ለፕሮፌሰር እንድሪያስ እሸቴ፣ ለፕሮፌሰር በረከት እንዲሁ ባወቅኋቸው መጠን ሐውልታቸው ላይ የሚቀረጽ ጽሁፍ ይኖረኛል። ለኋለኞቹ ከማስቀረጻቸው ቃላት መካከል:-

1ኛ) "ለዚሁ ነበር?
2ኛ) "ሁሉም እንዲህ ሊቀር!"
3ኛ) "ይህ ጀግና የሚያስበው በሆዱ ነበር . . . " የሚሉ ከብዙ በጥቂቱ ሲሆን ዕድሜ ከሰጠኝ ግን ሌሎች ውብ ማስታወሻዎች እየፈጠርሁ እቆያለሁ።
(ጠቢያ)

● በነገራችን ላይ ሩቅ ያሉት ወዳጆቻችን ለተራበው ወገናችን እጃቸውን ሲዘረጉ የቅርቧ ወዳጅ አገር ኤርትራ ምነው ከንፈሯን አልመጠጠች? ከራስ ካሳር እስከ ራስ ዱሜራ የተንጣለለ ባሕር ተንተርሣ እየተኛች እሣ እንኳን ብሉ አላለችን? ከብሪት ብቻ ነው የምታራግፍብን። ጭራሽኑ ወደቧ ላይ የተራገፈው የእርዳታ እህል ይጠፋል ተብሎ ይታማል። ከለማኝ ለማኝ ቁሩንጮ ቀማኝ እንዳይሆን እንጂ ነገሩ!



# እንዳው አንድ ጥያቄ አለኝ ! !

● ዙሪያ ዙሪያውን ድርቅ ገብቷል። ከከተማችን እህል ሲጠፋ ምን ልንሆን ነው?
አሰፋሽ - ከፍልውኃ
* አይዞሽ ለአዲሱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ምሥጋና ይግባውና ጦር ማስቲካ አሥር ሳንቲም ገብቷል።
* * *

● "ነፃ ፕሬስ ለነፃ ሕዝብ ትላላችሁ። ለመሆኑ እኛ ነፃ ሕዝቦች ነን?
አሰገደች ደገፋ ከአ.አ
* ብትሆኚማ ነው ተጣጥፈሽ የምትተኚው።
* * *

● ለግንቦት 20 በየቀበሌውና በየት/ቤቱ ለሠልፍ የወጣው ገንዘብ ለድርቁ ዕርዳታ ቢውል ምን ነበር?
አሊ አከባር - ከደሴ
* ወይ ነዶ! ካለፈ በኋላ ነው የምታስታውሱት!
* * *

● የፕሬዚዳንታችን ሃይማኖት ምንድነው?
ዮሐንስ ጣሰው - ከዱከም
* የፓትሪያርኩን ካወቁት በቂ ነው።
* * *

● ሚዜ መሆን ስለቸኝ ይኸው አምስተኛዬ ነው። መላው ምንድነው?
ብሩክ - ከግንፍሌ
* አታግባና በየጋዜጣው መላው ምንድነው እንዳልክ ኑር።
(ጦማር)
* * *

● በዋሽንግተን የፕሬዚዳንት መለስ ደጋፊ የሆነች ሴት "ጓድ መለሰ" እያለች ስትጮህ በVOA ሰማሁ። ሰውየው ጓድ ናቸው እንዴ?
ማሩ ጋርደው - ከዘበኛ
* ምን ይሳናቸዋል?
* * *

● ይሄ ሁሉ ሠራተኛ ከሥራ ተቀንሶ ደመወዙ ምንድነው የሚሠራበት?
ቶማስ - ከመገናኛ
* ሺህ ካድሬና ሺ ልዩ ፀጥታ ቢቀጠርበትስ!
* * *

● የዘር ፖለቲካ የሚሉት ነገር በሽታ ነው እንዴ ጎበዝ?
መሠረት - ከናዝሬት
* ያውም ኤድስ ነዋ!
* * *

● አሁን ማን ይሙት ክሊንተን የመለስን አመራር ያደነቁት ከልባቸው ነው?
ሺፈራው ቱጂ - ከአምቦ
* ዲፕሎማሲና ፈረንጅ ምላጭ ናቸው።
* * *

● አሜሪካንን የጎበኙት ገዥዎቻችን መስተንግዶአቸው በታክሲ የሆነው ለምንድነው?
የሺመቤት አባተ - ከአዲስ አበባ
* ተቃዋሚን ለመሸወድ ወይም ክብር በመነፈግ ይሆናላ።
* * *

● የጤና ጥበቃ ሚኒስትሯን ዕጣ ሰማን። የሌሎቹን ወይዛዝርት ሹሞቻችን ጉዳይስ እንዴት ይሆን?
ወሰን - ከቢስ መብራት
* "አይዞሽ ሙሽሪት . . . ሁሉም ይዳራል በየወረፋ" ይባል የለ!
* * *

● የአይጥ መርዝ በየጎዳናው ሲሸጥ ማየቱ ይዘገንነኛል። የሚመለከተው አካል ምናለ አንድ መፍትሄ ቢወስድ?
የሺመቤት ሙላት - ከአ.አ
* ምን አካል አለና!
* * *

● መሪዎቻችን ለምንድነው የእግዚአብሔርን ስም የማይጠሩት?
አሥራት - ከደብረሲና
* ሌኒናዊ መፈክሮች መች ወርደው አለቁና።
(ጦማር)
* * *

● የካፒታሊዝም የመጨረሻ ደረጃው ኢምፔሪያሊዝም ነው። የሶሻሊዝም የመጨረሻው ደረጃ ደግሞ ኮሙኒዝም ይባላል። የዲሞክራሲ የመጨረሻ ደረጃ ምን ይሆን?
ሠለሞን ታፈሰ - ከጂማ
* ወህኒ ቤት
(ተናገር)
* * *

● ጠቅላይ ሚኒስትራችን የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የወሰዱት በቅንጣ ሣይንስ ነው የሚባለው እውነት ነው?
ሥምረት ፈለቀ - ከአ.አ
* ዲግሪ አላቸው እያላችሁ ባትስድቧቸው መልካም ነው።
* * *

# እንዳው አንድ ጥያቄ አለኝ !

● ከብራዚሉ ኮከብ ተጨዋች ከሮማሪዮ ፍቅር ይዞኛልና እንዴት ልሁን? ትዕግስት - ከካዛንቺስ
* ኳስ ሁኚ።
* * *

● የሠሞኑን የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ፕሬዚዳንቱ ለምን ሳይመርቁ ቀሩ?
ኤልሣ - ከስድስት ኪሎ
* እሳቸው መቼ መርቀው ያውቃሉ?
* * *

● ምግቡ ሚጥሚጣ ነው የሚጠጣው ካቲ
እኔም እስቱፒድ ነኝ ኢትዮጵያ መምጣቴ። ብሎ የዘፈነው ማነው?
ፀጋዬ - ከታክሲ ተራ
* ዘፋኙ "ኤድስ" ነው ይባላል። እንደእኛ ግምት ይህን የሚሉት የኤድስን ቀሣፊነት ያልተረዱ ሰዎች ይመስሉናል። መጠንቀቁ ይበጃል።
* * *

● አሁን ት/ቤት ሲከፈት ከፍዬ ልማር ነው?
የሱነሽ - ከመርካቶ
* ወደሽ ነው ገጣቢት ንጉሥ ትመርቂ ያለሽ።
* * *

● ባለፈው ወር ከ1500 በላይ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች መመረቃቸው አላስደተህም?
አክሊሉ ነጋሽ - ከጎንደር
* 1500 ሥራ አጥ ማፍራት አይደል! ለምን እያስደስት።
* * *

● አባ ጳውሎስ የሲኖዶሱን አባላቶች በሙሉ ዘር እየቆጠሩ መመልመላቸው አያናድድም?
ሻረው ቆቱ - ከአ/አ
* ገሚሱ ዘር ቆጠሩ ይሏቸዋል። ሌላው ታጋይ ጳውሎስ ይሏቸዋል። ምነው በብፁዕነታቸው ባትመጡብን! በወርቅ መስቀላቸው ባታስረግሙን!
* * *

● ይህን ረሃብ አስመልክቶ "ተፈጥሮ ባደረሰብን . . ." እየተባለ እግዚአብሄር ተረሣ እኮ! ይሀቺ አገር በአህዛቦች እስከመቼ ትታመስ?
ፈጠነ - ከአ.አ
* ፈጣሪ ይቅር እስኪለን።
* * *

● ለመሆኑ ቤተመንግሥት ቁልፍ አለው ወይ?
ሠላማዊት - ከአ.አ
* ምን አማረሽ ደግሞ!
* * *

● ፕሬዚዳንት መለስን በጣም እወዳቸዋለሁ። እባካችሁ እኚህን ተወዳጅ መሪ በክፉ አታንሡብኝ?
ሰዓዳ - ከጀጎል
* አንቺ ለምትጋግሪው እንጀራ እሳት እንቆሰቁስም።
* * *

● ሁሉም ነጋዴ ሆነ። ይሀቺ አገር የቸርቻሪዎች አገር ልትሆን ነው እንዴ?
ብሥራት - ከመገናኛ
* ምን ይደረግ እንሽቃቀጥ እንጂ!
* * *

● ብልጠት በበዛበት አገር መኖር ሰለቸኝ ምናለበት ሁላችንም እንደርግብ የዋህ ብንሆን?
ቤተልሔም - ከ6 ኪሎ
* እርግቧም ብልጥ ሆናለች። ሁሉም እየማለባት!
* * *

● በአሁኑ የዓለም ዋንጫ ውድድርና በሕገ-መንግሥቱ አርቃቂ ጉባኤ ምርጫ ውድድር መካከል ምን ልዩነት ታያችሁ?
ማሩ ጋርደው - ከዘበኛ ሠፈር
* የኛዎቹ ያለማጣሪያ ነው ያለፉት።
* * *

● ፕሬዚዳንታችን ህዝቡ ሁለቴ በልቶ እንዲያድር አድርገነዋል። ጥረታችን ሶስት ጊዜ እንዲበላ ነው ያሉት ሶስተኛው የት አለ?
ሹምዬ - ከፈት በር
* ከዚህ በላይ ምን ቀረ ደግሞ? ሣርና ቅጠል እየተበላ ነው እኮ!
* * *

● አቶ ኢሣያስ በጉብኝት ሰበብ ወደ አዲስ አበባ እየተመላለሱ የውኃ መንገድ አደረጉት ምነው?
ሡልጣን ሻፊ - ከአዋሳ
* ለግምገማ ይሆናል።
* * *

● ኢሕአዴግ ሕዝባዊ መሆኑን በሠሞኑ ምርጫ አያችሁ አይደል? አሰፋ ገብሩ - ከፒያሳ

* በሬዲዮ ሰማን።
* * *

ልብወለድ

# የላጤው ኑዛዜ

(እንዱዓለም ከአ.አ)

ያለፈው ሰኔ የሥርግ ጎርፍ ካጠናቀቃቸው ወንደላጤዎች አንዱ ነኝ። ጠና ጠና ካሉት ወንደላጤዎች እንዲያውም ግንትር ያልኩት አሮጌው ሙሽራ እኔው ሳልሆን አልቀርም። . . . እድሜዬ የትየሌሌ ነው። ብዙው ተጋምሷል። ነጉዷል። ዕድሜ ደጉ ተንዘላዝሎ ተንዘላዝሎ ደህና ተገባዷል። ዕድሜዬ ስንት እንደሆነ በውል አላውቀውም። ከእንጀቴ ነው በውል አላውቀውም። ደግሞስ ዕድሜ ዝም ብለው ቢቆጥሩት ከምን ይገባል? ጥቅም ላይ ያልዋለን ሁሉ ቢቆጥሩት ምን ይፈይዳል? . . . ትውልዴ ካራ ቆሬ፣ ዘሬ እንደድሃ እህል ቅይጥይጥ ነው። ከአማራው፣ ከአርጎባው፣ ከኦሮሞው አለብኝ። በሁለት ኮረብታዎች መሃል እንደ ባልቴት ዝንጀሮ የተጣበቀችውን ካራ ቆሬን እስረኛና የወሎ መንገደኛ ካልሆነ ሌላው ብዙም አያውቃትም። አባቴ ሳልወለድ በፊት ወደ ከረዩ አገር ጥጥ ለቀማ ወርዶ በዛው ቀልጦ ቀርቷል። ይኑር ይሙት አይታወቅም። እናቴ የተወለድኩበትን ዘመን በትክክል አታውቀውም። ዓመተ ምህረት የሚሉት ነገር ደግሞ አይገባትም። . . . በመምሬ እከሌ ግብዝና ዘመን ክረምቱን ወጥተን አዝመራው ላይ ነው የተወለድከው ትለኛለች። አባ እከሌ የሞቱ ዘመን . . . እቴዋ እከሊት የተዳረች ዓመት ስትል ታብራራልኛለች። ዓመተ ምህረቱን ከእርሷም ሆነ ከዘመዶቿ የሚያውቅ አልተገኘም። እንዲያውም ዕድሜዬን አለማወቄ ደግ ነገር ነው። ምን ያደርጋል? . . . በቃ ተወልጃለሁ፣ አድጌያለሁ፣ አለሁ፣ እኖራለሁ፣ እርሱ የፈጠረኝ እስከፈቀደ ድረስ እቆያለሁ። ለነገሩ አርባውን ሳላጋምሰው አልቀርም።

ስንት ጥር ስንት ሰኔ አልፎ ዕድሜ እንደዋዛ ገስግሶ በማነህ ማነህ ተጋምሶ እነሆ በዘንድሮው ሰኔ ሞልቶልኝ ተሞሽሬ ዛሬ ባለትዳር ነኝ። የኮራሁ የደራሁ አባወራ! . . . የደም ገንቦ የሆነች ቁምጥጥ ያለች ቆንጆ ሚስት ያለኝ ወጥቼ እስከመለስ "ምን ሆኖ ይሆን? ምን አገኘው ይሆን?" ብላ ተጨንቃ ተጠባ የምትጠብቀኝ፣ ራበው ጠማው ብላ ጣፈጠልኝ አልጣፈጠልኝ ብላ ተጨንቃ ለወስፋቴ የሚሆን አብስላ የምትቆየኝ፣ ሙያዋ እጅ የሚያስቆረጥም ሚስት አባወራ ነኝ። . . . የቀዛ ወለም ዘለም ቀርቶ ከበርቻቻ፣ አስረሽ ምቺው፣ የባንኮኒ ላይ ድንፋታ የተሰናበትኩ . . . ሽንጥ ዳሌ ቁመና ውበት ደም ግባት እያልኩ የሰው ቆንጆ መጎምጀት የማይነካካኝ። ስንቷ ዘመናይ ቀርታ እነ ቆንጂት እነ ጎራዲት ተረስተው ሶስት ጉልቻ የመሰረትኩ ቤቴ ቤቴ ትዳሬ ትዳሬ የምል አባወራ ነኝ።

በዚህ ሁሉ የወንደላጤነት ዘመኔ እንደአቅሜ ከቢጤዎቼ ጋር መዳራቴ ባይቀርም የሴት ነገር አይዋጣልኝም። ከእንጀቴ ነው አይሆንልኝም። መቼም ያለፈ ነገር ስለሆነ እውነቱን ማውጣቱ ደግ ነው። ሴትን ልጅ ቀርቦ መተዋወቅ ራሱ የዳገት ያህል ነው የሚከብደኝ። እንዴ ተቀረቡኝ ደግሞ መወደዴን እንኳ እርግጠኛ ሳልሆን ፍቅር ብን ትክን ያደርገኛል። ኑሮዬን ትቼ ፍቅረኛ ተብዬዋን ሳሰላስል መሽቶ ይነጋል። በጀርባዬ ባዝላት፣ እንኮኮ ብላት አይከብደኝም። እዚህ ግቢ የማትባለዋ ሾጢ እንኳ በየቀኑ አንድ ነገሯ ውብ መሆኑ ቆንጆ መሆኗ ይታወቀኛል። ሴቱ ደግሞ መወደዱን ሲያውቅ ኩራቱ አይጣል ነው። የምክንያቱ አበዛዝ፣ የሰበብ አስባቡ ዝርዝር አያድርስ ነው። አንዳንዷ መወደዷን ስታውቀው ወጠምሻ ወጠምሻ ጎረምሳ እስከትላ የአክስቴ ልጅ ነው ማለት ትጀምራለች። በአጋም ሆነ በቀጋ የማትዛመደው ሁሉ ዘመዷ ይሆናል። ጀነን ኮራ ድክም ያደርጋታል። እንደመንቀባረር እንደመዘባነን ይሞክራታል። እኔ ደግሞ ቶሎ አይገባኝም። ፍቅር ብለን መውደድ ገዶን የተገናኘን ሰዎች አንደኛው በሌላኛው ላይ ምን የሚያኮራው ነገር አለ? የሚሉት ዘይቤ አለኝ። ሴቱ ሁላ ዋና ይዞ በትርፍ የሚነግድ መሆኑን ያወቅሁት ኋላ ኋላ ነው። ጅላፎ ቢጤ ቂላቂል ነኝ መሰል ዕሁድን ሰንበት ነው ካላሉኝ አይገባኝም። እየተኮራብኝ መሆኑ እንኳን የሚገባኝ ከረጅም ጊዜ በኋላ ነው። የተወደድኩ መስሎኝ ስንጋፈፍ ስንጋፈፍ ከርሜ የኪሴን አራግፌ የእጄን ጨርሼ አብቅቼ ነው መሞኘቴ የሚገባኝ። የተረዱኝ መስሎኝ አንድ ሳላስቀር የልቤን ዘርዝሬ ስንዘራዘር፣ ስተረተር፣ ገበናዬን ስዘከዝክ ከርሜ ነው የተቀለደብኝ መሆኑ የሚታወቀኝ። ከቁጥር የማልጣፍ ዋና ተይዞ በትርፍ የሚነገድብኝ "ተለዋጭ" ቢጤ መሆኔን የምገነዘበው የማታ የማታ ነው። . . . ማፍቀር እንዴት ሞኝነት ይሆናል? የተወደድኩ መስሎኝ ልቤ ቢረታ፣ እንዴት ከጅልነት ይቆጠርብኛል? . . . ለፍቅር ብዬ ብበለጥ፣ ለመወደድ ብዬ ዝቅ ብል፣ ለፍቅረኛዬ ደስታ ብዬ የእጄን ሁሉ ብጨርስ እንዴት ከጥፍራምነት ይቆጠርብኛል?

ያለፍኩትን የወንደላጤነት ሕይወት ሳስበው ምስቅልቅል ያለ ውል የሌለው የሃሳብና የትዝታ ጉዞ ከፊቴ ይደቀናል። . . . ከስንቷ ጋር ነበርኩ? ስንቷስ ከእኔ ጋር ነበረች? ስንቷስ ከልቧ አፍቅራኝ ይሆን? ስንቷስ ዋናዋን ይዛ "ትርፍ" አድርጋኝ ይሆን? . . . እኔ አላውቅም ከእንጀቴ ነው አላውቅም። ብቻ ነገራቸው የማይረሱኝ እኔ ተወደድኩ ብዬ ደፋ ደፋ ስል ያሾፉብኝ የማይዘነጉኝ ሴቶች አሉ።

የአዜብን ነገር እስከመቼም አልረሳውም። አገባሃለሁ ስትለኝ ከርማ ጓዳዬን፣ ገንዘቤን አስረክቤአት እሷ ግን የልቧን በልቧ ይዛ ፓስፖርት አውጥታ በራሴው ገንዘብ ትኬት ገዝታ ሳልሰማ

ሳላውቀው ግሪክ አገር ጥላኝ ነጎደች። የአበባም ነገር እይዘነጋኝም። የወደደችኝ መስሎኝ ስንት ስሆንላት ከርሜ ስበቃት አንብባ እንደጨረሰችው መጽሐፍ ዘጋችኝ። በየቀኑ ተገናኝተን የምንነፋፈቅ የነበርን ፍቅረኛሞች ኋላ ኋላ እንደመንጠባረር እያደረጋት በየቀኑ መገናኘት ቀርቶ በሳምንት እሱም በዛና በወር ሆነ። ስራ በዝቶ፣ እክስቴ ከውጭ መጥታ፣ የቤተሰብ ስብሰባ፣ የጓደኛ ማህበር፣ . . . የምክንያቱ ዓይነት ይደረደርልኛል። እኔ ደግሞ ላሜ ቦራው እውነት መስሎኛል። በኋላ ከአንተ ጋር ከታክሲ ታክሲ መገለባበጥ ሰለቸኝ ብላ አረፈችው። ቆይቼ ስሰማ የአክስቴ ልጅ ብላ ካስተዋወቀችኝ ፀጉሩን ጋሜ ከተቆረጠው ወጠምሻ ጎረምሳ ጋር ትወዛወዛለች አሉኝ። ይህቺ መናጢ የመናጢ ልጅ ለእሷ ቀሚስና ጫማ ያወጣሁት ገንዘብ፣ ለፀጉሯ መሰሪያ፣ ለጥፍር ቀለሟ፣ ለከንፈር ቀለሟ፣ ለሻዶው፣ ለሜካፕ ያወጣሁት ወጪ፣ ለወር መዳረሻ፣ ለትራንስፖርት እያልኩ የከሰከስኩት ፍራንክ መኪና አይደለም አገር ይገዛልኝ ነበር።

የወንደላጤነት ዘመን የመጨረሻ የሆነችውን ትርሲት ዘሪሁንን ሳስባት ለራሴም ይገርመኛል። ከእርሷ ጋር ያሳለፍነው የፍቅር ጊዜ ሳይሆን የወሲብ ወቅት ነበር። ከመነሻው ተናናቅን። እርሷም ናቀችኝ። እኔም ናቅኋት። እየተናናቅንም ቢሆን ግን ሁለታችንም አብረን መቆየት እንፈልጋለን። . . . ትርሲት ዘሪሁንን ያወቅኋት አንድ የምረቃ ፓርቲ ላይ ነው። እኔና ሶስት ጓደኞቼ ነበርን። እንደእኛው የተጋበዙ ቆነጃጅት ጥግ ጥጉን ይዘው ተኮልኩለው ወሬያቸውን ይሰልቃሉ። ጥንድ ጥንድ ሆነው የመጡ ተጓዳኞችም ነበሩ። እንደኛው ጓደኞችን በሴት ነገር ኩቲ ነው። ውሻ ቢጤ! እየተቅለሰለሰ ሴትን ልጅ መድፈር ያውቅበታል። እኔ ደግሞ አይሆንልኝም። ከአንጀቴ ነው አይሆንልኝም። ከእኛ ጋር ተቀምጦ ማዶ ለማዶ በዓይኑ እየተጠቃቀሰ እኛ ሳናውቀው አከፋፍሎን ጨርሷል። በኋላ ዳንስ ሲጀመር ትርሲትን ጠርቶ አስተዋወቀንና የራሱን ድርሻ ይዞ መደነስ ጀመረ። ይህቺኛይቱ የእኔ ድርሻ መሆኗ ነበር። ነገሩ ዱብ ዕዳ ሆነብኝና ለብዙ ጊዜ ዝም ተባባልን። "ተጫወቺ እንጂ" ብቻ ሆነ። በኋላ አብረን ደነስን። ያቅሜን ያህል ወንከር ወንከር አልኩ። ዳንስ ብሎ ጨዋታ አልወድም። ደግሞም አላውቅበትም። ልልመድህም ብለው አልሆነልኝም። እኔ ያደኩት ካራ ቆሬ፣ ልጅነቴ ያለፈው በከብት እረኝነት . . . ዳንስ ብሎ ነገር ከየትአባቴ ልወቀው። የዚያን ዕለቱ ግንኙነታችን መነሻ ሆነና ይበልጥ ተቀራረብን። መገናኘትም ጀመርን።

ትርሲት ቆንጆ ባትሆንም ቁመናዋ የተስተካከለ ነው። እርሷም ይህን የምታውቀው ይመስላል። በምታደርገው ሁሉ ቄንጥና ቅላጼ ትጨምርበታለች። አካሄዷ፣ አነጋገሯ፣ አስተያየቷ ሁሉ በቄንጥ ነው። የድምጿ ቅላጼ የወሲብ ቅላጼ አለው። ወሲበኛ ቢጤ ናት። ጨዋታችን ጨርሶ አይጣጣምም። የአራምባና ቆቦ ያህል ነው።

. . . እኔ ስለ ካራ ቆሬ ዘመዶቼ፣ ስለእረኝነት ትዝታዬ፣ አልዩ አምባ ስላሉት የአባቴ ዘመዶች ላወራት እሻለሁ። ከውሪ አብሮ አደጎቼ ጋር የተንቦጫረኩትን የሠፈሬን ኩሬ፣ ሌጣ ፈረስ ስለጋለብኩበት የአገሬ መስክ፣ በአውዳመት የጨፈርኩበትን ቀዬ፣ አዲስ አበባ ተመምጣቴ በፊት የዘፈንኩበትን መስክ፣ በእንቁጣጣሽ ስለሳምኳት ከንፈር ወዳጄ ላጫውታት እፈልጋለሁ። የአገሬን ያደኩበትን ጨዋታ ጨዋታውን ገራገሩን ላጫውታት እፈልጋለሁ። ጨርሶ አይጥማትም። በንቀት አይሉት በመገረም ትኩር ብላ ስታየኝ ትቆይና ደጋግማ ታዛጋለች። ካዛጋት በቃ ደብሯታል ማለት ነው። እርሷ ደግሞ አሜሪካ ስለገቡት ጓደኞቿ፣ አቴንስ ስላለው የድሮ ቦይ ፍሬንዷ፣ ጣሊያን ስለምትኖረው እህቷ የተደላደለ ኑሮ፣ . . . ስለአዲስ ቀሚስ ስለአዲስ ጫማ፣ ስለአዲስ ፋሽን፣ የጓደኛዋ ቦይፍሬንድ ስለገዛት አዲስ መኪና፣ ስለፓስፖርት፣ ስለ ቪዛ ስታወራልኝ ብትውል አይሰለቻትም። ስታወራ ብትውል አትጨርሰውም። እኔ ደግሞ ያመኛል። እርሷ ላወራችው እኔን ይደከመኛል። ከምታወራልኝ ዝባዝንኬ ይልቅ ስታወራልኝ የምታሳየኝ ቄንጥ ይጥመኛል። . . . ስስ ከንፈሮቿን ታሞጠሙጥና ቅንድቧን ከፍ ዝቅ እያደረገች ተከፍቶ የተረሣ ሬዲዮ ያህል ነው የምታወራው። እጆቿን እያወናጨፈች እነዚያን ሎጋ ጣቶችዋን ከቃላት ይበልጥ ታናግራቸዋለች። ስታወራ ቅብጥብጥ ያደርጋታል፣ ያቁነጠንጣታል። ያዳመጥኳት መስዬ ልብ ብዬ ሁለ መናዋን ማጤን እጀምራለሁ።

ቁንጅናዋ ፍንትው ብሎ ይታየኝ ይጀምራል። በእውነት ውብ ናት። በሁሉ ነገሯ ቄንጠኛ ናት። አነጋገሯ፣ አቀማመጧ በቄንጥ ነው። የአነጋገር ለዛዋ እንቅስቃሴዋ ስልት አለው። . . . የወሲብ ስልት፣ የወሲብ ቃና . . . በእውነት ወሲበኛ ናት። ለዚያች አፍታ የሁለመናዋ ውበት ፍንትው ብሎ ይታየኝና ፀጥ ያለው ወንድነቴ ተግ ይላል። እንደደነበረ ኮርማ ወይፈን አፋችራለሁ። አይኔም እያማተረ ደርሶ በተነባበሩ እግሮቿ ጋ ሲደርስ የተገለበ ጭኗ አውሬ ያደርገኛል። ልብ ያላለች መስላ በቄንጥ ማውራቷን ትቀጥላለች። አንዱንም አልሰማትም። ምራቄን ግርግጭ ሳደርግ ጉሮሮዬ እንዳሳጣኝ አውቀዋላሁ። "ጀመረህ እንግዲህ" ትላለች በመሽኮርመም ዓይነት። በወሲብ ቅላጼ! "የምታወሪልኝን አንዱን አልሰማሁም" እላታለሁኝ። እየተሻሸን፣ እየተቃቀፍን፣ እየተሳሳምን ተያይዘን ወደ ሌላ ዓለም እንንጉዳለን። ከትንሽ አፍታ በፊት ስለማይጥመኝ ዝባዝንኬ ይቀባጥሩ የተብሩት ከንፈሮቿ ሌላ ፋታ የማይሰጥ ስራ ይጀምራሉ። በቄንጥ ይወናጨፉ የነበሩት እጆቿ አመልጥበት ያለኝ ይመስል ጠፍንገው ይይዙኛል። አንበሳ እጅ እንደ ወደቀች ድኩላ እንጋልላታለሁ። ዳሩ እኔስ አንበሳ አይደለሁ። መላ አካሏ በሌላ ስልት በሌላ ቅላጼ መወዛወዝ ይጀምራል። ትንሽ እንደመቁነጥነጥ ያደርጋትና ስልምልም ብላ የተወጋች ያህል እያቃሰተች ወደ ሌላ ዓለም ትሰጥማለች።

(ወደ ገጽ 27 ይዞራል)

# የዴብራ ጦስ

(በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ልብወለድ)

ከገረሱ
ካለፈው የቀጠለ
ክፍል ዘጠኝ

ፈጠነ የዴብራ ጓደኛ ሲንቲያን እሱ እንደገመታት ሆኖ አላገኛትም። እሱ እሷ ትሆናለች ብሎ የፈራው ነገር እሷ እሱ ትሆናለች ብሎ የፈራው ነገር እሷ እሱ እንደዚያ ይሆናል ብላ በፍርሃትና በጥርጣሬ መጠየቋከጠበቀው ውጪ ነበር። የዴብራን ሁኔታ እሱም እንዳየው ሆነ ካሣሁን እንደነገረው በደምብ ያውቅ ስለነበር በዴብራ ላይ ያለው ሁኔታ ማለትም ባህርይና ድርጊት በሲንቲያም እንዲሁም በሌሎች ጥቁር አሜሪካን ሴቶች ላይ የሚንጸባረቅ ሁለንተናዊ (universal) ባህርይ አድርጎ ነበር የሚረዳው። ሲንቲያ ግን ፍፁም ሌላ ልጅ ሆነችበት። እንደዴብራ ጮሃ አታወራም፤ አትንቀዠቀዥም። ረጋ ያለች አስተዋይና ርቆ አሳቢ ሆነችበት። ምናልባትም በውበቷ ተማርኮ ሌላውን ባህርይዋንና ድርጊቷን የሚያይበት ዓይነ ህሊናው ታውሮበት ይሆን? ራሱን መልሶ መላልሶ የጠየቀው ጥያቄ ነበር። የተረዳው ግን ያው ጨዋናቷንና ረጋ ባይነቷን ብቻ ነበር። ሲንቲያም ሲንቲያ ናት፤ ዴብራም ዴብራ ናት፤ ሁለት የተለያየ ባህርይ ያላቸው ሴቶች። የአንድን ሰው ባህርይና ድርጊት ያ ሰው የመጣበት ዘር ወይም ጎሳ ወይም ህብረተሰብ ክፍል አጠቃላይ ባህርይ አድርጎ መውሰድ ለካ ስህተት ነው? ጥላቻም ወይም prejudice ለካ መነሻው ይህ ነው? ቀደም ሲል በሚኖርበት አካባቢ በተደረገ አንድ ስብሰባ ላይ ይህን በተመለከተ የተነሳው ክርክር ትዝ አለው። አማራዎች እንዲህ ናቸው፣ ትግሬዎች እንዲህ ናቸው ወዘተ እየባለ በተለምዶ የሚነገረው አባባል የprejudice አዝማሚያ ነው የሚል ከባድ ክርክር የተነሳበት ስብስባ ነበር ለአፍታ በሃሳቡ የመጣበት። አንዳንድ ጥቁር አሜሪካኖች ላይ የሚያየውን እሱ ደስ የማይሉትን ባህርያት የሁሉም ጥቁር አሜሪካዊ ባህርይ አድርጎ ይወስድ የነበረውን ግምት እንዲሚረምር የሲንቲያ ሁኔታ አጋጣሚ ፈጠረለት። ለካ እንዲህ ማሳብ ፍርደ ገምድልነት ነው ብሎም አሰበ። ለማንኛውም ግን ቸኩሎ ውሳኔ ላይ ከመድረስ ተቆጥቦ ከሲንቲያ ጋር ባለው ግንኙነት ሁኔታውን ለማጥናት ወሰነ። ጓዷኛው ካሣሁን ከዴብራ አገኘሁ የሚለውን ወሲባዊ ደስታ እሱም ከሲንቲያ አገኛለሁ፤ ለጊዜው ማንም አበሻ ሳያይ እደሰትባታለሁ ብሎ አስቦ የነበረውንም ሃሳብ ለጊዜው ገሸሽ አደረገ። ገሸሽ ባያደርግም ሲንትያ ዕድሉን አልሰጠችውም። ትዕግሥት እንዲያደርግ አስጠንቅቃዋለች።

ከሲንትያ ጋር የፈጠረው ግንኙነት እየጠነከረ ከዕለት ዕለት ብዙ ነገር እያስተማረው መጣ። ሲንቲያ ፈጥነን ለሁሉ ነገር እንዳይቸኩል መምከርና ብዙውን የራሷን ባህል እንዲረዳና እንዲያውቀው ማድረግን ሥራዋ አድርጋ ያዘችው። እንደ ዴብራ ይዛው በየመጠጥ ቤቱ አልዞረችም። በየሙዚየሙ፤ በየትርዒቱ ቦታ፤—ታዋቂ የባህል ተጫዋቾች ትርዒት በሚ ያሳዩበት ቦታ ይዛው ትዞራለች። እንዳ ንዴም የጥንቱን የጥቁር አሜሪካኖች አኗኗር፣ የባርነት ጊዜ ሥቃያቸውን ወዘተ የሚያሳዩ □ዲዎችን እቤቷ ታመጣና ፒዛ አዝዘው ቅዳሜና እሁድ ቤት ታውለው ነበር። ይህ ሁሉ ሲሆን ፈጠነን ሁሌ የሚገርመው ነገር ነበር። ራሱን ይጠይቃል። "ካምስት ጊዜ በላይ አብረን ውለናል፤ ለምንድነው ወደ አልጋ የማትጋብዘኝ?" እሱም ቢሆን ለምን ገፋ አድርጎ እንዳልጠየቀ ይገርመዋል አንዳንዴ ሲያስበው። ከአበሻ ሴት ጋር መውጣት ሲጀምር በመጀመሪያው ግንኙነት (date) ካልሆነም በሚቀጥልው በጣም መግድርደር ካበዛች በሶስተኛው ግኑኝነት ሰገነት ላይ መስፈር አለበት። እንደዚያ ካላደረገ ሴቷም የምትታዘበው ነው የሚመስልው። አንድ ወቅት አንዷን አበሻ ይተዋወቅና ራት ከበሉና ትንሽ ዞር ዞር ካሉ በኋላ ቤቷ ሊያደርሳት አድራሻውን ሲጠይቃት "ምነው ቤትህ ሌላ ሴት አለች እንዴ?" ብትለው ይዟት እቤቱ ወስዷታል። የተዋወቁ የመጀመሪያው ቀን ሁሉን ነገር ፈጽሟል። በሷው ግፊት ማለት ነው። እና ታዲያ "ተግዳርዳሪ የሚባሉት የአበሻ ሴቶች እንዲህ ቀልጣፋ ከሆኑ እቺ እዚህ ሥልጣኔ ከፍተኛ ደረጃ ደርሷል የሚባለው ቦታ ያለችው ሴት ምን ነካት? የለም ከኔ ከርፋፋ መሆን የተነሳ ሳይሆን አይቀርም፤" ይልና "ዛሬ ቀልጠፍ ብዬ መጠየቅ አለብኝ፤" ብሎ አቅዶ ሄዶ ሲያገኛት ፈርቶ ይተወዋል። በግንኙነታቸው ዕለት አቅዳ የምትምጣው ነገር ጭራሽ ስለሱ ማንሳት ቀርቶ እንዳያስብ የሚያደርገው ይሆናል። እስቲ ተያይዞ ሙዚየም ሲኬድ እንዴት ስለ ወሲብ ይወራል? ነውር ነው። ፈጠነ የነበረው ምርጫ ከእሷ ጋር ውሎ ሰውነቱና ወሲባዊ ስሜቱ ግሎ ሲለያት ወደ ሰናይት መሮጥ። ሰናይት ጋ መግደርደር የለም። ደግሞ ፈጠነን ታውቀዋለች፤ ቀልድ አያውቅም። ያላትን ወዲያው እሺ ካላለች ይዘጋታል። ከዘጋት ደግሞ dump አደረጋት ተብሎ አበሻ ጋ ቢወራስ?

ቀኑ ቅዳሜ ነበር። አንድ ቀን። ያለፈው ዓርብ ማታ ከነካሣሁን ጋር አመሻሽቶ ስለነበር ጠዋት አልጋው ላይ እንዳለ ወደ 9:00 ገደማ ስልክ ይደወላል። ሲንቲያ ነበረች።

"ተኝተሃል የኔ ማር ወለላ?" ትለዋለች።

"አዎን " ይላታል።

"ማታ አመሸህ እንዴ?" ትጠይቀዋለች።

አመሽሁ ቢላት የት አባክ አመሽህ ትለኛለች ብሎ ሲፈራ ሲቸር የፈለገው ይምጣ በማለት "እዎ ጥቂት" አላት።
"ተደሰትክ?" እንደገና ጠየቀችው።
"yes" አላት።
. "I am happy for you my sweet heart." አለችው። ከልቧ እንደሆነ ሁኔታዋ ያስታውቃል።
ገረመው። ያላጋጠመው ነገር። ትጮህብኛለች ብሎ ፈርቶ ነበር። አንዲት የውጪ ሴት መጣች ቀረች? በማለት ነበር የሆነውን የተናገረው።
"እረፍ ትንሽ የኔ ወለላ፤ ትንሽ ቆዮቼ ደውልልሃለሁ፤" ብላ ሲንቲያ ስልኩን ስትዘጋ ሁኔታዋና አነጋገርዋ ያልጠበቀው ነገር ሆነበት። እሱ ይህን የት ያውቅና፤ የሚያውቀውና የለመደው ቁጣ፤ ዛቻና ኩርፊያ። አንድ ጊዜ ከሰናይት ጋር እሳትና ጭድ የሆኑበት ሁኔታ ትዝ አለው። እንዲህ ነበር።
ሰናይት ትደውላለች። ስልኩን ያነሳል። እንደምን አደርክ? የለም።
"ማታ እቤት ያን ያህል ስልክ ስደውል የት ነበርክ?" ትለዋለች ቱግ ብላ።
"ጓደኞቼ ጋ፤" ይላታል።
"ሌሊት ሌሊት እቤት የማያስገቡ ጓዲኞች ምን ዓይነቶች ይሆኑ?"
ሽሙጥ እንደሆነ ገብቶታል።
"ነገርኩሽኮ! ጓደኞቼ ጋር አብረን አመሸን ጨዋታ ይዘን፤ ወደ 12 ሰዓት ነው የገባሁት።" ይላታል።
"ጥሩ ነው! እስከ 12 ሰዓት ከሚያመሽ ሰው ጋር እንዴት serious መሆን እችላለሁ፤ እኔ መቀለጃህ አይደለሁም ቢገባህ! " ትለዋለች ድምጿ በእልህ እየተንቀጠቀጠ።
"ስሚ ሰናይት! አንቺ እደውላለሁ ወይ ጠብቅኝ አላልሽ ቀደም ብለሽ። በሃሳብሽ ያለውን ደግሞ ለማወቅ ጠንቋይ አልቀልብም። እና እቤት ተጎልቼ አንቺ ገና ለገና ትደውያለሽ ብዬ ደግሞ መጠበቅ ያስቸግረኛል። " ይላታል እሱም ተናዶ።
"ጠንቋይ አልቀልብ? ለኔ ነው እንዲህ ያለ መልስ የምትሰጠኝ። ባልደውልስ! ባልመጣስ! አንተ መዞር አለብህ ማለት ነው።" ትለዋለች። ቁጣዋ መለስ ያለ ይመስላል፤
"ነገርኩሽኮ ሰናይት! የትም አልሄድኩ፤ ጓዲኞቼ ጋ ነው። እኔስ ብሆን ብቻዬን ባዶ ቤት ቁጭ ብዬ አላሳዝንም፤ ለምን አታስቢም።" ለስለስ ያለበት ምክንያት ነበረው። ሊያባብላት ፈልጎ ነው ከቁጣው መለስ ያለው።
"እኔ ዕድሌ ነው። ለኔ አልነበረም እንዲህ ያለ መልስ የምትሰጠው። እንዴት ለምነህ እንዳገኘኸኝ ደግሞ አትረሳውም። አሁን በቃ! ደግሞ የፈለገህ ቦታ ብታመሽ እኔ ሰናይት እንደሆነ ግድ የለኝም፤ የምናደድ መስሎሃል፤"
እንባ እንደተናነቃት ገባው። የምትናገረው ነገር ከተያዘው ርዕስ ለቀቅ እያለ ሲሄድ ነገር ነገር እንዳላት ይገባዋል። ከመሬት ተነስቶ የሚያነጫንጫት ጉዳይ ምን እንደሆነ ተረድቶላታል፤ ስለሚያውቃት። መረጃ በሌለው ባልተጨበጠ ነገር መቅናት። ሴቶቻችን ከፍቅራቸው ለምን ቅናታቸው እንድሚቀድም ይገርመዋል። አንድ ወንድ ውጪ ሲያመሽ "ምን ችግር ገጥሞት ይሆን?" ብሎ ከማሰብ በአዕምሮአቸው የሚጉላላው "ይኼኔ ከአንዷ ጋር ነው!" የሚል ጥርጣሬ በብዙ ሴቶች እንደሚታይ ያገቡ ጓዲኞቹ የነገሩት ስለሆነ "ትርፉ ጭቅጭቅ ነው፤" በሚል ምንም ቁጣ ቢኖርበት መታገሱን መረጠ።
ሲንቲያ ግን አልጮኸችበትም። ጥርጣሬ አልገባችም። "ደስ የሚልህ ቦታ ነው ያመሸኸው? ተደሰትክ?" ነው ያለችው። ሌላ ጥርጣሬ ውስጥ መግባት ሃሳቧ ውስጥ የለም፤ ቢኖርም ዙሪያ ጥምጥም ሳይሆን ቀጥታ የምትጠይቀው። አልጋው ላይ ጋደም ብሎ ከገባበት ሃሳብ የሲንቲያ ስልክ ቀሰቀሰው።
"ትንሽ አረፍክ?" አለችው።
"አዎን!" አላት።
"ዛሬ የት ነው የምትውለው?" አለችው።
"እስካሁን ፕሮግራም አላወጣሁም። " አላት።
"አንድ የወጣ ቆንጆ ፊልም አለ፤ ልጋብዝህ ፈልጋለሁ። It is my treat." አለችው።
"አመሰግናለሁ።" አላት።
"አንተ ነህ የምትነዳው። 1:00 p.m. ላይ እቤቴ ጠብቅሃለሁ።" አለችውና ስልኩን ዘጋች።
"ልጋብዝህ እኔ፣" ማላቷም ያልጠበቀው ነገር ነበረ። እሱና ሌሎች አበሾች የሰሙትና የሚያውቁት ጥቁር አሜሪካን ሴቶች ገንዘብ ማጫረስ እንጂ እኔ እንዲህ ላድርግልህ አይሉም የሚባለውን ነው። ታዲያ ሲንቲያ ጥቁር አሜሪካን አይደለችም ማለት ነው?
ፈጠነ ቀድሞ በስህተት የወሰደውን ግምት የሲንቲያ ሁኔታ እንደገና እንዲያጤነው ገፋፋው። ቀድሞ ከጓደኛው ከካሣሁን ጋር ስለ ጥቁር አሜሪካን ሴቶች ያደርግ የነበረውን ክርክር እየቀነሰ መጣ።
የዚያን ዕለት በተቃጣሩበት ሰዓት ለመድረስ ልክ ወደ ቤቷ ሲሄድ እግረ መንገዱን አበባ ገዛ። እቤቷ ደርሶ ሲሰጣት አንቅ አድርጋ ሳመችው። ስማው አለቀቀችውም። እንደዚያ ቀን ስማው አታውቅም። ከዚህ በፊት ደግሞ እሱ ይህን ያህል ከተሳሳመ የሚያውቀው ወደ አልጋ ይዞ መሮጥን ነበር። እዩዩ አልጋ። ስማው ስማው ስትጥግብ መቀመጫ አሳይታው ተቀመጥ አለችው። በመሳም ኃይል የጋለውን ሰውነቱን እንደያዘ መቀመጫው ላይ ዘፍ አለ። መጣች ሲላት "በል መጣሁ፤ ፍሪጁን ከፍተህ የምትፈልገውን ውሰድ" ብላ ያመጣላትን ቀይ ጽጌረዳ አበባ ማስቀመጫ ውስጥ አድርጋ ወደ መኝታ ቤቷ ስትሄድ በዓይኗ ተከተላት። አካሄዷ በተለይ በለበሰችው አጭር ቀሚስ የተጋለጠውን ባቷን ሲያይ ስሜቱን የበለጠ ቀሰቀሰው። ተነስቶም ወደ ፍሪጅ እንዳይሄድ የጋለው ሰውነቱ ሊያወላክፈው

ሆነ። ተከትሏት መኝታ ቤት እንዳይገባ "ና!" አላለችውም። "አይ ምን አጣደፈኝ፣ ተዘጋጅታ ልትመጣ ነው፤ እንግዲህ ዛሬ መሆኑ መሰለኝ፣ ወይ ትጠራኛለች፣ ወይ እዚሁ ይሆናል፤" እያለ ሲያስብ ቦርሳዋን አንጥልጥላ መጣች።

"በል ተነስ እንሂድ ሰዓቱ ደርሷል፤" ብላ ወደ መውጫው በር ስትሄድ እጢው ዱብ አለ። በጋለ ስሜቱ ሳቢያ የዛለ ሰውነቱን ይዞ እየተደናበረ ተከተላት።

የፈጠነና የሲንቲያ ሁኔታ እየተካሄደ እያለ ካሣሁን በሰናይት አማካይነት የተዋወቃትን ራ ሄልጌጋ ባይነቷን በመጠኑ ቢወድላትም ሊቀጥራት እየፈለገ "ይህ ቀን አይመቸኝም! በዚህ ቀን አይሆንም!" እያለች ማስቸገሯን ግን አልወደደላትም። ይደውልና ትንሽ አነጋግሯት የመገናኘት ቀጠሮ ነገር ሲያነሳባት ምክንያት ስትሰጠው "ሁለተኛ አልደውልላትም" ብሎ ይወስንና ከጥቂት ቀናት በኋላ እልህ ይገባና እንደገና ይሞክራል።

ካሣሁን አንድ አራት ጊዜ እንዲህ ከሞከረ በኋላ "ዛሬ የመጨረሻ ነው፣ ምን አለማመጠኝ፣" ብሎ ለአምስተኛ ጊዜ አንድ ቀን ሲደውልላት ትንሽ ለወጥ ብላ አገኛት።

"ምነው ሰሞኑን ሳትደውል? እኔማ አገር ለቀህ የሄድክ መስሎኝ ነበር፤" አለችው።

ያላሰበው አነጋገር ነበር። "እሱስ እዚሁ ነኝ። ብደውል ምን ያደርጋል ብዬ ነው?" ይላታል።

"እንዴት ምን ያደርጋል ስትል?" አለችው። አነጋገሯ ከወትሮው ቀልጠፍ አለበት። ያ ረጋ ባይነቷ እንዳለ ሆኖ እንዲህ በመጠኑ ቀልጠፍ ያለ አነጋገር ስታክልበት ደስ እንደምትል ተሰማው። ጭራሽ መዘጋትም ጥሩ አይደለም። በጣም መንቀልቀልም በአበሻ ሴቶች አያምርም የሚል አመለካከት ስለነበረው።

"እአይ ማለቴ አንቺ እንደሆን የማትበይ ወፍ ሆንሺብኝ፤" አላት።

ሳቀች።

"ምነው አሳቀሽ ከምሬ ነው?" አላት።

"አበላሉን አጥተህበት እንደሆን እንጂ እኔስ በሥርዓቱ ለመበላት የተዘጋጀሁ ነበርኩ።" አለችው።

አባባሏ ገረመው። እሷ እንደዚህ ትናገራለች የሚል ግምት አልነበረውም።

"ምናልባት ገበታው ላይ በቅጡ መቀመጥ አልቻልሽ እንደሆነሳ?" አላት እሱም ቀልድ ጣል ለማድረግ ብሎ።

"እኔስ ገበታው ላይ በቅጡ ቀርቤ ይሆናል። ምናልባት አንተ ከፈለግኸው ገበታ ላይ ላይሆን ይችላል የቀረብኩት።" አለችና ትንሽ ደስ የምትል ሳቅ አሰማች። ሳቋ ሙዚቃ መሰለው። ደስ የሚል ሙዚቃ። ምስጢሩ ትንሽ ግልጽ አልሆን ቢለውም እጁን ሊሰጥ አልፈለገም። ምስጢሩን አለመረዳቱን ደግሞ መግለጽ አላዋቂነቱን ማለትም "አራዳ" አለመሆኑንና "ፋራ" መሆኑን የሚያጋልጥበት መሰለው። አበሻ ሴት ጋ ደግሞ "አራዳ" መሆን ያስፈልጋል፤ በሱ ግምት።

"ገበታው ላይ መቅረብሽ አልታይ ብሎኛል። እኔማ ላቀርብሽ ስፈልግ ምክንያትሽ በዛብኝ።" አላት።

"ስማ ካሣሁን፤ አየህ እዚህ ላይ ነው እንግዲህ አለመግባባታችን የሚታየው። አንተ ገበታ እያልክ የምታወራው እኔ ቀርቤአለሁ ብዬ ከማወራው ገበታ ጋር አንድ አልመሰለኝም። ያንተ ገበታ ሌላ፣ የኔ ሌላ፤ የኔው አልታይ እንዳለህ ስለትረዳሁ ነው እስካሁን ቀጠሮ ያበዛሁብህ።" አለችው።

አሁን ግራ ገባው። "የእኔ ገበታ ካንቺ የሚለይበት ሁኔታ አልገባኝም፤" አላት።

"ካሣሁን ቀደም ሲል ከነበረኝ ቦይ ፍሬንዴ ለምን እንደተለየሁ ታውቃለህ? ልንገርህ። ይህ ምናልባት በብዙ የአበሻ ወንዶች ያለ ሁኔታ ስለሆነ ምናልባትም ያንተም ሊሆን ይችላል። እንዲህ ስልህ ደግሞ እንደማትቀየም ተስፋ አደርጋለሁ። ከአንድ ሴት ጋር የሚኖራችሁን ግኑኝነት ሁሌ የምታዩት በወሲብ ግኑኝነት አኳያ ብቻ ነው። ማለቴም ሴቷ የተፈጠረችው ለወሲብ ርካታ ዕቃነት ብቻ አድርጋችሁ ነው የምትወስዱት። ከወሲብ ሌላ፤ ሌላ ዓለም ያለ አይመስላችሁም። ሮጣችሁ እዚያ ላይ ነው። ስለዚህም ነው ከዓመሏና ከአስተሳሰቧ ጥሩነት ይልቅ የመቀመጫዋንና የዳሌዋን ማማር ስታደንቁ የምትገኙት። እዚህ ላይ እንዳትሳሳትብኝ፤ እኔ ወሲባዊ ስሜትን ለማንኳሰስ አይደለም ይህን የምለው። ግን አንድ ወንድ ገና ሲያገኘኝ እኔን ወደ አልጋው ሊያንደረድረኝ ከቸኮለ የሚፈልገውን ነገር ካገኘ በኋላም እኔን ለመዝጋት በእዚህ አገር አባባል dump ለማድረግም የሚቸኩል መስሎ ነው የሚታየኝ። ሌላም ሌላም ብዙ ስህተቶች አይባችሁዋላሁ።

ካሣሁን በመገረም አፉን ከፍቶ ነበር የሚሰማት። ራሄል ሲተዋወቃት የዚህ ዓይነት የመጠቀ አመለካከት ይኖራታል የሚል ግምት አልነበረውም። እሱ የተረዳት ዝምተኛ በቃ ምንም የማታውቅ እና እንዳው እሺ ብትል አብሮ ለጥቂት ጊዜ ወጥቶ ለመተው ዓይነት ነበር። ይህ አነጋገሯ በጣም ከበደው።

"ምናልባት ሌሎች ወንዶች ላይ እንዲህ ያለ ባህርይ አይተሽ ይሆናል። በደፈናው ወንዱን ሁሉ እንዲህ ስትኮንኚ ልክ ይመስልሻል። እኔ ደግሞ ካሰብሽው ውጪ ሌላ ባህርይ ያለኝ ልሆን እችላለሁ።" አላት።

"ሰው እኮ የሚናገረው ከልምዱ ነው። እኔም የምናገረው ከገጠሙኝ ሁኔታዎች ተነስቼ ነው። እና ማ ይሙት አሁን አንተስ ብትሆን እንዲህ ያጣደፍከኝ ለምንድነው? አትደብቀኝ። አንተ ቅድም ገበታ ብለህ ያወራኸው እሱኑ ነው። ከዛም በፊት ደጋግመህ ልታገኘኝ ስልክ የምትደውለው ለዚያው ነው። እኔ ደግሞ ወደዚያ ከመሮጥ በፊት መግባባት መኖሩን፣ አብሬ ለተወሰነ ጊዜ እንኳን

ቢሆንም መዝለቅ መቻሌን ማረጋገጥ እፈልጋለሁ። ቀደም ስል ያደረግሁዋቸውን ስህተቶች መድገም አልፈልግም።

ካሣሁን ግራ ገባው። በእርግጥ ያለችው ነገር ሁሉ እውነትነት እንዳለው ህሊናው ያውቀዋል። እምኖ መቀበልን ግን አልፈለገም። ዝም ማለቱን አይታ እሷው ቀጠለች።

"የአበሻ ወንዶች ሌላ ያያሁባችሁን ነገሮች ልንገርህ። ወሲባዊ ስሜታችሁ የሚቀሰቀሰው መጠጥ ስትወስዱ ነው። ይህን እንዳትከደኝ። እንዳንካካድ ብዬሃለሁ። ብዙ ወንድሞች ስላሉኝ በቅርብ ካየሁት ሁኔታ ነው የምነግርህ። ቦይ ፍሬንዴ ነው ብዬ ቀን ስደውልለትና ላግኝህ ስለው አሁን አልችልም ይለኝና ማታ መሸት ብሎ ትንሽ ከቀማማሰ በኋላ ሃሳቡን ቀይሮ አሁን ልምጣ ሲለኝ ምን ትገምታለህ። እኔን የሚያስታውሰው ሲጠጣ ብቻ ነው ማለት ነው። እና ከእንግዲህ አብሬው ልወጣ የምፈልገው አበሻ ወንድ ካለ መጀመሪያ ይህ ባህርይ እንደሌለበት አረጋግጬ ነው።" አለችው። ንግግሯ ከምሬት የመነጨ መሆኑን ካሣሁን መረዳት አላቃተውም።

"አበሻ ወንድ ስትይ ሌሎቹን በምን አየሻቸው?" አላት ረጋ ብሎ።

"አመጣጥህ ምን ለማለት እንደፈለግህ ይገባኛል። አልደብቅህም። የውጪ ማለትም ያገሬ ሰው ያልሆነ አውጥቼ አይቻለሁ። ያከብሩሃል ቢያንስ፤ ይህን ስልህ ደግሞ ለዘላቂ ኑሮዬ ይበጁኛል የሚል እምነት ኖሮኝ አይምሰልህ። ከአገሬ ልጅ የሚበልጥብኝ የለም። አብሬ ተደሰትኩ የምለውን የውጪ ሰው፤ ሰው በመሆኑ አከብረዋለሁ፣ ስለሚያከብረኝ። ግን ያደግሁበት ባህርይ፤ ልምድና ባህል ደግሞ ስላለ እሱም ሆንኩ እኔ አብረን በምንሆንበት ጊዜ miss የምናደርግው ነገር ይኖራል። ያም ስለሆነ ምንም ያህል አብረን ብንደሰት ምቾት ያለው ደስታ ስላልሆነ የአገሬን ልጅ እፈቅዳለሁ፤ ታዲያ በሥርዓት መቼ ተገኝታችሁ።" አለችው።

ካሣሁን የራሄል አነጋገር መጠቅ እያለበት ሲሄድ ራሱን መለስ አድርጎ እንዲገመግም አደረገው። ብዙ ነገርም ታሰበው። እስከ ረዥም ጊዜ ድረስ የአበሻ ሴት ለማግኘት ያደረገው ጥረት ፊቱ ላይ ድቅን አለበት። የዚህ ዓይነት የበሰለ አስተሳሰብ ያላቸው አበሻ ሴቶች በዚህ የውጭ አገር አሉ የሚል ግምት ከአዕምሮው ጠፍቷል። እና ታዲያ ይህቺ የት ነበረች። ሲያያት እንዲያው ደስ ስለምትልና ደግሞ ብዙ ጊዜ እንደሚያያቸው አበሾች (pretentious) ስላልመሰለችው፤ እሺ ካለች አንድ ሁለቴ ብቻ አውጥቷት ሊዘጋት፤ በዚያውም ጓደኛውን ፈጠነን በአበሻ ሴቶች ጉዳይ ለአንዴም ለመጨረሻ ጊዜ ለመርታት ነበር ሊያወጣት ያቀደው። ያልጠበቀው ነገር ሆነበት።

"እና ታዲያ፤" አላት ጥቂት አሰብ አድርጎ፤ "እና እኔንም እንግዲህ የዚህ ዓይነቱ ሰው አለመሆኔን መጀመሪያ ማረጋገጥ ፈልገሽ ነዋ እንገናኝ ስልሽ ታሪክ የምታበዥው፤" አላት።

"እሱም ነው። ደግሞ ግልጽ አድርጌ ልንገርህና አንተ ሁሌ ደውለህ የምታናግረኝ በጣም ከመሸ በኋላ ነው ልብ ብለህ እንደሆን። ቅድም እንዳልኩህ አንድ ሁለቷን ኳ ካደረግህ በኋላ ብቻ ትዝ የምልህ ስለመሰለኝ ነው። አየህ በዚያ ሰዓት ምናልባት አልጋህ ላይ ሆነህ ይሆናል። እና የምለው ይገባሃል።" አለችው።

"አንቺ እንዳው ዝም ብለሽ ነው ባክሽ። እኔ በዚያ ሰዓት የምደውለው ሰዓቱ ስለሚመቸኝ ነው። በሥራ ቀን ቀርቶ በዕረፍቱም ቀን ለመጠጥ ይህን ያህል አይደለሁም። ደግሞ እንዳባባልሽ፤ የፈለግሁሽ ለወሲብ ብቻ እንደሆነ አድርገሽ መገመትሽ ተሳስተሻል። በሌላ በኩል ደግሞ ወሲብን ሙሉ በሙሉ የምትኮንኚ ይመስላል እንዳባባልሽ። በሁለት ተቃራኒ ጾታዎች መሀል ካሉት ግኑኝነቶች ሁሉ ትልቁን ቦታ ይዞ ያለ እሱ እንደሆነ መረዳቱ ቁምነገር መሰለኝ።" አላት።

"እንደዚያ አላሰብኩም፤ ወሲባዊ ግንኙነትንም አላንኳሰስኩም። የሚያናድደኝ ወንዶች ሴቶችን የሚፈልጓቸው ለዚያ ብቻ ሆኖ ሳገኛቸው ነው።" አለችው ራሄል።

"እዚህ ላይ ደግ!" አለ በሆዱ። ለራሄል ያለው ግምት እያደገ ሄደ። ይህችንም ልጅ የማግኘት ጉጉቱ ከፍ እያለ መጣ። . .

(በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል።)



ውብሸት ገሠሠ



መኩሪያ በቀለ

ከአዲስ አበባ ቤታቸው በ ፲፱፻፹፮ እንደወጡ የጠፉ

ያሉበት ባለመታወቁ ቤተሰቦቻቸው በትልቅ ጭንቅ ላይ ናቸው።

ስለነሱ የምታውቁ ለላንዳፍታ አስታውቁልን።

ቤተሰቦቻቸው


# ኑሮ በአሜሪካ

## በአዲስ ዓመት አዲስ ተስፋ እንስጣቸው

ይሄኔ አገራችን ብንሆን የእንቁጣጣሽ አበባ አምጥተውልን እኛም መርቀናቸው ሽልመን እንልካቸው ነበር። ያለነው ግን በባዕድ አገር ነው። ዛሬ በሽልማቱ ፋንታ አዲስ ተስፋ እንስጣቸው። አባትና እናት በቋንቋችን ስናወራ ዓይናቸውን እያቁለጨለጩ "What did you say Daddy? What did you say Mommy? እያሉ ስናያቸው ያሳዝኑናል።

በውጭ አገር ኑሮአችን ያፈራናቸውን ልጆቻችንን ኩሩ በሆነው ባህላችን ኮትኩተን ለማሳደግ እንድንችል የጋራ ችግራችንን የምንወያይባቸውና መፍት ሄምበጋራ ልናገኝ የምንችልባቸውን የኮሚኒቲ ማህበራትን ማጠናከር ይኖርብናል። እናትና አባት የሚያወሩት ቋንቋ ይናፍቃቸዋል፣አዲሱን ዓመት ስንቀበል እነኚህን ውድ ልጆቻችንን የቤተሰቦቻቸውን ቋንቋ የሚማሩበትን ሁኔታዎች በያለንበት እንድናመቻችና ትምህርት ቤቶች እንድንከፍት ጥሪ በማድረግ ይሆናል። ተባብረን የምናደርገው ሁሉ ውጤት ይኖረዋልና አትላንታ ከተማ የተጀመረው ዓይነት የህጻናት የቋንቋ ማዕከሎች ያብቡ እንላለን። በአዲስ ዓመት ይህን ተስፋ ለልጆቻችን እንስጣቸው።

እደጉ ተመንደጉ እንበላቸው!!



# ዜናዎች በፎቶ

## ባለፉት ሁለት ወራት

# አትላንታ

በተለያዩ ከተሞች የተከናወኑትን ዐበይት ተግባራት እንዲተዋወቅላችሁ የምትፈልጉ በዜና መልክ ማቅረብ እንድንችል በፎቶግራፍ የተደገፉ ድርጊቶቻችሁን አሳጥራችሁ በመጻፍ እንድትልኩልን በትህትና እንጠይቃለን። ጥያቄ ቢኖረን መልስ ለማግኘት እንድንችል የስልክ ቁጥራችሁንም ላኩልን።

## በአትላንታ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር

በአትላንታ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር የቦርድ ዲሬክተሮች የመጀመሪያውን ስብሰባ በማድረግ ሹማምንቶችን መርጠው 6 የተግባር ኮሚቴዎችን በማቋቋም ሥራቸውን ጀምረዋል። አዲሱን ዓመት መቀበያ ምሽትም ያዘጋጁ ሲሆን ዲኬተር ኮሊጅ ባዘጋጀው የኤትኒክ በዓል ላይ ተሳታፊ ሆነዋል። በዚሁ ዝግጅት ላይ የተለያዩ የኢትዮጵያ የባህል ዕቃዎች ለዕይታ (exibition) የቀረቡ ሲሆን የባህል ዘፈኖችና የመድረክ እስክስታ በበዓሉ ለተገኘው ህዝብ ቀርበው ተደናቂነትን አትርፈዋል።

♦♦♦♦



በአትላንታ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር የቦርድ ዲሬክተሮች

## ፕሮፌሰር እስፔንሰር በአትላንታ

የኢትዮጵያ ጽኑ ወዳጅ ተብለው የሚታወቁት ፕሮፌሰር እስፔንሰር አትላንታ ከተማ በመገኘት ለኢትዮጵያውያን መግለጫ ሰጡ። በዚሁ መግለጫቸው አሜሪካ በኢትዮጵያ ላይ የነበራትን የጥንት ፖሊሲ ከአሁኑ ጋር በማገናዘብ ታሪካዊ መረጃዎችን በመጥቀስ በአሁኑ ወቅት ባለው የአገሪቷ ችግር ኢትዮጵያውያን ምን ማድረግ እንዳለባቸው አብራርተዋል። ፕሮፌሰሩ አሁን ባለው የሽግግር መንግሥት መሪዎች ላይና የአሜሪካንን ፖሊስ በተመለከተ ሃላፊነት ባላቸው አሜሪካኖች ላይ ያላቸውን ምሬት አልድብቁም። ከፋሺስት ወረራ ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያን የሚያውቋትና የሚወዷት እስፔንሰር በንግግራቸው መጨረሻ ለቀረበላቸው ጥያቄዎች መልስ ሰጥተዋል። ይህንን ትምህርታዊ ጉባኤ ያዘጋጀው የኢትዮጵያ መድህን ፓርቲ የአትላንታው ድጋፍ ኮሚቴ ነው። የመድህን ፓርቲ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባል አቶ መሀሪ በላይ በዚሁ ስብሰባ ላይ መግለጫ ሰጥተዋል። ስብሰባውን የመሩት ዶክተር ሥዩም ገላዬ ነበሩ።

♦♦♦♦



አቶ መሀሪ በላይ ዶክተር ሥዩም ገላዬና ፕሮፌሰር እስፔንሰር

## በአትላንታ የመአህድ ድጋፍ ኮሚቴ ዓመታዊ ስብሰባ አደረገ

አትላንታ የሚገኘው የመላው አማራ ህዝብ ድርጅት ድጋፍ ኮሚቴ ዓመታዊ ስብሰባውን በማድረግ መግለጫዎችን ጥሪ ለተደረገላቸው እንግዶች አሰምቷል። በዚሁ ስብሰባ ላይ ዶክተር ጋሻው ወ ላቀው ከ መግለጫቸው በኋላ ጥልቀት ያላቸውን ግጥሞቻቸው አሰምተዋል። እንዲሁም ዶክተር ጌታቸው በላይነህ የድጋፍ ኮሚቴውን እንቅስቃሴ በተመለከተ መግለጫ ሰጥተዋል።

♦♦♦♦



ዶክተር ጋሻው ወ ላቀውና ዶክተር ጌታቸው በላይነህ

# የላጤው . . .

(ከገጽ 20 የዞረ)

(ከገጽ 20 የዞረ)

እኔ አብሬያት አልሰጠምኩም። . . . ሌላ ቅላጼ . . . ሌላ ስልት! የማለክለክ ያህል የሚወጣው ትንፋሿ እንደእንፋሎት ይጋረፋል። ከትንሽ ቋይታ በኋላ እንዴ በሃይል ታቃስትና ተወራጭታ ፀጥ ዕረጭ ትላለች። በላብ ተነክራ ድምጿም ትንፋሿም ጥፍት ይላል። ጨርሳ መስጠሟ ይታወቀኛል። ዝርግትጉት ያለች ድል የተመታች ትንሽዬ ፍጡር!

· ከሰመጠችበት ዓለም ስትመለስ ተረበኛ ምላሷ ስራውን ይጀምራል።

"ፈረስ ነህ ፈረስ! . . . የሰው ፈረስ" ትለኛለች።

"ጋማዬን ይዘሽ ሌጣዬን እየጋለብሽኝ ምን ታደርጊ" እላታለሁ። ነገሯን ወደ ቀልድ ለመለወጥ ፈልጌ። እርሷ ግን የምሯን እያጉተመተመች የስድብ ውርጅብኝ ታወርድብኛለች። አንዳንዴ ጆሮ ግንዷን በጥፊ ላግላት አስብና መልሼ እታገሳለሁ። ለሁለት ዓመት ለሚሆን ጊዜ በዚህ ሁኔታ አብረን ቆየን። በመጨረሻ ልንለያይ የቻልነውም እንደመገናኛታችን ሁሉ አንድ ፓርቲ ላይ እርሷው ጎትጉታ ይዛኝ ሂዳ ልትጎልተኝ ፈለገች። ከአንድ ልጅ እግር ሰው ጋር ደጋግማ እየተነሳች ትደንሳለች። እርሱም ምን መስዬው እንደሆን አላውቅም እየተመላለሰ መጥቶ እያስፈቀደኝ ይዟት ይነሳል። አጅሪት እኔ ሂጂም ቅሪም ሳልል ቅልጥፍ ብላ ትነሳና አብራው ትውረገረጋለች። ቅናት ቢጤ ውስጤን አቃጠለው። ከመጠጡ ደጋግሜ ተጎነጨሁ። ለብ አለኝ። ወንድነት ወንድነት ተሰማኝ። ትንሽ ቆይቼ ሙዚቃው ሲጀምር

"ተነሽ እንደንስ" አልኳት

"ደክሞኛል!" አለች እንደመቆናጠር እያደረጋት። አበድኩ፣ ነገር ነገር ሸተተኝ።

"ከእኔ ጋር ሲሆን ነው የሚደክምሽ . . . በይ ተነሽ" አልኳትና እጇን ይዤ ጉትት አደረግኋት። በመካከሉም ጠረጴዛችን ተገለበጠና በላዩ ላይ የነበረው መጠጥ ተደፋ። በጣም በሸቀች። ጦፈች። እኔም ለየልኝ፣ አበድኩ። ያዙኝ ልቀቁኝ አልኩ። ስካርም ጀማምሮኝ ስለነበር ለገላጋይ አስቸገርኩ። ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል ሆነና በሞቅታ መንፈስ የስድብ ውርጅብኝ አወረድኩባት። ካልገደልኩ ብዬ ተጋበዝኩ።

"ወይኔ አለሜ . . . ይህቺ መናጢ የመናጢ ልጅ እንዴት ብትንቀኝ ነው" ብዬ ፎከርኩባት ለያዥ ለገላጋይ አስቸገርኩ። ከጫጫታውም ከንዴቱም ከስካሩም ጋር ተደማመረና ፀብ አሰኘኝ።

ወንድነቴ ከልክ አለፈ። ያን ከጎኔ እየመዘዛት አብሯት ሲደንስ የነበረውንም ውርጋጥ እንደ ቅሪላ በረገጥኩት ፈቃዴ ነበር።

"አንቺ መናጢ . . . ምኔ ይታፈርብኛል እባክሽ? እኔ አለምነህ ካብትህይመር ከኋላ ቢያስከትሉኝ፣ ከፊት ቢያስቅድሙኝ አይታፈርብኝም።" እያልኩ በጠጣ አንጀቴ አንቧረኩባት። ገላጋይ ገባና እርሷንም ዞር አደረጓት፣ እኔንም አስገብተው አስተኙኝ። ያ እስሬ እያስነሳ ያስደንሳት የነበረው ውርጋጥ በግርግሩ መሃል ሳይጠቀልላትም አይቀር። ብቻ እኔና እርሷ ተገናኝተን አናውቅም በነጋታው የሆነውን ሁሉ ሲነግሩኝ እኔም አፈርኩ። እርሷም አፈረች።

ይቅር ብለው ካልተዉት በወንደላጤ ሕይወት ብዙ ጉዳጉድ አለ። ያ ሁሉ አልፎ ዛሬ ባለትዳር ነኝ። የላጤነትን ዘመን ቢያረዝሙት ቁምነገር የሌለው ዝባዝንኬ ትዝታ ማብዛት ነው እያልኩ ጠና ጠና ያሉትን ወንደላጤ አብሮ አደጎቼን እመክራለሁ። ሀብት ቢሰበስቡት ገንዘብ ቢያከማቹት በአንድ ጆንበር ጠፊ ነውና ቢጤህን ፈልገህ መሳይህን ተካ እያልኩ ገንተር ያሉ ወንደላጤ ወዳጆቼን እዘክራለሁ። በ50 ዓመት መዳረሻዬ መሞሸሬ እየገረመኝ እኔን ያየህ ተቀጣ እላለሁ። የጉልምስና ወዘናን በማነህ ማነህ አሟጦ አብራ የምታረጅን ማግኘት ኋላ ሊቸግር ይችላል ባይ ነኝ። የሚሰማኝ ባገኝ የበኩሌን ብያለሁ።



# ላንዳፍታን በሞቅታ!

ከጣጤው (አትላንታ)

ጠጪ እንኳ አይደለሁም። ያው እንደተለመደው ሁለት ሶስቱን ኳ አደርጋለሁ። (እኔ ልሙት ከዚያ በላይ አልችልም፤) በሞቅታ የሚወነጨፍ አዕምሮን ይዞ ከወረቀትና ከብዕር ጋር መቀመጥን የመሰለ ጸጋ አጋጥሞኝ ቁጭ! ሆሆ!

እና እንዴት ናችሁ ላንዳፍቶች? መቼም ድዳም ፎከታም መባሌን ሳትሰሙ የቀራችሁ አይምስልኝም። "ውነትም ጣጤው" በሚል ጽሁፍ አቶ ሀይሉ ሮበሌ ተችተውኛል። ትችት አልኩት እብጂ ጽሁፋቸው "ፉተታ" ነበረች። "ጣጤውን ለመዝለፍ ሳይሆን . . ." ብለው ጀመሩና "ቅሌታም ድንክዬ . . ከየት የመጡ ጉድ ነዎት?" ብለውኝ እርፍ! ወቸ ጉድ!

አቶ ሀይሉ "ላንዳፍታን በሞቅታ"ን እንደ ህጋዊ ጽሁፍ ቆጥረዋት ካበቁ በኋላ ህገወጥ ካልሆንኩ ሞቼ እገኛለሁ በማለት አንዴ ቁመቴን፣ አንዴ ጭንቅላቴን፤ አንዴ አንገቴን እየጎነተሉ ትን አስብለውኛል። አፌ ቁርጥ ይበልላቸውና "ሥማርትዬ"ም ብለውኛል።አንድ ቢራ እንኳ ሳልገዛለት እንዲህ የሚምነሽነሽ ጎበዝ ሲያጋጥመኝ የመጀመሪያዬ መሆኑ ነው። ይኼ ሁሉ አልበቃ ብሎ ". . .የሚመኙት ነገር ቢቀርብዎ ይሻላል፤" በማለትም ማስጠንቀቂያ ሰጥተውኛል። እኔም እንዲህ "በመዋረዴ" ምክንያት የደም ብዛቴ ጨምሮ፤ ዓይኔ ተጠናግሮ፤ ናላዬም ስለዞረ የቁም ቅዠት ጀምሮኛል። አልደብቃችሁምና ጽሁፋቸውን ባየኋት ቁጥር አቶ ሃይሉን በካልቾ እየጠለዝኩ ቁልቁለቱን ሳንደረድራቸውም ታይቶኛል። "ንዴት" ተወጥቻለሁ።" ከዛ በተረፈ አቶ ሃይሉ አያ ድብልብሌ ሆነውብኛል።

ከጊዮርጊስ በታች ከሠራተኛ ሰፈር ባሻገር በሚገኘው የገብረ ትንሣይ ኬክ ቤት መሽሞንሞናቸውን የጠቆሙኝ አቶ ሃይሉ ዘንድሮ እዚህ ፈረንጅ አገር ሆነው ግብረ ገብ አስተማሪ ለመሆን የሚያስቡ ሰው ይመስላሉ– ግን ሰውዬው ብዙ ነገሮችን ይትርዱ አይመስሉም። በተለይ የጽሁፌን ዋና መንፈስ የተገነዘቡት ስላልመሰለኝ በፉተታ የተከናነበውን እንገታቸውን ገለጥለጥ በማድረግ እንደ ፍርድ ቤት ነገረኛ የተገተሩ ጅማቶቻቸውን ለማለስለስ እሞክራለሁ።

ውድ አቶ ሃይሉ! "ላንዳፍታን" በሞቅታ"ን ከማንበቦ በፊት አንድ ሁለት ቢራ ኳ ቢያደርጉ ጥሩ ይመስለኛል። "ትችትዎ" የኮስታራ ቄስ፤ የዕድር አለቃ ወይም የ"ጨዋ ነኝ" ባይ ትችት ስለመሰለኝ ነው ቢራ ያዘዝኩልዎ። ሁሉን ነገር አክርሮ የማየት ችሎታዎ የሚደነቅ ቢሆንም አንዳንዴ ቸል ማለትንም ቢለምዱ ጥሩ ነው። ይዝናኑ፤ ይፈንድቁ፤ አዕምሮዎም ይወንጨፍ። እልፍ እልፍም "ክረ ምናባቱ!" ማለትን ይልመዱ። አይፍሩ፤ ዓለም አትፈነዳም፤ ኢትዮጵያም አትጠፋም። ቀና ቀና ብለው ደረትዎንም ነፋ አድርገው ጉሮሮዎን "እእህህ" ብለው ጠርገው ከት ብሎ መሳቅንም ይጀምሩ። አለበለዚያ እንዲሁ በባዶ ሜዳ አንድ ጣጤ መጽሄት ላይ ሴት ቀጠረ ብለው ጨጓራ የሚገሸልጡ ሰው ከሆኑ ህይወት ጉድ ልታደርግዎ ነው። በመግቢያዬ ላይ እንዳስቀመጥኩት እኔ የማወራዎ ባንኮኒ ተደግፌ ቢራ ይገፔ መስሎኝ ነበር። እርሶ ደግሞ የሚተቹኝ ከቤቴ ባሻገር ካለው ቤተክርስትያን ግቢ ውስጥ ግድግዳውን እየተሳለሙ ይመስላል። መንገዱን ሻገር ብለው ይምጡና ቢራ እየጠጣን እናውጋ፤ አለበለዚያ እኔ ቢራ፣ እርሶ ጠበል ይዘው እንዴት ይሆናል በሞቴ?

"ውነትም ጣጤ" በምትለው ጽሁፎ አንዴ ግብረገብ አስተማሪ፣ ደስ ሲልዎ ከእፍ እፍ ኮሌጅ ተማሪ የበለጠ አሽሙረኛ፣ ሀይ ሲልብዎ "እውነተኛ ኢትዮጵያዊ" የሚል ሰርተፊኬት ሰጪ፣ በመጨረሻም እንባቢ ሁሉ "የአንድ ደቂቃ ጸሎት" እንዲያደርግ የስግደት ቄስ ትዕዛዝ ሰጪ ሆነውብኛል። መቼም ይህቺን ሲያነቡ "ይህ ሰው ጤናም አልያዘው?" እንደሚሉኝ አልጠራጠርም፣ ሳይካትሪስትነትም የሚከብድዎ አይመስለኝምና!

አቶ ሃይሉ የካይሮ ደርሶ መልስን ጉዳይ አንስተው እግረ መንገዳቸውንም "እየገደሉም እየሞቱም" ነው የሚል ፎርሙላም አዘውልኛል። መቼም በዚያች ጽሁፍ ያላሉት ጉዳይ ባለመኖሩ አቶ ሃይሉ ሮበሌ ከመባል ይልቅ አቶ "ምንተስኖት ዳምጤ" ቢባሉ ስምም ነበር። እና "እውነተኛ ኢትዮጵያውያን" ቢታሣሩ ይሻል ነበር ብለህ ለምን ጻፍክ በማለት ሲተቹኝ "ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው" ብለው ያባቶቻቸውን ተረት ተረቱብኝ እንጂ የኔ አባቶች "ህልም ተፈርቶ መኝታ አይቀር" ብለው ያስተማሩኝን ለማስገንዘብ ነበር ድካሜ።

ካይሮ እስካለን ድረስ እዛው ግብፅ ውስጥ ተደርጓል እየተባላ የሚነገርለት አንድ ታሪክ ላጫውትዎ፤ ሙሴ የእስራኤል ልጆችን ከግብፅ ያወጣቸው ቀይ ባህር ለሁለት ተከፍሎለት ነው ይባላል። ግራ የገባኝ ነገር ስላለ እርሶን ልጠይቅዎ። የእሥራኤል ልጆች በየት በየት አድርገው ነው መጀመሪያውኑ ግብፅ የገቡት? ከእርሶ የምጠብቀው መልስ ከሚከተሉት አንዱ መሆን አለበት።

1. ከግብፅ ሲወጡ ብቻ ሳይሆን ወደ ግብጽም ሲገቡም ቀይ ባህር ተከፍቶላቸው ነበር።
2. ወደ ግብፅ የገቡት በግራቸው ነበር
3. አንተ ጤናም አልያዘህ

እንግዲህ የሚገባዎ ከሆነ እኔ ጣጤዎ እንኳን የዘመኑ ፖለቲከኞችን ቀርቶ የቀይ ባህርን ለሁለት መክፈል የምጠይቅ ሰው ነኝ። አይዝዎ አይዘኑብኝ፤ ግፋ ቢል "ስብእት ለእብ" ብለው ይለፉኝ፤ እግረ መንገዶን ፍልስፍናዬን ለመገንዘብ ይሞክሩ፤ አልሆን ካልዎት ቢራ ፉት ይበሉበት።

ጨዋታ ላይ እስካለን ድረስ ሌላ ነገር ላጫውትዎ። እዚህ ፈረንጅ አገር ውስጥ ሬድ ኔክ (Red Neck) በመባል የሚታወቁ ፈረንጆች አሉ። እነዚህ "ቀይ አንገቶች" ያሜሪካንን ፖሊሲ የሚቃወም ሰው ባገኙ ቁጥር "Love it or Leave it" (ካልወደድከው ጥለኸው ሂድ) በማለት የሚደነፉ ሰዎች ናቸው። አሜሪካ ውስጥ የጃፓን መኪናዎች በብዛት ገዥ ስላገኙ መንገድ ላይ የቆሙት ቶዮታ ከብብ አድርገው በመዶሻ የቀጠቀጡ ጠባብ ብሄረተኞች ናቸው። ከዚህም በላይ ጥቁር ህዝብን የሚሳደቡና የሚጠሉም ዘረኞችም ናቸው። ልክ እንደእርሶ "የበላህበትን አትርገጥ okay" የሚሉ ናቸው። ታዲያ ይኸውልዎ ጓደኞቼ "ያባሻ ሬድ ኔክ" መኖራቸውን እንዴት እስካሁን አትውቅም ብለው ሲጠይቁኝ ቀልድ መስሎኝ በመሳቅ ተውኩት እንጂ እንዲህ እንደርሶ በአደባባይ የወጣ ያበሻ "ሬድ ኔክ" መኖሩን አላውቅም ነበር። ያባሻ ሬድ ኔክ ሲያጋጥመኝ የመጀመሪያው ነውና በሞቴ ትንሽ ያዳምጡኝ።

እዩ አቶ ሃይሉ! ፈረንጅ አገር ስለምኖር ፈረንጅን የመተቸት መብቴን የሚነጥቀኝ የለም። እርሶ በበሉበት ቦታ ሁሌ የሚያጎበድዱ ካልሆኑ በቀር የኔ ፈረንጅን መተቸት እንገትዎን ባላቀላው ነበር። "አቶ ጣጤው የኛ አገር ፖለቲከኞች ከፈረንጅ ቂጥ ስር አይውጡም ብለዋል፤ ኸረ እርሶስ ቢሆኑ የት ነው ያሉት?" በማለት አንቱ እያሉ ጠይቀውኛል። (በነገራችን ላይ አንቱ አንቱ ስንባባል ማን ከማ ለይቶ መጻፉ እየከበደ መጣ፤) እንግዲህ ልብ ብለው ያድምጡኝና ልመልስልዎ።

የምኖረው እዚሁ ፈረንጅ አገር ከርሶ ጋር ነው። ፈረንጆቹ የኢትዮጵያን ስም እያነሱ እንደፈለጉ የሚያወሩበት የሚጽፉበት አገር ነው። ሲከፋቸው አጥላልተው፣ደስ ሲላቸው አሞግሰው፤ አንዳንዴም ከነአንካቴው መፈጠርዋንም ረስተው "የት ነው ኢትዮጵያ" ብለው የሚያፌዙበት አገር ነው። ድፍን ፈረንጅ የሚጠቀምበትን የመናገርና የመጻፍ መብትእኔን ለምን ሊነፍጉኝ እንደፈለጉ ሊገባኝ አልቻለም። "የበሉበትን አይርገጡ" ማለትዎ በጣም አሳዝኖኛል። የጭሰኝነት መንፈስ አለብዎ ልብል? አይዝዎ አይፍሩ ፈረንጅን መተቸት ህገወጥነት አይደለም። ኃጥያትም እንዳይመስልዎ። ኢትዮጵያዊ ሁሉ ለአንድ ደቂቃ እንዲጸልይ እርሶ ትዕዛዝ የሰጡበት "እኩልነትና ዴሞክራሲ" ትንሽ እንኳ ቋቅ አይሎትምን?

ኢትዮጵያን ከድህነትና ከድንቁርና ለማላቀቅ ከተከፈተው የሃሳብ ገበያ ውስጥ እርሶን የመሰለ የፈረንጅ ቤተኛ አሁን ድረስ መኖሩ ገርሞኛል። ዳቦና ዱቄት እያጎረሱ መቀነትዎን ሲፈቱብዎ ያልነቁ መቼ ሊነቁ ይሆን? ወይስ የመንቃት ፍላጎቱ የሎትም?

ፈረንጆቹን ከተቸሁባቸው ነጥቦች ውስጥ አንዷን ብቻ መንጥቀው "ያገሬ ህዝብ በረሀብ ሲቆላ" የደረሱልን ፈረንጆች አይደሉም ወይ? ብለዋል አቶ ሃይሉ። የ"አልሰሜን ግባ በለው" ዓይነት ስለመሰለኝ ስለረሃብ ምንነት መጥቀስ አስፈላጊ መስሎኛል።

ረሀብ (Famine) እንዳው የወር ደመወዙን ጨርሶ ሌላ የደመወዝ ቀን በናፍቆት እንደሚጠብቅ የወንደላጤ ማድቤት የሚቀመስ ነገር ማጣት አይምሰልዎ። ረሀብ (Famine) የህዝቦች የተለምዶ ምግብ ምንጭ ቀስ በቀስ እየጠወለገ፣ ከካቻምናው ያምናው፣ ካምናው የዘንድሮው እህል ምርት እየቀነሰ በመሄድና በመጨረሻም ያለ የሌለ ንብረት ተሸጦና ተበልቶ ካለቀ በኋላ የምግብ ምንጫቸው ሙሉ በሙሉ ደርቆ ሲቀር ህዝቦች ምግብ ፍለጋ ቤታቸውን፣ ትውልድ አገራቸው ጥለው የሚሰደዱበት የረዥም ዘመን ሰው ሠራሽ የፖለቲካ ችግር እንጂ ሌላ እንዳይመስልዎ። በቴሌ□ዥን ላይ የምናያቸው ረሀብተኞች እዛ ደረጃ ሊደርሱ የበቁት በዙ ዘመን መጣጣርና መታገል በኋላ መሆኑን ቢገነዘቡት ጥሩ ነው። ስለዚህ የተራቡ ህዝቦችን መርዳት ቅዱስ ሥራ መሆኑን አልክድም። አባባ ጃንሆይም ገንዘብና ዳቦ በየመንገዱ ያድሉ እንደነበር አውቃለሁ። ፈረንጆችም የሚያደርጉት ይህንኑ ይመስለኛል። ይኼን ይኼን ቆጥረው ይሆን የደረሱልን ፈረንጆች ናቸው የሚሉኝ? ዓላማዎ ረሀብን ከኢትዮጵያ ጭራሽ ለማጥፋት ከሆነ ከዚህ ዓይነት አስተሳሰብ በላይ መመንጠቅ ይኖርቦታል። ለመሆኑ ዘንድሮስ? ባገራችን ረሀብ እንደገና መግባቱን ያውቃሉ? እንግዲህ (እንደርሶ አባባል ከሆነ) በየአራት/አምስት ዓመቱ የፈረንጅ ምፅዋት መጠበቅ ሊኖርብን ነው። ወይስ የረሀብን ምንጭ አውቀን ላንዴና ለሁሌ ልናጠፋው እንጥራለን? ምርጫው የርሶ ይሁን!

እንግዲህ የጽሁፌን መንፈስ ሳይርዱት የቀሩ አይመስለኝም። ቢራ ተይዞ ባንኮኒ ተደግፎ የሚካሄደውን ዓይነት እሰጥ አገባ መሆኑንም ይረዱት። ከዚህ በተረፈ "ሽማግሌ ዋሽቶም ያስታርቃል፤" የሚባለውን ትርት እውነት መስሎዎት መተረትዎ ገርሞኛል። እኔ የማውቀው "ሽማግሌ ተቆጥቶ ያስታርቃል፤" የሚለውን ነው። ያኛው ዝም ብሎ የዘልማድ አባባል እንጂ ሌላ አይምሰልዎ። ካላመኑን ትችትዎ የወጣችበትን "ላንዳፍታ"ን ይመልከቱ።



# በአትላንታ
# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች
# ከገዙት ቤተክርስቲያን ገቡ።



የአትላንታ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ከስምንት ዓመት የኪራይ ቤት ወጥታ ወደ ራሷ ቤት ገባች። አባ ገብረመስቀል መኩሪያ ወደ አትላንታ በመጡ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከቦርዱ ጋር በመሆን ምዕመናኑን በማስተባበር ቤተክርስቲያን በመግዛትና በማደስ ያደረጉት ጥረት ተሳክቶ ይኸው ዛሬ የአትላንታ ምዕመናን የራሳቸው የሆነ ቤተክርስቲያን ባለቤት ለመሆን በቅተዋል።

ነሃሴ ፳፪ ፲፱፻፹፮ ዓ ም (August 28, 1994) በተደረገው ታላቅ በዓል ብፁዕ አቡነ ይስሀቅ፣ ብፁዕ አቡነ መልከሰዴቅ እንዲሁም ከተለያዩ እስቴቶች የመጡ ካህናት በተገኙበት ሙሉ ሥርዓተ ቅዳሴ ተከናውኖ፣ ታቦተ ህጉ በሙሉ ሥርዓት በባህላችን መሠረት በመንበረ ታቦቱ ገብቷል።

ወደ አንድ ሺህ የሚቆጠሩ ምዕመናን የተሳተፉበት ይህ ክብረ በዓል የተከናወነው ከሥርዓተ ቅዳሴው በኋላ በእልልታና በደስታ ታቦተ ህጉን በማጀብ አካባቢው በሚገኘው ጎዳና ላይ በመዘዋወር ነበር ። ከፍትኛ ድምቀት በነበረው በዚህ በዓል ላይ የነበሩ ብዙ ምዕመናን ከአገር ከወጡ ወዲህ አይተው በማያውቁት በዚህ ሥርዓት ላይ መገኘታቸው እጅግ ያስድሰታቸው መሆኑን ገልጽዋል። ብዙዎቹም ከደስታ ብዛት ዓይናቸው እንባ አዝሎ እንደነበረ ለማየት በቅትናል።

ቤተክርስትያኑን መርቀው የከፈቱት የምዕራቡ ዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ሊቀ ዳዳስ ብፁዕ አቡነ ይስሀቅ ነበሩ። በዚሁ ዕለት የቤተክርስቲያኒቱ የቦርድ ሊቀመንበር አቶ ተፈራ ወንድማገኘሁ ይህንን ለማከናወን የተደረገውን ጥረት፣ ያጋጠሙትን መሰናክሎች ካስረዱና ለዚህ ታላቅ ዓላማ የገንዘብ፣ የቁሳቁስና የጉልበት ዕርዳታ የሰጡትን አመስግነው አባ ገብረ መስቀል መኩሪያ በከፍተኛ ደረጃ አድንቀዋቸዋል።









## የበዓሉን ሥነ ሥርዓት የሚያሳዩ ፎቶግራፎች












# ጓደኛ ለሚፈልጉ

ጓደኛ ፈላጊዎች ራሳቸውን እስተዋውቀው፣ ሊተዋወቁ የሚፈልጉትን ሰው ዓይነት የሚጠቁሙበት አምድ ነው። ስምና ትክክለኛ አድራሻ በመጽሔቱ ላይ አይወጣም። በስምና አድራሻ ፋንታ የኮድ ቁጥር ይወጣል። የኮዱን ቁጥር የምንሰጠው እኛ ነን። በስምና አድራሻ ምትክ የኮዱ ቁጥር ይወጣል። ስምና አድራሻ እኛ ጋ በምስጢር ይቆያል። ትክክለኛ ስምና አድራሻ ግን እኛ ጋ መድረስ አለበት።በጣም አጠር ተደርጐ ቢጻፍ ዕድሉን ለብዙ ሰው ማዳረስ ይቻላል።

ለመተዋወቅ የምትፈልጉት ሰው ዓይነት ወጥቶ ካገኛችሁ ቁጥሩን በመጥቀስ ደብዳቤ ጽፋችሁለት/ጽፋችሁላት እነስ ያለ ኤንቨሎፕ ውስጥ አሽጋችሁ ኤንቨሎፑ ላይ የናንተን ሙሉ አድራሻ በተለምዶ፣ የሚላክለትን/የሚላክላትን ሰው ኮድ ቁጥር በእርሳስ ጥጉ ላይ ጽፋችሁ በሌላ ከፍ ባለ ኤንቨሎፕ ውስጥ ከታችሁ አሽጋችሁ በአድራሻችን ትልካላችሁ። እኛም የኛን ፖስታ በመክፈት ከውስጥ ያለውን ኤንቨሎፕ አውጥተን የኮድ ቁጥር የተጠቀሰውን ግለሰብ ትክክለኛ አድራሻ ከመዝገባችን ኤንቬሎፑ ላይ በመሙላት እንልካለን። ከዚያ በኋላ እንደፍጥርጥራችሁ።

የሚከተሉትን መመሪያዎች በደምብ አጢኑ።

1ኛ. ለፖስታና ለአገልግሎት አከፋፈሉ በሚቀጥለው ዓይነት ይሆናል፤
ከአሜሪካ - $5.00 (በmoney order)
ከካናዳና አውሮፓ - $6.00 (በአሜሪካ ገንዘብ፣ money order)
ከኢትዮጵያ - ምንም አይከፈልም።
ለ"ላንዳፍታ" ቋሚ ደምበኞች (subscribers)
(ላንዳፍታ ማዘዣ ቅጽ ሞልታችሁ ከፍያ የላካችሁ) $4.00 ብቻ ነው።
2ኛ. ዕድሜያቸው ከ18 በታች ለሆኑ ይህ አገልግሎት አይሰጥም።
3ኛ. ይህ አምድ ዓላማው መተዋወቂያ መድረክ ለመፍጠር ብቻ መሆኑን መግለጽ እንወዳለን።
4ኛ. እባካችሁ እንዲጻፍላችሁ የምትፈልጉትን ነገር አሳጥሩት።
5ኛ. በመጀመሪያ የብዕር ጓደኝነትን በማጠንከር የበለጠ መተዋወቅን እንመክራለን።

አዲሱ አድራሻችን፤

LANDAFTA
P.O.BOX 49301
ATLANTA, GA 30359

## ጓደኛ የሚፈልጉ ሴቶች

ስም 1071፤ ዕድሜ 29፤ መኖርያ አዲስ አበባ፤ የትምህርት ደረጃ ኮሜርስ፤ ኦርቶዶክስ ክርስትያን፤ እስካሁን አላገባሁም፣ ልጅ የለኝም። መተዋወቅ የምፈልገው ወንድ፤– ኢትዮጵያዊ፤ ያላገባ ልጅ የሌለው፤ በትዳር የሚያምን፣ ቤቱን ትዳሩን የሚወድ ታማኝ፤ የማይጠጣ፣ የማያጨስ (በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰህ ጻፍልኝ።)

## ጓደኛ የሚፈልጉ ወንዶች

ስም 1072፤ ዕድሜ 35፤ መኖርያ ዩናይትድ እስቴት፤ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ፤ መተዋወቅ የምፈልጋት ሴት፤ ዕድሜ ከ23 እስከ 30፤ ኢትዮጵያዊት፤ መልከመልካም፤ ብሩህና ከቀድሞውም ከዘመኑም የባህል ተፅዕኖ በተወሰነ ደረጃ ነፃ የሆነች (በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰሽ ጻፊልኝ።)

አዳም ሔዋን

# አላለልኝ ይሆን ! !

ከትዝታ

(ካለፈው የቀጠለ )

ውስጠ ህሊናዬ ብዙ ይታገለኛል። የሆነን ነገር መቀበል የተሳነኝ ይመስለኛል። ዕቃውን ጠቅልሎ ታክሲ ጠርቶ መሄዱን ዓይኔ እያየ ህሊናዬ አልቀበል ማለቱ ይገርመኛል። ተነስቼ አለመሸኘቴ፣ ደህና ሁን ብዬ አለመሰናበቴም ለዚሁ ይሆን? ብቻ ምን አለፋችሁ ቁጭ ብዬ ቀረሁ፣ የሚመለስ የሚመለስም መሰለኝ። ሲግደረደርም ነው የሚል ስሜት ለአፍታ ውልብ ብሎብኝ ነበር። እኔ ልጅት ወንድ ልጅ ሲሸነፍልኝና እጅ ሲሰጠኝ ነው የለመድኩት፤ ጥንት ያኔ፤ እና እሱም በቃ እጅ ሰጥቻለሁ አሳንቺ ይህች ዓለም ለኔ ዓለም አይደለችም ካላለ ምኑን እቀበለዋለሁ። ከዚያ ታዲያ ለኔ ያለው ፍቅር እያስገደደው የምፈልገውን ሳልጠይቀው አውቆ ማድረግ አለበት፤ እኔን ለማሸነፍ። ያኔ ታዲያ ልቤን ትንሽ ለዓመል ያህል ከፈት አደርግለትና በዚያው ደስታ ይዞት ሲፍንክንክ ነው እኔን መማረኩ የሚገባኝ። ያደግሁባት ዓመሌ ይህች ናት፤ ይህችን መረዳት ደግሞ የሱ ፋንታ ነው። እሱ ግን ኩሩ ነው መሰለኝ። ዓመሌን አላወቀም። ደግሞ ፍርሃት ፍርሃት አለኝ፤ እሱም ጥሎኝ ሄደ፤ ሌላውም ዞር ብሎ አላይ አለኝ፤ አገኘሁት ያልኩት ለኔ ይገባል ያልኩት ሁሉ ወይ ቀደም አድርገው ይዘውታል፤ ወይ እኔን ለጊዜያዊ እርካታው ተጠቅሞብኝ ይሸሸኛል፤ ዕድሜዬ ደግሞ ገፋ። ታዲያ ይህ ሰው ምን ጎደለው? ለአፍታ በአዕምሮዬ ለመጣው ድንገተኛ ሃሳብ መፍትሄ ቢሆን ብዬ ከመቀመጫዬ ብድግ አልኩና እሱ ወደ ወጣበት በር ሄጄ በሩን ከፈትኩ፤ ሃሳቤ ተመለስ ለማለት ነበረ መሰለኝ። ግን እሱ የለም። ከመቼው ታክሲው እክልፍልፎ ይዞት ሄዷል። ታክሲ ነጂውን በሆዴ ሳልረግመው አልቀረሁም። እሱም ሄደ፤ እኔም ቀረሁ። ተመልሼ ቤቴ ገባሁ። የምይዘው የምጨብጠው ጠፋኝ። በአንድ ወገን እንዴት አይለማመጡኝም? የማን ቀብራራ ነው? ሲል ኩሩ መንፈሴ በሌላ በኩል ደግሞ ፀፀት የገባው ስሜቴ ምነው እንደዚያ ባላልኩት ማለት ሲጀምር ከጠረጴዛው ላይ ያለው ማጽናኛዬ የወይን ጠጁ ታየኝ።

የዚያን ዕለት ማምሻውን ከቤቴ አልወጣሁም። ድንገት ጸጽቶት ቢደውል ከቤት እንዳያጣኝ። አንድም ስልክ ሳይደወል ቀረ። ቀደም ሲል ለጓደኞቼ ወደ ሌላ ከተማ እሄዳለሁ ብዬ ዋሽቼ ስለነበር እነሱም አልደወሉም።

በትካዜ ባህር ብቻዬን ከወይን ጠጄ ጋር መዋኘት ጀመርኩ። ማምሻውን ወደ አስር ሰዓት ገደማ አንድ ሃሳብ መጣልኝ። እሱ አሁን እቤቱ ደርሷል፣ ቁም ነገረኛ ሰው በመምሰል ደህና መድረስ አለመድረሱን በመጠየቅ ሳቢያ ለምን አልደውልለትም የሚል ነበር። ለመደወል ስልኩን ካነሳሁ በኋላ መልሼ ቁጭ አደረግሁ። ልትለማመጠኝ ነው ብሎ ቢያስብስ? ልደውል አልደውል በማለት ከራሴ ጋር እተካራ ገጠምኩ። ስልኩን እያነሳሁ መልሼ እያስቀመጥኩ፤ አንዳንዴም ቁጥሩን መደወል ጀመር አድርጌ በመተው፤ ብቻ ምናደከማችሁ፣ መንፈሴ ተቀበዘበዘ። መጽናኛዬን የሆነችውን የወይን ጠጄን በገፍ ተያያዝኩት። ሌላ ሃሳብ ብልጭ አለብኝ።

"የምን ሞኝነት ነው። የምንስ አጉል መግድርድር ነው። ሰውዬውን እንደሆነ መንፈሴ ፈቅዶታል። ያለፈው ምሽት አብረን ያደረግነው ነገር እንደሆን ተስማምቶኛል። በጣም ነው የተደሰትኩት፤ በዚህ ላይ ደግሞ የተማረ፣ አስተዋይ ሰው ነው፤ ረጋ ያለ፣ ለትዳር የሚሆን ሰው ነው። ታዲያ ምን ጎደለው?" ብዬ ቀና ቀናውን ማሳብ ጀመርኩ። እሱ እያለ ያደረግሁት ነገር በወቅቱ ትክክል መስሎኝ ባደርገውም አሁን እሱ በሌለበት ቦታ ይጸጽተኝ ጀመር። "ምነው እንደዚያ ባላልኩት? ምነው እንዲያ ባላደረኩ? እያልኩ ያለፈውን ያደረግሁትንና የተናገርኩትን ነገር ሁሉ ማሰላሰል ጀመርኩ።

በርግጥ ለሱ እንደገለጽኩት "I am not attracted to you" ያልኩት ከልቤ ይሆን? ወይስ ለሌላ ምክንያት መሸፈኛ ነው? በሆዴ ያለው እውነቱን ነገር ለራሴ እንኳ ለመግለጽ ያልፈለግሁበት ምክንያት ጭራሽ አልገባኝም። "moody ነሽ" የሚሉኝም ለዚህ ይሆን? አንዳንዴ ሴቶች ላይ ያለብን ችግር አለ። በሆዳችን ያለውን ነገር ወንዶች ሲያውቁብን በተለይም ግንኙነት ያለን ወንዶች ሲያውቁብን ያቅበጠብጥናል፣ ያናድደናል። እውነት የሆነውን በሆዳችን ያለውን ነገር ሲያውቁብን ሆነ ሲነቁብን የተሸነፍን ይመስልናል። ሴቶች ይህን ባንካካድ ጥሩ ነው። እሱ ". . . ከግምቷ በላይ ሆኖ ስላገኘችው እውነት አልመስላት ሊላት ይችላል። . . . የተጠበቀው ነገር ከግምት በላይ ሆኖ ከተገኘ አቀባባሉ ሊጠፋ ይችላል . . ." ያለው አባባል ለአፍታ ውልብ አለብኝ። ይህስ ቢሆን? ደግሞስ ይህም ባይሆን? ሌላ ምክንያትስ ቢኖር? ይኸው እንዳልኳችሁ ለራሴም ታማኝ መሆን ሲቸግርኝ። አይቀርም እነግራችኋለሁ፤ እውነቱን። ብቻ ከሃሳቤ ባህር ስወጣ ልድውልለት መወሰኔን ልንገራችሁና የሆነውን ላጫውታችሁ።

ስልኩን ብድግ አድርጌ ደወልኩ። እሱው ጋ። ልለው የፈለግሁትን ወስኜ።

"አሎ፤ ማን ልበል?" አለኝ። ትደውላላች ብሎ እንዳልጠበቀ ተረዳሁ።

“ትዝታ ነኝ፤ ደህና መግባትህን ለመረጋገጥ ነው የደወልኩት፤ ደህና ገባህ?” አልኩት። ፈልጋ ነው የደወለችው ቢልም አሁንስ ግድም አልነበረኝ።

“አዎ ደህና ደርሻለሁ፤ አመሰግናለሁ፤” አለኝ።

ጊዜ ማጥፋት አልፈለግሁም። “የደወልኩልህ ሌላም ምክንያት ኖሮኝ ነው፤ ፈቃደኛ ከሆንክ ልንገርህ።” አልኩት። ፈቃደኛ አይደለሁም ቢለኝ ምን መልስ እንደምሰጠው ግን ያልተዘጋጀሁበት ጉዳይ ነበር።

“I hope ጭቅጭቅ የሚያነሳ እንድማይሆን!” አለኝ።

“ምንም ጭቅጭቅ የለውም። አንተ ከሄድክ በኋላ ከልቤ የተሰማኝን ልገልጽልህ ፈልጌ ነው፤” አልኩት።

“እሺ፣ ምንድነውሱ?” አለኝ።

“በመጀመሪያ ላደረግሁት ነገር፣ ለተናገርኩህ መጥፎ አባባል ሁሉ ከልቤ ይቅርታ እጠይቃለሁ፤” አልኩት።

“ትዝታ፣ ይህንን የምትይው ከህሊና ጸጸት ራስሽን ነጻ ለማድርግ ነወይስ እኔን የጎዳኝን የመንፈስ ቁስል ለማሻር?” አለኝ።

“ለየትኛውም ይሁን የምለውን ተናግሬ ስጨርስ ልታውቀው ትችላለህ። መቼም ታውቃለህ። እኛ ሴቶች የተለየ ባህርይ አለን። delicate ነን። ለመከፋትም፣ ለመደሰትም፣ ለሁሉም sensitive ነን። እና በኋላ ደግሞ በሆነው ነገር ደግሞ ቶሎ መግለጽ ባንፈልግም እንጸጸታለን። እና ይህን የምልህ ምክንያት ኖሮኝ ነው። አንተ ከሄድክ በኋላ ምን ዓይነት ጸጸት ውስጥ እንደገባሁ ለመግለጽ ቃላት ያጥረኛል። በመጀመሪያ ነገር “I am not attracted to you” ያልኩህ ከልቤ አይደለም። ‘. . . ከግምቷ በላይ ሆኖ ስላገኘችው እውነት አልመስላት ሊላት ይችላል። . . . የተጠበቀው ነገር ከግምት በላይ ሆኖ ከተገኘ አቀባበሉ ሊጠፋ ይችላል . . .” ስትለኝ ልክ ነው ብዬ ብቀበልህ የተሸነፍኩ ያስመስልብኛል በማለት ነው። ምናልባትም ያ አባባልህ ልክ ሊሆን ይችላል። ስለሱ ያለኝን አስተያየት ባትጠይቀኝ ደስ ይለኛል። ይህን ልልህ የፈለግሁት “I am not attracted to you” ላልኩት መነሻውን ለመግለጽ ብዬ ነው።

“ልጠይቅሽና እንዲህ ካልሽ እንግዲህ አሁን! Are you attracted to me?” አለኝ።

“ይኸው ስነግርህ መልስህ እዚያው ትሄድብኛለህ። don't forget አበሻ ነኝ።” አልኩት።

“እና?”

“ማለት የፈለግሁት ይገባሃል። ብማረክብህም ተማርኬልሃለሁ ብዬ መናገር ያሳፍረኛል፤ የባህልና የልምድ ጉዳይ ስለመሰለኝ በዚህ ልትከሰን አትችልም።” አልኩት።

“በዚህስ አልከስም። የምከሰው ግን በሌላው ባህርያችሁ እንደፈረንጆች እንሁን ስትሉ ነው።” አለኝ።

“በሱም አንከሰስም። ያለንበት ሁኔታና ቦታ እንዲታይልን እንፈልጋለን። በአገራችን ባህል ዙሪያ አድግን አሁን የምንኖረው በፈረንጆቹ ባህል ውስጥ ስለሆነ መስለን ለማደር የምናደርገው ድርጊት ነው። በተበረዘው ባህላችን፣ ማለትም በምዕራባዊው ዓይናውጣነትና በኢትዮጵያዊው ይሉኝታና ዓይናፋርነት መሀል ተንጥልጥለን ከሁለት የወደቀ ዛፍ ሁነናል። እና ይህን ደግሞ መረዳት የሚያቅትህ አይመስለኝም። ” አልኩት።

“ምነው ከሌላ አገር በመጡት ላይ ይህን ባህርይ አናይም? ለምሳሌ ሜክሲካኖችን ውሰጂ፤ ሽረ ሌሎችንም?” አለኝ።

“ይህስ እኔንም አንዳንዴ ሳይገርመኝ አይቀርም። ምናልባት ኋላቀር ከሆነ አገር በመምጣታችን ፈረንጅን እንዳምላክ ከማየት የመነጨ ሊሆን ይችላል። እስቲ አሁን ምርምሩን ልተውና ወደ ቁምነገሩ ልመለስ። እና ታዲያ ማንም አበሻ ሴት በአንድ ወንድ ብትማረክ ተማርኬአለሁ ብላ በቃል ለመግለጽ አትደፍርም፤ እስከማውቀው ድረስ። “አባቶቻችን “ሙያ በልብ ነው” እንዲሉ በተግባር ነው የምታሳየው።” አልኩት። እንቺ መውደድሽን በየትኛው ተግባር ነው የገለጽሺልኝ ቢለኝ መልስ የለኝም። እንግዲህ ቢገባው ይግባው።

ለጥቂት ደቂቃ ዝም ማለቱ አሳሰበኝና፤ “አለህ ወይስ ስልኩን ዘግተኸዋል?” አልኩት።

ቁና ተንፈስ አለና፤ “አለሁ፤ የት እሄዳለሁ፤ እንዳው ነገሩ ገርሞኝ ነው።” አለ።

“ምኑ ነው የሚገርም?” አልኩና ጠየቅሁት።

“እዛ እያለሁ ያየሁብሽ ሁኔታ አሁን ከምትነግሪኝ ነገር ጋር አልጣጣም ብሎኝ ነዋ?” አለኝ ድምጹን ለስለስ አድርጎ።

“ያኔ እኔ ራሴ ምን እንደሆንኩ አላወቅሁትም፤ ሁሉ ነገር ተምታታብኝ። ምናልባትም እንዳልከው too good to be true ሆኖም ሊሆን ይችላል፤ ወይም ህሊናዬ በውስጤ subconciously የሚያስብው ነገር ኖሮ ያንን ሊገልጽ አልፈለገም ይሆናል። በወቅቱ ስፈጽመው ራሱ ትክክል የሆነ ነገር እንደፈጸመ ሰው ሁሉ ሆኖ ነበር የሚሰማኝ። ቆይቶ ሳስበው ‘ምን ማለቴ ነው‘ እላለሁ። ስለዚያ ስለፈጸምኩት ስህተት እያሰብኩ እንደገና ሌላ ስህተት እፈጽማለሁ።” አልኩት፤ አነጋጋሬ ሁሉ ከልቤ ነበር።

“ትዝታ እዚያ ያላሸበት ቦታ ድረስ የመጣሁት አሁን እንዲህ የምትናገሪውን ግልጽ ልጅ ለማግኘት ነበር።”

“ግን አላገኘሃትም። ይህን አውቃለሁ። አንተው ከማለትህ በፊት እኔው ልጨርሰው፤” አልኩት።

“አዎ ልክ ነሽ፤ አልተሳሳትሽም፤ አላገኘሁዋትም። ያችን ቀደም ሲል ለሶስትና አራት ሰዓት ሳልሰለች በስልክ ስንት ቁም ነገር ስታወራ የነበረችውን ትዝታን አላገኘሁዋትም። ቢገርምሽ ተሳስቼ ከሌላ ሰው ጋር ነወይ የተገናኘሁት ብዬም አንድ ወቅት አስቤ ነበር። እንዳው እስቲ ልጠይቅሽ አንድ ነገር፤ ምናልባትም ለዚህ መልስ ካለሽ እንደዚያ የሆንሽበትን ምክንያት ልታውቂው ትችያለሽ። ምን መሰለሽ የምጠይቅሽ? ገና አይሮፕላን ማረፊያ መጀመሪያ physically እንዳየሽኝ በግምትሽ ውስጥ የነበረውን ሰው ነወይ ያገኘሽው?” አለኝ።

“ግልጽ ሆኜ ልንገርህና ገና አንተን ለመጠበቅ ወደ አይሮፕላን ማረፊያ እየመጣሁ እያለ ነበር እንደ

መነጫነጭ እንደ መነጫነጭ ማድረግ የጀመረኝ፤ እና አንተን ከማግኘቴ በፊት ጀምሮ እንዳው neagtive negative የሆነ ነገር ብቻ ይታየኝ ስለጀመረ ከግምቴ ውጪ የሆነ ሰው ነው ያገኘሁት ብዬ ለመደምደም ያዳግተኛል።” አልኩት።

“ሌላ ጥያቄ ደግሞ ልጠይቅሽ። I want you to be absolutely frank. ለመሆኑ አንቺ በአሁኑ ጊዜ ባል ለማግባትና የኑሮ ጓደኛ ለማበጀት fully ready ነኝ፤ እና እፈልጋለሁ ብለሽ ወስነሻል ወይ?” አለኝ።

“ምን ማለትህ ነው? ይህን ቀደም አድርጌ ነግሬህ የለ? ገና የተዋወቅን ሰሞን። እንደምፈልግና ready እንደሆንኩማ ነግሬህ ነው እዚህም ልትመጣ የተነጋገርው፤” አልኩት።

“እሱንማ አውቀዋለሁ። እንዳው ለሌላ ጥያቄ መነሻ እንዲሆነኝ ብዬ ነው። እስካሁን ሳታገቢ የቆየሽበት የራስሽ ምክንያት ይኖርሻል። እሱን ማወቅ አልፈልግም። ማወቅ የምፈልገው አሁን የደረሰሺበት ዕድሜ ሳታገቢ ቆይተሽ አሁን ለማግባት የወሰንሽበትን ዋናውን ምክንያትሽን እንድትመረምሪው ለማድረግ ነው። ይህ ሁኔታ በርግጥ አንቺ በጋብቻ የማመን ያለማመንሽ ሁኔታ ይጠይቃል። በርግጥ በጋብቻ ታምኚያላሽ ወይ? ማለትም ስታጋቢ አንድ ከመሆን ወደ ሁለት ልጅ ሲወለድም ሶስት አራት መሆን ይምጣል። እንግዲህ በራስ ብቻ የሚወሰን፣ ለራስ ብቻ የሚታሰበው ይቀርና ለሁለት ማሰብ፣ የራስን ሃሳብ ብቻ ማከናወን ይቀራል። በግልሽ ብዙ የምትወጂውን ነገር መስዋዕት “sacrifice” ታደርጊያለሽ ማለት ነው። እንግዲህ How much are you ready for that? Are you ready to sacrifice some of your interests? ይህን የምጠይቅሽ ምክንያት ኖሮኝ ነው። ምናልባት እዚህ ላይ ይቅርታ እጠይቅሻለሁ። ጋብቻን ሰው ስለፈለገው ፈልገሽው ግን እነኚህን አንዳንድ interests መስዋዕት ለማድረግ ዝግጁ ላትሆኚ ትችያለሽ። ምናልባትም ይህ ፍርሃት ሊሆን ይችላል በsubconcious አዕምሮሽ ውስጥ ተቀርጾ ያለ? ምን ይምስልሻል? በዚህ መንገድስ አይተሽው ታውቂያለሽ?” አለ።

የሚገርማችሁ ነገር በስልክ ስናወራ በጣም ነው የምንግባባው። የፈለገውን ቢናገር እሰማዋለሁ። እዚህ መጥቶ በህይወት ተገናኝተን የተነጋገርን ጊዜ ሰይጣኔ ነበር እስሬ የመጣው፤ ይህን ሳትታዘቡ አልቀራችሁም። አሁን ያለውን ነገር ልብ ብዬ ነበር ያዳመጥኩት፤ እሱ ያለውስ ነገር ቢሆን? እሱም ነው ብዬ መቀበሉ አልታየኝም።

“እኔ የማውቀው ready መሆኔን ነው።” አልኩት።

“ትዝታ ሰው ምን ይለኛል ብሎ ጋብቻ ሲባል ሰምትሻል? ” አለኝ።

“ሰው ምን ይለኛል ብሎ?” አልት በመገረመም እንደመሳቅም ብዬ።

“እንዲት የጓደኛዬ ሚስት የነበረች አሁን ተፋተዋል፤ እሷ ናት ይህን ስም የነገረችኝ። ከባሏ ጋር ልናስታርቃት ወዲያ ወዲህ ስንል ‘አሻፈረኝ አልታረቅም‘ ስትለን ይህንኑ ጥያቄ አቀረብኩላት። ጓደኞቿ ሁሉ አግብተው እሷ በመቅረቷና ደግሞ ጓደኞቿ ስለጨቀጨቋት እንጂ ለጋብቻ ዝግጁ ሆና እንዳላገባች ነገረችን። በ35 ዓመቷ ዝግጁ እንዳልሆነች ሁሉ። ታዲያ ጋብቻን የተቀበለችው ጓደኞቿ ስላደረጉ፣ ከሁሉ በላይ የሚገርምው ያገባችውን ሰው እሷ ይህን ያህል ወዳው ሳይሆን ጓደኞቿ ግርማ ሞገስ አለው ስላሏት ነበር። የሚገርምሽ ነገር ላግባሽ እያለ ያስቸግራት የነበረ እሷም በሃሳብም በሁሉም ነገር የምትግባባው ሌላ ሰው እንደነበረና ጓዲኞቿ ‘ምነው ይህን ውቃቢ የራቀው ቀትረ ቀላል፣ ስንቱ ሸበላ እያለ‘ ስላሏት ብቻ እንጂ ገና ከመጀመሪያውኑ ከዚህ ከጓደኛዬ ማለት ከባሏ ጋር ይህን ያህል መግባባት እንዳልነበራት ነገረችን። ነገሩ ገባኝና ቢታረቁም አብረው መቆየት እንደማይችሉ ተረዳንና ተውነው እልሻለሁ።

“ተፋቱ በቃ?” አልኩት በጉጉት።

“ተፋቱ። እሱን ከፈታች በኋላ ያንን ፊት ፈቅዳው የነበረውን ሰውዬ ልታገባው ስታፈላልገው እሱ አግብቶ ልጅ ወልዶ አገኘችው፤” አለ።

“በቃ እሷ ሌላም አላገባች?” አልኩና ጠየቅሁት። ስለዚች ልጅ ለምን ደጋግሜ እንደጠየቅሁት አላውቅም።

“እሱን ማወቅ የምትፈልጊ አይመስለኝም።” አለኝ።

“ንገረኝ፣ ለምን አልፈልግም?” አልኩት።

“መጨረሻዋማ አላማረም። በዚያ ብስጭትም ይሁን ተስፋ በመቁረጥ frustrate አደረገች። ጓደኞቿ ሁሉ የልጆች እናት በመሆናቸው ከልጆቿቸው ጋር ብዙ ጊዜ ስለሚሆኑ ለሷ ጊዜ አጡላት። እርግፍ አድርጋ ተወቻቸው። በጣም ወጣት፣ ከዕድሜዋ በጣም ያነሱ ወጣቶች የሚዝናኑበት ቦታ መሄድ ትጀምርና ሲመሻሽ አንዱን በድብቅ እየጠለፈች እቤቷ ትወስዳለች። ሌላ ጊዜ ደግሞ ሌላውን። ‘ተረኛ ዛሬ ማን ይሆን? አንተ ወይስ እኔ?‘ እያሉ ማላገጫ አደረጓት። የከተማው ወሬ ሆነች። አሁንማ በቃ መጠጥ ጠጪ ሆና ዞር ብሎ የሚያያት የለም።” አለኝ።

ደነገጥኩ። በጣም ደነገጥኩ። የኔም መጨረሻ ይህ ይሆን? በርግጥ እሱ እንዳለው የማገባው ጓደኞቼ አብዛኞቹ ስላገቡ ይሆን? እሱንስ እንደዚያ አድርጌ ያስተናገድኩት የኔን ሳይሆን የጓደኞቼን ፍላጎት ስለማያረካና፤ እሱን ይገፍ ጓዲኞቼ ጋ ስቀርብ እነሱ እንደሚንቁት ገምቼ ይሆን? ውቃቢ የራቀው ብለው ይተቹብኝ ይሆን ብዬ በመፍራት ይሆን? ወይስ ሌላ ምክንያት ነበረኝ? ” . . .

(በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል)

## ውድ አንባብያን

ይህ ታሪክ በዚህ መጽሄት ላይ መውጣቱን የተመለከተውና ታሪኩን የተከታተለው የዚህ ገጠመኝ ሁለተኛው ባለታሪክ (ትዝታ ጋ መጥቶ አፍሮ የተመለሰው) የዚህኑ ታሪክ በሱ በኩል ያለውን ሁኔታና እሱም የተሰማውን ልኮልናል። ከሚቀጥለው እትም ጀምረን በተከታታይ እናቀርባለን።

# ዕጣዬ

ከአብረኸት

ከአለፈው የቀጠለ

## ክፍል ፭

የአባቷንና የእናቷን ትዕዛዝ የማታከብር ዱሪዬ ልጅ ናት ብላችሁ እንደማትገምቱኝ ተስፋ አደርጋለሁ። የቤተሰብ ሁኔታ ምስቅልቅሉ የወጣበት፣ አባትና ልጅ የማይደማማጥበት ጊዜ እንደነበረ በወቅቱ እዚያ የነበራችሁ ታውቁታላችሁ። አባቴን እወደዋለሁ፤ በአባትነቱ አከብረዋለሁ። ፍቅርንና ሰላምን የሚያስትምሩኝን የአባቴን ባህሎች ቅርሶችና ልምዶች እጠብቃለሁ። አከብራለሁ። በአንፃሩ ጥላቻንና መሠረት የሌለው መናናቅን የሚያስትምሩኝን ኋላ ቀር ልምዶች ብኮንን የአባት እናቴን ትዕዛዝ እንደናቅሁ ተደርጎ ሊታይብኝ አይገባም ባይ ነኝ። ወደ ታሪኬ ልመልሳችሁ።

የዚያን ዕለት ተከስተን በቅጡ ባለማነጋገሬ አባቴ ተናዶ ሳለ እኔም ሰይፉ ጋ ስልክ ደውዬ ከሱ ጋር ሳወራ አባቴ መጥቶ ስልኩን ከጄ ነጥቆ፤ የምወደውን የሚያስብልኝን ሰይፉን ስድቦ፤ ማስጥንቀቂያ በመስጥቱ ምን ያህል እንዳስደነገጠኝና እንዳናደደኝ ተረዱልኝ። በአባቴም ላይ ሊኖረኝ የሚችለው ፍቅር ምን ያህል ሊቀንስ እንደሚችል ተገንዝቡልኝ። የልጁን ደስታ የማይሻ አባት ማነው? ልጁንስ በግድ እሱ ለሚፈልገው ዓላማ፣ እንዲያውም በእግዜር ዘንድ እንደ ኃጥያት ለሚቆጠረው ጥላቻ ልጁን የሚማግድ አባት፤ ብሎም ለራሱ የንግድ ሥራ ልጁን እንደ ሸቀጥ ለማቅረብ የሚፈልግ አባት ማነው? ተከስተን አላውቀውም፣ ከኔ ዘር የመጣ በመሆኑ ብቻ ለኔ ጥሩ ባል ይሆናል ብሎ መገመትስ ምን ይባላል? ፍቅር ወሰን የለውም። ዘር አያይም፣ ይህ እንዴት አባቴን አልታይ አለው?

አባቴ የዚያን ዕለት ባደረገው ነገር ልናደድ እንጂ በሌላ ጎኑ በጣም ፈራሁት። ምን ዓይነት ፍርሃት? ከመውደድና ከማክበር የሚመነጭ ወይስ ከጥላቻ የመነጨ? እናንተው ገምቱት።

የምወደውን ሰይፉን የሚያጠቃብኝ ሆኖ ታየኝ። ሰይፉን ከኔ ለመነጠል የማያደርገው ነገር እንደሌለ ነው የታወቀኝ። አባቴ ማድረግ የሚፈልገውን ነገር ማድረግ ካልቻለ እልህ ይገባል። እልህ ሲገባ ቂም ይጭራል። ቂም ከያዘ ደግሞ መሣሪያው ገንዘብ ነው። እና ስልኩን ከጄ ነጥቆ "በፖሊስ ነው የማስይዝህ" ብሎ ሲዝትበት ከልቡ እንደሆነ አውቀው ነበር። እኔ ላይ ሲያፈጥብኝ ያስደነገጠኝም ይኸው ዛቻው ነበር። እልህም ይሁን ምን እኔም መልሼ አፈጠጥኩበት፤ እንደሌላው ጊዜ ሁሉ ዓይኔን ስብር አድርጌ ዞር አላልኩም። እንባ በሞላው ዓይኔ ጭጋግ አባቴ ሌላ መስሎ ታየኝ።

"ይህን ዱሪዬነትሽን አሁንም አልተውሽም ማለት ነው?" አለኝ በጥፊ ሊመታኝ እየከጃጀለው። መልስ አልሰጠሁትም። በእልህና በንዴት ሳቢያ የመጣብኝ እንባ ወርዶ ጉንጬ ላይ ዱብ ሲል ተሰማኝ።

"ምን ሆንኩ ብለሽ ነው የምታለቅሺው? ሟርተኛ! " አለ።

መልስ አልሰጠሁትም። አፍጥጬ ዓይን ዓይኑን ማየቴን ቀጠልኩ።

"የምን ትዕቢት ነው መልስ የማትሰጪኝ? " አለ የባሰ ቆጣ ብሎ።

በእጄ ዓይኔ ላይ የወረደውን እንባ ጠረግሁና እዚያው ትቼው ጓዳ ወዳላችው ክፍል ገባሁና ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ። ተከትሎኝ አልገባም። አልቅሼ አልቅሼ እንዳበቃሁ ለቅሶ ብቻ መፍት እንደማይሆን ተረዳሁ። ከአባቴ ቤት የመኖር ተስፋዬ እንደጨለመ ታየኝ። እስከዚያም ድረስ ማለትም አንድ መፍትሄ እስካገኝ ድረስ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብኝም አወቅሁ። የምሰጠውን መልስ፣ የማደርገውን ነገር ሁሉ ጥንቃቄ ካላደረግሁ ሰይፉን ለጥቃት እንደምጋብዝ ተሰማኝ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንባዬን ጠራርጌ ተመልሼ ወደ መደብሩ ገባሁ። ምንም አላነሳም እሱም። ከዚያን ቀን ጀምሮ ቤትም ሆነ መደብሩ ውስጥ ዝምታ ትልቁ መሣሪያዬ ሆነ። የሚበጀውንም ነገር ለማስብ ዝምታዬ ጥሩ መንገድ መሆኑ ተሰማኝ። አባቴ አኮረፈኝ። ሰበብ እየፈለግሁ ላናግረው ስሞክርም ዘጋኝ። ይህ ደግሞ የበለጠ አሳሰበኝ። በባልነት የታጨልኝም ተከስተም ከዚያን ቀን ወዲህ ውድ መደብሩ መምጣት አቆመ።

ይህ ሁኔታ በተፈጸመ በሁለተኛው ሳምንት ገደማ አንድ ቀን እናቴ እቤት እንድውል አደረገችኝና አነጋገረችኝ። ምክር እንድትሰጠኝ አባቴ ያወጣው ዕቅድ እንደሆነ ገባኝ። ተከስተ ሽማግሌ እንደላከና እነሱም መልስ ለመስጠት ቀጠሮ እንደሰጡ እናቴ ነገረችኝ።

"ልጄ ሰውዬው ጥሩ ሰው ነው አሉ። አንቺም በዚህ ቀውጢ ጊዜ አረፍ ብለሽ ትዳር ይዘሽ ብትኖሪ ጥሩ ነው።" አለችኝ የዋህዋ እናቴ። እናቴ ይህን የምትለው እሷ አስባው ሳይሆን በይ የተባላችውን እንደሆነ ህሊናዬ ያውቀዋል።

"እማይ ሰውዬውን አላውቀውም። ካላወቅሁት ደግሞ ልወደው አልችልም። እንዴት አድርጌ የማልወደውን ሰው አግቢ ትይኛለሽ።" አልኳት እያስተዛዘንኩ።

"ልጄ መውደድ እኮ አብሮ ከመኖር የሚመጣ ነው። እኔ አባትሽን ከማግባቴ በፊት አለአንድ ቀን አላየሁትም። ታዲያ ይኸው ትዳራችን ጥሩ ሆኖ ሀብት አፍርተን እናንተን ልጆቻችንን ወልደን ስመን ተከብረን እንኖራለን፤" አለችኝ።

"አይ እማዬ! ይህ እኮ ድሮ በናንተ ጊዜ ሠርቶ ይሆናል። አሁን ጊዜው ተለውጧል። እማዬ የማልወደውን ልጅ አግባ ብለሽ አንቺ እንድማትፈርጂብኝ አውቃለሁ፤" አልኳት።

"ምን አድርጊ ትይኛለሽ ልጄ፤ አባትሽን ታውቂዋለሽ። እኔ በመሃል ቤት ጨነቀኝ።" አለችኝ።

ሆዴ በጣም ባባ። እናቴንም ጭንቀት ውስጥ መክተት አልፈለግሁም። በደፈናው "እማዬ ትንሽ ጊዜ ላስብበት፤ ጊዜ ስጭኝ፤" አልኳት።

የማስብውም አልነበረኝ፣ የተከሰተ ነገር እንደሆነ የሞተ ጉዳይ እንደሆነ ህሊናዬ ያውቀዋል። ጊዜ እንዲሰጠኝ የፈለግሁት የማደርገውን ነገር ለማመቻቸት እንዲመቸኝ ነው። እናቴም በዚሁ ጥያቄዬ ረክታ ሌላ ማውራት አልፈለገችም።

እንግዲህ በዚህ ሁኔታ ብዙ ልቆይ እንደማልችል ይታያችሁዋል። ያለኝ ምርጫ ሁለት ብቻ ነበረ። አባቴ እንደሚለኝ ሆኜ ከሱ ጋር ተስማምቼ መኖርና ሰይፉን መርሳት አንደኛው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የምወደው ሰይፉ ጋ ጠፍቼ መሄድ። የመጀመሪያው አማራጭ ላይ ያለኝን አቋም ነግሬአችሁዋለሁ። ሰይፉን ማጣት በፍጹም የማልፈልገው ነገር ነው። ቢሆንልኝ አባቴን ማስቀየምም አልፈልግም። ሰይፉን እንድወደው የሚያደርገኝ ደግሞ እሱ ለኔ ያለው ፍቅርና ሃሳብ ስለሆነ በምንም ነገር እሱን ላለመለወጥ ቁርጠኛ ሃሳብ ወሰድኩ። ችግሬ እንግዲህ እንዴት አድርጌ ነው ጠፍቼ እሱ ጋ የምሄደው? እንደዚያ ባደርግ አባቴ ሰይፉን አሳዶ ትልቅ ችግር ውስጥ እንደሚከተው አውቃለሁ። ለማንኛውም ሁኔታውን ከሰይፉ ጋር ለመነጋገር ወሰንኩ። አንድ ከመሆን ሁለት ሆኖ ማሰቡ ጥሩ መስሎ ታየኝና በአንድ የጥንት ጓደኛዬ ለቅሶ መድረስ አመካኝቼ ሰይፉ ቤት አንድ ቅዳሜ ጠዋት ሄድኩ።

በወራችን ነበር የተገናኘነው። ሰይፉ መጀመሪያ ሲያየኝ ደነገጠ። ሁኔታውን ሁሉ አስረዳሁት። ዓይኔ እንባ ሞልቶት ዓይን ዓይኑን እያየሁ ነበር አወራ የነበረው። እቅፍ አድርጎ ይዞኝ ካጽናናኝ በኋላ፤

"እንግዲህ ዘዴ መፈለግ አለብን፤ አንቺ እኮ መጀመሪያ ብለሽ ነበር፣ እኔ ነኝ ጥፋተኛው፤ ከሁሉ በፊት ለዚያ ስህተቴ ይቅርታ እጠይቅሻለሁ።" አለኝ እቅፉ ውስጥ እንደያዘኝ።

አያችሁት አይደል፤ ህይወት የሆነ ሰው እንደሆነ።

"ሰይፍዬ ምንም ጥፋት የለብህም። ያሰብከው ቢሆን ኖሮ ጥሩ ነበረ። ግን የአባቴን ሁኔታ ስላላጤንከውና የኔ አባት እንደሌሎቹ አባት ሁሉ ደግና ከራሱ ይልቅ ለኔ ለልጁ የሚያስብ መስሎህ ነው። ስለዚህ ይቅርታ የሚያስጠይቅ ጉዳይ አይኖርም። ይልቅስ ቶሎ ብለን የሚሻለንን ነገር መፈለግ አለብን። እንዳልኩህ ላስብበት ብዬ የጠየቅሁዋቸው ጊዜ ትንሽ ነው።" አልኩት።

"አንድ ነገር ልጠይቅሽ፣ ምናልባት እንዴት ብትጠረጥር ነው እንዲህ የምትለው ብለሽ እንድትጠይቂኝ ግን አልፈልግም።" አለኝ።

"የፈለግኸውን ጠይቀኝ፤" አልኩት ሊል የፈለገውን ለመስማት በመጓጓት።

"ኤልስዬ መቼም እንዋደዳለን፤ ይህን አልጠራጠርም። እኔና አንቺ ደግሞ እንደልባችን እንዳንሆን ይህ ትልቅ ደንቃራ ተፈጥሮብናል። ይህን ችግር ለመወጣት ቀላል መንገድ የለም። ስለዚህ የምንውስድውን እርምጃ የሚወስነው የፍቅራችን መጠንና እኔ አንቺን፣ አንቺ እኔን ለማግኘት የሚኖረን ጉጉት መጠን ነው። ይህን እርግጥኛ መሆን አለብን" አለኝ።

አባባሉ ልክ ቢሆንም ለምን እንዲህ እንዳለ አልገባኝምና እንዲያብራራልኝ ጠየቅሁት።

"ምን መሰለሽ? የምናደርገው ነገር ሁሉ ከእልህ የመነጨ እንዳይሆን እናረጋግጥ። አንቺም አባቴ እኔ የፈለግሁትን ነገር ለኔ እንዴት አይደርግልኝም በሚል፤ እኔም እንዴት ከማን አንሼ ነው እሷን እንዳላገባ የሚከለክሉኝ ብዬ በማሰብ እንዳይሆን በመፍራት ነው።" አለና እቅፉ ውስጥ ሽጉጥ አደረገና ዓይን ዓይኔን ቁልቁል አየኝ። 'ምናልባት የተናገርኩት አባባል አስቀይሚት ይሆን?' የሚል ፍርሃት ያደረበት ይመስላል።

"ግልጽ ሆነህ ስለጠየቅኸኝ ደስ ብሎኛል። በኔ በኩል ያለውን ልንገርህ፤ ሰይፍዬ እኔ እወድሃለሁ። እልህ ነው እንዳትለው ደግሞ እኔ አንተን መውድድ የጀመርኩት በፊት ገና እቤት ተመልሼ ሳልገባ ጀምሮ ነው። እኔ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነኝ፤ አንተስ?" አልኩና ቀና ብዬ ዓይን ዓይኑን በጉጉት ተመለከትኩ።

ፈገግ አለና አየኝ። "ምን ይመስልሻል?" ብሎ መልሱን እንዳገኘ ሁሉ ጠጋ ብሎ ከንፍሬን ሲስም ተጠመጠምኩበት። "ከአንቺ የሚለየኝ ምንም የለም፣ ካለሞት በስተቀር" አለ በሹክሹክታ መልክ ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብሎ።

"እኔም ሰይፍዬ!" አልኩት በሰለለ ድምጽ። ከጥቂት መሳሳምና ጨዋታ በኋላ እቅዳችንን ማውጣት ጀመርን። ዕቅዳችንንም አወጣን። ያሰብነውን እንዲፈጽምልን ከአልጋው ጎን ተንበርክከን ጸለይን። የፍቅር አምላክ እንዲረዳንም ለመነው።

በዕቅዳችን ያወጣነውን ሁሉ ለመፈጸም ተያይዘንም ለመጥፋት ምንም አልፈራንም። ግን አንድ ትልቅ ችግር ነበረ። ሰይፉ የሚጦራቸው እናቱና የሚያስተምራት እህቱ በምን ሊተዳደሩ? ቀደም ሲል እንደነገርኳችሁ ሰይፉ እየሠራ በሚያመጣው ገንዘብ ነበር እናቱና እህቱ እሱም ጭምር የሚተዳደሩት። ለዚህ መፍትሄ ሳናገኝ ብንሄድ ከባድ የህሊና ጸጸት እንደሚደርስብን ለመገመት አላዳገተንም። የመሄዱ ሁኔታ እንደተወሰነ ሆኖ ለሰይፉ እናትና እህት የሚሆን ነገር ለመተው የመጀመሪያው ዕቅዳችን አደረግነው። በርግጥ ሰይፉ እናቱን ለማሳመን ራሱ ችግር እንዳለበት አልደበቀኝም። እናቱ በጣም ይወዱታል፤ እንዲለያቸውም አይፈልጉም። ለማንኛውም የነሱን ሁኔታ ሳናመቻች ምንም ነገር ማድረግ አልፍልግንም። በዚህ መሠረት ነሱ የሚሆን ነገር ለማበጃጀት የመጀመሪያውን ሥራ ጀመርን። ሰይፉ ከሚሠራበት መሥሪያ ቤት የገባው ዕቁብ ስለነበረ እሱን ለመግዛት ወሰነ። ሁኔታውን ቅርብ ለሆነው ጓደኛው ነግሮት ጓደኛው የሚቀሩትን የአራት ጊዜ ክፍያ እንዲኪፍልለት ማድረግ እንደሚችል ነገረኝ። ሰይፉ ጠንቃቃ ስለነበረ ትንሽ ያጠራቀመው

ገንዘብ ስለነበረ ያንንም ሊተውላቸው እንሚችል አስረዳኝ። በዚህም በዚያም ተደማምሮ አንድ ሶስት ሺህ ብር ያህል ሊተውላቸው እንደሚችልና ከዚያም ከተቸገሩ እኅቱ የናቱ ወንድም ምንም የራሱ ቤተሰብና ሃላፊነት ቢኖረው ሲቸገሩ አይቶ ዝም እንደማይል ነገረኝ። እኛ ውጪ ወጥተን ከተደላደልን በኋላ የሱን እህት ለማስወጣት ተስማማን። ለማንኛውም ጊዜው እስኪቃራብ ድረስ ለሷም ሆነ ለእናቱ ነገሩን ላለመንገር ወሰንን።

ይህን ሁሉ የምነግራችሁ ምክንያት ቢኖሮኝ ነው። በኔና በሰይፉ መሀል ያለው ፍቅር እንዳው ተራ ዓይነቱ እንዳልሆነና ብዙ መስዋዕት የከፈለበት መሆኑን ለማስረዳት ስለሆነ ታሪኬ እየረዘመ የተንዛዛ ቢመስላችሁም በጽሞና ተከታተሉኝ።

ከሰይፉ ጋር በዚህ መልክ ዕቅዳችንን ነድፈን በእሱ በኩል የሚደረገውን ዝግጅት ነግሬአችሁዋለሁ። በአንቺስ በኩል ልትሉ ትችላላችሁ። እኔማ ያቀድኩት ነገር አለ።

ቀደም ሲል ለእናቴ ትንሽ ጊዜ ስጡኝ ብያት እንደነበር አጫውቼአችሁዋለሁ። ማለቴ ተከስተ ሽማግሌ ላከ ስለተባለው ጉዳይ። እና ይህ ሁኔታ ለኔ ጥሩ አጋጣሚ የሚፈጥርልኝ መሆኑ ጉልህ ሆኖ ታየኝ። ለመጥፋት ታስባለች ብለው እንዳይገምቱ እንደገና ጠባዬን መለወጥ አስፈለገ። በቀጥታ ተከስተ ለጠየቀው ጥያቄ እሺ ባልልም የምል ለመምሰል ሞከርኩ። መቼም ሴት ነኝና ስትግደረደር ነው ብለው እንዲያስቡ ለማድረግ ጊዜ አልፍጀብኝም። በተለይ አባቴን ቀዝቀዝ ማድረግ ነበረብኝ። እና አልፎ አልፎ መደብሩ ውስጥ ነገሩ በአንዳንድ ምክንያት ከተነሳ መሽኮርመም ጀመርኩ። እንደድሮው በመቆጣት ፋንታ አባቴ እንደ ቀልድም እንደምርም ሁኔታውን ካነሳ ያፈርኩ መስዬ ለመታየት ሞከርኩ። ዓላማዬም የተሳካልኝ መሰለኝ። አባቴም በሁኔታዬ መመለስ ደስ ብሎት ብዙ ነገር ቃል ገባልኝ። የራሴ የሆነ የንግድ ሥራ እንደሚከፍትልኝ፣ ቤትም ገዝቶ እንደሚሰጠኝ፣ ብቻ ምን አለፋችሁ የተስፋ መዓት አዥጎደጎደልኝ። እኔም ጥቂት ጊዜ የተግደረደርኩ መሰልኩና "ቶሎ አታቻኩሉኝ እንጂ እሺ፤ ሰውዬውንም ልወቀው በደምብ።" አልኩኝ። አባቴ በጣም ተደሰተ። "ቁምነገረኛ ልጅ ብትሆኝ ነው እንዲህ ያሰብሽው፤ ልክ ነሽ፣ ሰውዬውን በደምብ ልመጅው፤" አለኝ። አሁን ሁሉ ነገር እየተሳካልኝ፣ አባቴም ክትትሉን እያላላልኝ መጣ። አባቴም ሙሉ በሙሉ እንዲያምነኝ ለማድረግ ጥረቴን ቀጠልኩ። የፈለግሁትን ነገር ማድረግ እንድችል ሁሉ እየሆነልኝ መጣ። እንግዲህ እንደነገርኳችሁ አንድም አባቴን ለማዘናጋት ሲሆን ከሁሉ በላይ ደግሞ ሌላ የፈለግሁት ጉዳይ ነበረ። ሰይፍዬ ለኔ ሲል ሥራውን፣ እናቱንና እህቱን ጥሎ ያለ የሌለ ንብረቱን ትቶ ሊጠፋ ሲወስን በኔ በኩልስ ምን ማድረግ የሚኖርብኝ ይመስላችሁዋል። ለሰይፉስ እናትና እህት ሶስት ሺህ ብር ምን ያህል ሊያኖራቸው? እኛስ ብንሆን ስንጠፋ ለስንቅና ለመቋቋሚያ አያስፈልገንም ብላችሁ ነው? እንግዲህ ከአንድ የሳር ቤት ጥቂት ሳር ቢመዘዝ ቤቱ አያፈስምና አባቴን ጠባዬን ቀይሬ፤ ተለሳልሼ እንዲያምነኝ አድርጌ በኔ ላይ ያለውን አመለካከቱን እንዲቀይር የጣርኩበት ሁለተኛው ምክንያቴ ግልጽ ሳይሆንላችሁ አይቀርም።

(በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል)

ውድ አንባብያን

"ዕጣዬ" በተሰኘ ርዕስ፤ አብረኸት (የብዕር ስሟ ነው) በኑሮዋ የገጠማትን ታሪክ በተከታታይ እያቀረበችልን ነው። ይህን አሳዛኝ የኑሮ ታሪክ ለአንባብያን እንዲጥም አድርግን ከማቅርብ በቀር የጨመርነው ወይም የቀነስነው ነገር የለም። እሷ አሁን ያለችው አሜሪካን ሲሆን ያለችበትን ቦታ በእሷ ጥያቄ ከማቅረብ ተቆጥበናል።

## ወይዘሪት እስናቀች ገላው



ከአባቷ ከአቶ ገላው አበጋዝና ከእናቷ ከወይዘሮ ሸዋረገድ ገብረጻድቅ አዲስ አበባ ተወልዳ ታድጋለች። የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን አጠናቅቃ ንግድ ሥራ ትምህርት ቤት ገብታ ተመርቃ አዲስ አበባ በአንድ የውጭ ንግድ ድርጅት ተቀጥራ ሠርታለች። ከህፃንነቷ ጀምሮ ባደረባት የልብ ህመም ምክንያት ለህክምና ወደ ሺካጎ መጥታ ለአንድ ዓመት ያህል ስትረዳ ቆይታ ስላልተሻላት August 17, 1994 ከዚህ ዓለም በሞት ተለየችኝ። አስከሬኗም ወደ አገር ቤት ተልኳል። ለአገሯና ለወገኗ ያላት ፍቅር ከፍተኛ እንደነበረና ጸባየ ለስላሳ፣ ትሁትና እግዚአብሄርን ፈሪ እንደሆነች የሚያውቋት ሁሉ ይናገራሉ። በህመሟ ጊዜ በመጠየቅና በማስታመም ስታርፍም አስከሬኗ ወደ ኢትዮጵይ እንዲሄድ በመርዳት ለተባበሩንና የህዘናችን ተካፋይ በመሆን ላስተዛዘኑን ለቺካጎ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን ጥልቅ የሆነ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

ቤተሰቦቿና ጓደኞቿ

# ባላገርና ፓለቲካ

(ከአለፈው የቀጠለ)

ባለፈው ዕትም የባላገሩን ኑሮና ብሶት እንስተን ተጨዋውተን የደርግ መንግሥት እየተሸነፈ ወደ ኋላ በማፈግፈግ ላይ በነበረበት ወቅት አገሬው ራሱንና ክብቱን እንዲጠብቅ እርስ በእርሱ ሲላላክ የነበረውን መልዕክት አቅርበን ነበር የተለያየነው። . . . ባላገሩ ቢጮህ የሚሰማው ጠፍቶ፣ አቤት ቢል የሚዳኘው አጥቶ፣ ቢመክር ቁምነገር የሚለው ሳያገኝ ቀረና ከመንግሥት ጋር ሆድና ጀርባ ሆነ። በመንግሥት ሹሞች ላይ ጥላቻም ንቀትም አደረበት። ለመንግሥት ውድቀት ለሹሞቹም ውርደትን ይመኝ ጀመር። መንግሥት በሚያወጣው መመሪያና ትዕዛዝ ላይ ሲመቸው አሻፈረኝ ማለት ጀምሯል። ሳይመቸው ሲቀር ደግሞ እየለገመ ማስቸገር ይዟል። . . . በዚህ ሁሉ መሃል ደግሞ መንግሥት የሀገር ጉዳይ፣ የነፃነት ነገር እያነሣ ባላገሩን ድረስልኝ ይላል። ወያኔ ተረማምዶ እንዳይመጣበት ገድበህ ያዝልኝ ብሎ ይወተውታል። የጽሁፌ ዋና ዓላማ የትኛውንም ወገን ለማንኳሰስ ወይም ለማሞገስ ሳይሆን ጊዜ የሰጠው ፖለቲከኛ የአገሬን ባላገር ሳያማክር የሚያወጣው ፖሊሲ ባላገሩን እርስ በእርስ አጋጭቶ የድሃ ጎጆውን አናግቶ ለራሱም ለባለጊዜውም መጥፊያ መሆኑን ለማሳዬት ነው።

መንግሥት ያወጣቸው ፖሊሲዎች በሙሉ ማለት ይቻላል አፈጻጸማቸው ባላገሩ እንዲወዳቸው ሳይሆን የሚገደድባቸው ነበሩ። . . . የገበሬው ኑሮ የተመሠረተበት የእርሻ መሬት አከፋፈል የባላገሩን ወሽመጥ ቆርጦት ነበር። ገበሬው ራሱ በመረጣቸው ኮሚቴዎች አድልዎ እየተፈፀመበት ብዙው ገበሬ ጠሙን አዳሪ ሆኗል። ደህና ደህናው መሬት የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለማበረታታት ለአምራቾች ተሰጥቷል። የቀረው በጉቦ በአምቻና በጋብቻ ለተመራረጡ ሰዎች ተደልድሏል። ባላገር መንግሥትና ሹመኞቹን መናቅም መጥላትም ጀመረ። እንዲህም ሲል በዜማ ብሶቱን ገልጿል።

ምን ያለ ጊዜ ነው የጊዜ ጨብራራ፣
ዓይን ያለው ቁጭ ብሎ ዕውር እየመራ።
ምን ዓይነት ጊዜ ነው የጊዜ ቁርንጮ፣
ወልዶ ለዘመቻ ሰርቶ ለመዋጮ።

እያለ ዘመነኞቹንና ዘመኑን ማብጠልጠል ጀመረ።

የገበሬ ማኅበር የኮሚቴ አባላት በፓርቲው ድርጅታዊ አሠራር የሚመረጡ ናቸው። በዚህ ሁኔታ ሥልጣን የሚያገኙ ሰዎች ደግሞ በአምቻ በጋብቻ አድልዎ በተሞላባት አሠራር የለም መሬት፣ የውኃ ገብ እርሻ ማሣ ባለቤቶች ሆነዋል።

የኮሚቴ ዘመድ ከቶ ምንጎድሎበት፣
በእጁ ገብቶለታል ውኃ ገቡ መሬት።
ወንድም ሊቀመንበር የተሾመላችሁ፣
አማች ፍርድ ሸንጎ የተሾመላችሁ፣
መሬት በዓይን ስፍር የተለካላችሁ፣
ድምብል ድምብል መሬት የተለካላችሁ፣
እረሱት እርሱት እንዳደረሳችሁ።

በማለት ባላገሩ በተደረገው የአድልዎ ሥራ መብገኑን ገልጿል። ለኮሚቴ ተመራጮች የሚከፍለው ጉቦ የሚያበላው ነገር ያልነበረው ባላገር በደሉ በዛበት፣ የእርሻ ማሣ ተነፈገ፣ ምርት የማይሰጥ የተጋጠ ማሣ ላይ ተጣለ፣ ድህነት ከፋበት።

ለሊቀመንበሩ እምሰጠው አጥቼ፣
ለሰባት ኮሚቴ የምሰጠው አጥቼ፣
ያለ እሸት ከረሙ የድሃ ልጆቼ።
ያልሞትኩ መስሏችኋል ሬሳዬ ያልወጣ፣
ከቤቴ ባድማ እሸት መዝሪያ ሳጣ።
አረቄ ያልቀዳ፣
ቡና ያላፈላ ያልቆረሰ ቁርስ፣
ቦዳ ተቀበለ እንደሙታን ልብስ፣
እንዲያው ዝም ብሎ ቁጭ ብሎ ያልቅስ።
ወይ ዘመድ በኖረኝ ወይ አማች በኖረኝ፣
ወይ ቅቤ በኖረኝ፣ ወይ ማር በኖረኝ፣
እንደዚህ ተጥዬ ወድቄ አልገኝ።
ዘንግቼ ነው እንጂ እጅግ ተሳስቼ፣
የሊቀመንበሩ አማች መሆን ትቼ።

እያለ የሚፈፀምበትን አድልዎ፣ የሚደርስበትን በደል በለቅሶ፣ በዘፈን፣ በሙሾ፣ በፉከራ፣ በየሠርጉ ላይ፣ በየለቅሶው ላይ፣ በየአውደዓመቱ፣ በየክብረበዓሉ አጋጣሚ አንጎራጉሯል።

የባላገሩን ብሶት ከእንጉርጉሮው የተረዳለት አልነበረም። ብዙ የእግር መንገድ ተጉዞ ለትልልቁ ሹም አቤት ቢልም የሚፈርድ ዳኛ፣ ነገር የሚቆርጥ ሹም አልተገኘም። ዝም እንዳይባል ደግሞ የመኖር የመሞት ጥያቄ ሆነ። ባላገሩ አጣብቂኝ ገባ። ልቡ ቂም ቋጠረ። የመንግሥትን ሹም እንደአምላክ መፍራቱ ቀረና ይዘልፍ ጀመር። እንዲህ እያለ:-

ኢሠፓውም ዕውር ኮሚቴውም ዕውር፣
አውራጃውም ዕውር ወረዳውም ዕውር፣
ሁሉም ዕውር ናቸው፣
ድሃ ሲያለቅስ አይተው ዝም ማለታቸው።
ፍርድ ሸንጎው ጋራ ሊቀመንበር ገደል፣
የሚሰማው ጠፋ የገበሬን በደል።

ባላገር ዙሪያ ገባው ገደል ሆነበት። በአንድ ፊት የራሱ ተመራጮች ይበድሉታል። አቤት ቢልም የሚፈርድለት ዳኛ አጥቷል። ዘመኑን እየተራገመ ኑሮውን እያማረረ ይህ ቀን እንዲያልፍለት አምላኩን ይማፀን ጀመር።

ሊቀመንበሩ አምጣ፣ ፀሐፊውም አምጣ፣
ኢሠፓውም አምጣ፣ ኮሚቴውም አምጣ፣
ድሃን የጨነቀው እንዲህ ዓይነት ጣጣ፣
ዳግም መወለድ ነው፣ ይህን ቀን የወጣ።
የአሣማ ኮሚቴ
የጅብ ሊቀመንበር የጦጣ ፀሐፊ፣
አረ ተይ አንቺ ቀን ቶሎ ቶሎ እለፊ።

እያለ ይህ ቀን እንዲያልፍለት ደ'. ቀን እንዲመጣ ተማጽኗል።

የባላገሩ ብሶትና ምሬት በአንድና በሁለት የመንግስት ፖሊሲዎች ላይ አልነበረም። በሁሉም ፖሊሲዎች አፈጻጸም ላይ አላማከሩትም። እንዲወደው አላደረጉትም። የገበሬውን ሕይወት ሊያሻሽሉ ይችሉ የነበሩት ፖሊሲዎች እንኳ በግዳጅ እንዲፈጸሙ በመደረጉ ባላገሩ በመንግሥት ላይ ቂም ይዞ ነበር።

በአለም አቀፍ ደረጃ የተደነቀው የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ እንኳ የባላገሩ ስሞታ ነበረበት። ጠልቶትም ነበር። ምክንያቱም የትምህርት ፕሮግራሙ ከገበሬው የሥራ ጊዜ ጋር አይጣጣምም ነበር። በሞት የሽረት የአዝመራ ወቅት እንደሌላው ጊዜ ሁሉ ገበሬው መሠረተ ትምህርት እንዲማር ተደረገ። የተዘራውን እህል ወፍና አሞራ ለቀመው። በቡቃያነቱ ከብት ጋጠው። አሮጊት፣ ሽማግሌው፣ ልጅ አዋቂው ሁሉም በጅምላ ተማሪ ሆነና የሚጠብቅ ጠፋ። ከብቶች የሚያስማራ፣ አጣቂ የሚባል ቅጠል በልተው እንዳይሞቱ የሚጠብቅ እረኛ ከመሠረተ ትምህርቱ እስኪመለስ ከብቶች ከበረት አረፈዱ። ከመሠረተ ትምህርት መቅረት ደግሞ ያስቀጣል። ያሳስራል። ባላገሩ እንዲህ ሲል ብሶቱን ገልጿል።

ከትምህርቱ ሁሉ ትንሽ የቀረችሁ፣
ካለእህል የቆመ ከቶ ማን አያችሁ፣
ከብት አጣቂ በላ ቡቃያው ተጋጠ፣
ምን መንግሥት ይገኛል ከእህል የበለጠ።
ክረምት እየመጣ ጤፍ እንደመዝራት፣
አዝመራ ደርሶ ማሽላ እንደመዝራት፣
ሰኔ ግም ብሎ ዳጉሣ እንደመዝራት፣
በሮች ተፈትተው ዋልን ተማሪ ቤት።

እያለ ችግሩን በዘፈን፣ በእንጉርጉሮ፣ በለቅሶ፣ በፉከራ ለባለጊዜዎች አሰማ። አቤት አለ። መፍትሄ ነው ያለውንም በዚያ አጋጣሚ በግጥም እንዲህ አለ።

እንፈልግ ነበረ መማሩንስ እኛ፣
ብንፈልግ አጥተን ነው ከእህል በላይ ዳኛ።
ብርቱ ብርቱው ይማር ደካማውም ይቅር፣
ተስማምቶ አይደለም ወይ ሲኖሩ በአገር።

ብሎ መከረ። ምን ተበደላችሁ ያለ አልነበረም፣ የሚሰማም ጠፋ።

መሠረተ ትምህርት በአዝመራ ወቅት እንቅፋት መሆኑ ብቻ ሳይሆን ለመሠረተ ትምህርት ዘመቻው የሚመጡትን ዘማች መምህራን መቀለብ ግዴታ ነበረበት።

ገበሬ በዓመት አንዴ ከሚያገኛት የእርሻ ምርት ለእርሻ ሰብል ኮታ ከፍሎ፣ ግብር ከፍሎ፣ የእናት አገር ልዩ መዋጮ አዋጥቶ፣ የገበሬ ማኅበር፣ የወጣቶች ማኅበር፣ የሴቶች ማኅበር የአባልነት ከፍሎ፣ ማሕበር ደግሶ፣ ሰንበቴ አውጥቶ፣ ለዕድር፣ ለቤተክርስቲያን አስራት ከፍሎ፣ ከዚያው ላይ ቀለብ ተሰፍሮ፣ ለዓመት ልብስ ተሸምቶ፣ ለዘር ሆኖ፣ ለመሠረተ ትምህርት ዘመቻ የሚመጣውን ብዙ ጎረምሣ መቀለብ ደግሞ ተጨማሪ ሸክም ነበር። ገበሬው ምሬቱን እንዲህ ሲል ገልጿል።

አሥራት ከፍዬ መኢገማ ቀርቶኛል፣
መኢገማን ከፍዬ አኢወማ ቀርቶኛል፣
አኢወማን ከፍዬ አኢሴማ ቀርቶኛል፣
አኢሴማን ከፍዬ እርሻ ሰብል ቀርቶኛል፣
ለሁሉም ከፍዬ አንድ ብር ቀርታኝ፣
ጨው አምሮኝ ልበላ አይኔ ሲቅለበለብ፣
ያቺንም ወሰደች ለዘማቹ ቀለብ።

በማለት በደሉን አንጎራጎረ። የልቡን ምሬት ሙሾ አወረደበት። የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ በየጊዜው በመንግሥት ግምገማ ይደረግበት ስለነበር ይህን የገበሬውን ሮሮ ከቁምነገር የጣፈ አልተገኘም። የሰማ አልነበረም።

በደርግ መውድቂያ አካባቢ ክሊኒኮችና ወፍጮ ቤቶች ሳይቀሩ በገበሬው በራሱ የተቃጠሉበትና የተዘረፉበት አጋጣሚዎች በርካታ ነበሩ። እነዚህ የአገልግሎት መስጫ ተቋሞች ብዙዎቹ ከመንግስትና ከዓለም ባንክ በዕርዳታ የተገኙ ነበሩ። እነዚህ ተቋሞች ባላገሩ እንደሚጠቅሙት ያውቃል። ነገር ግን ለግምገማ፣ ለጉብኝት፣ እያለ በስቴሽን ዋገን እየጋለበ እንደደራሽ ጎርፍ የሚመጣውን ባለጊዜ ማስተናገዱ፣ እነርሱን ተሰልፎ መጠበቁ፣ ለእነርሱ ማደግደጉ እጅግ እየከበደው መጥቶ ነበር።

ደርግ ቅይጥ ኢኮኖሚ እንዳወጀ፣ በአምራቾች የኅብረት ሥራ እንደሞዴል በሚታየው ጎጃም እንዲህ ሆነ። በ1982 መጨረሻ በጎጃም በአንደኛው አውራጃ ውስጥ ባላገሩ በጠራራ ፀሐይ ወጥቶ ክሊኒኩን እያፈራረሰ ቆርቆሮውንና አጣናውን ይከፋፈላል። ወፍጮውን እየቀጠቀጠ ሰባብሮ ቁርጥራጭ ብረቶችን፣ ቼንጋውን፣ ቋቱን፣ ቆርቆሮውን እንደደረሰው ድርሻ ድርሻውን ይከፋፈላል። የአውራጃው የኢሠፓ ሹማምንትና የመንግሥት ባለስልጣኖች ነገሩን ቢሰሙትም ቀርበው ማስቆም አልደፈሩም። ይህ ከመሆኑ ከጥቂት ሳምንታት በፊት ጎጃም ቢቸና አካባቢ መንደር ምስረታን እያፈረሰ ወደ ቀድሞው ቀዬው በመመለስ ላይ የነበረን ገበሬ ለማስቆም የተላኩት ፖሊሶች ከእነአለቃቸው ተገድለው ነበረና ባላገሩ መፈራት ጀምሯል። ከእራሱ መካከል ጎበዝ አለቃ እየመረጠ ባላገሩ ሲማማል መክረሙን ያውቁታል።

(ወደ ገጽ 43 ይዞራል)



# የአበው ቅርስ



## እንቆቅልሽ . . . ምን አውቅልሽ !!

እንቆቅልሽ በመኖሪያ ቤትም ይሁን በመዝናኛ ቦታ በሰዎች መካከል በጥያቄና መልስ መልክ የረቀቀና የተደበቀን ሚስጢር ያዘለ በምልልስ መልክ የሚቀርብ የጥያቄና የመልስ ጨዋታ ነው። ጠያቂው በአካባቢው ባሉት ነገሮች በአንደኛው አስመስሎ ሲጠይቅ ተጠያቂው ደግሞ ትርጉም የሚሆኑትን ነገሮች ተመስለው ከቀረቡት ምሳሌዎች አንፃር እየተመለከተ ፍቺውን ለመስጠት ይሞክራል።

ጠያቂው አንድ ፍቺው ያልታወቀ መመራመርን የሚጠይቅ ጥያቄ ለመጠየቅ እንደፈለገ ለማሳወቅ "እንቆቅልህ?" በማለት ለተጠያቂው ያሳውቃል። ተጠያቂውም "ምን አውቅልህ!" ሲል ለጥያቄው መዘጋጀቱን ያሳውቃል። ጠያቂውም እንቆቅልሹን እንዳቀረበ ቶሎ መልስ ለማግኘት ወይም ተጠያቂው አላወቅሁትም ተረትቻለሁ እንዲል

ዋለብህ አደረብህ
ሰርዶ በቀለብህ
እንቆቅልሼ ጠነዛብህ
እያለ ያዋክበዋል።

ተጠያቂውም

"ዋለብህ አደረብህ፣ ሰርዶ በቀለብህ ባትለኝ
እንደሳምሶን ቀን ስጠኝ፣"

በማለት ለቀረበው እንቆቅልሽ ፍቺውን ፍለጋ ይቀጥላል።

ተጠያቂው እንቆቅልሹን መፍታት ካልቻለ የማሰብ ኃይሉ ዝቅተኛ እንደሆነ ተቆጥሮ ጠያቂው "የምገዛው አገር ስጠኝ" ይለዋል። ተጠያቂውም ለእንቆቅልሹ መልስ ለመስጠት አለመቻሉን ሲረዳው የሚያውቃቸውን ከተሞችና አካባቢዎች አንዱን ጠርቶ "እከሌ" የሚባለውን ሀገር ሰጥቼሃለሁ ሲል መሸነፉን ለጠያቂው ያሳውቃል። ጠያቂው የተሰጠውን ሀገር በመናቅ አልወስድም ሲል ይግደረደራል። የተሰጠውንም ሀገር ተቀብያለሁ ካለም ጠያቂውን እንዲህ እያለ ይወርፈዋል።

በሰጠኸኝ አገር ተቀምጬ፣
ምን አጥቼ፣
እኔ ጌታ ሆኜ፣
አንተን አሽከር አድርጌ፣
ሠጋር በቅሎዬን ጭኜ፣
አንተን ከኋላዬ አስከትዬ፣
በቅሎዬ ስትሠግር፣
አብረሃት እስር እስር ባትበር፣
በአለንጋ ጆሮ ጆሮህን፣
በሰጠኸኝ አገር ተቀምጬ፣
ምን አጥቼ፣
ሠላሳ ጥማድ አስጠምጄ፣
ኩዳዱን አሳርሼ፣
የእከሌን ተራራ የሚያህል ምርት አስመርቼ፣
ምርት ምርቱን ለራሴ፣
እንተራዬ ከትቼ

ግርድ ግርዱን ለአንተና ለበቅሎዬ እሰጣችኋለሁ፣
ለክረምት መውጫችሁ።
እያለ የቻለውን ያህል ተጠያቂውን እየወረፈና እያንኳሰሰ ይሰድበዋል።

ከሰደበውም በኋላ መልሱን ይነግረዋል። ቀጥሎ ተጠያቂው የጠያቂነት ተራ ይሰጠዋል። እሱም እንቆቅልሽ ጠይቆ ተጠያቂው እንደርሱው ሊመልስለት ካልቻለ በመሰደብና በማንኳሰስ ብድሩን ይመልሳል።

ዕንቆቅልሽ በገጠር ከሥራ መልስ ልጆች ምድጃ ስር ከበብ ብለው እሣት እየሞቁ በመጠያየቅ የጊዜ ማሳለፊያ ያደርጉታል። አዋቂዎችም አልፎ አልፎ በመሸታ ቤትና በሸንጎ ሥፍራ በመጠያየቅ ይመላለሱበታል። በተዘዋዋሪ መንገድ ትምህርት መስጫ ዘዴ ነው።

ጠያቂ : እንቆቅልህ?
ተጠያቂ : ምን አውቅልህ?
ጠያቂ : ወንድሙን ወንድሙ ይዞ የሚያስመታ እወቅልኝ።
ተጠያቂ : እኔ እንደአንተ ውርርድ አልሻ

ያኸውም ጉጠት (ፒንሣ) ነው። መቺውም መዶሻ ሲል ይመልሳል። መልሱን ያወቀ ስለሆነ አገር አይሰጥም። አይሰደብም።

እስቲ እንግዲህ እኛም እንቆቅልሽ እንበላችሁ።

እንቆቅልሽ! . . . የድንጋይ ንጉሥ የቅጠል ትኩስ እወቁልኝ።

መልሱን እንድትልኩልን ወይም አገር እንድትሰጡን እንፈልጋለን።
(ከፊል ምንጭ ከአቶ ተሰማ መርሻ ጥናታዊ ጽሁፍ የተወሰደ)

## ጥንት የሆነ

(ከዓለማየሁ ሞገስ መጽሐፍ የተቀበጨበ)

ዐፄ ምኒልክ ወደ አድዋ ሲዘምቱ አዝማሪ ተከልክሎ ነበር ይባላል። አንድ የጉጃም አዝማሪ የሚከተለውን ግጥም ስለገጠመ ተከትሎ እንዲሄድ ተፈቀደለት ይባላል።

ምኒልክ ተጉዞ የሚጠይቁኝ፣
ፊትም አላለፈም ኋላም አይገኝ። አለ።

ኋላም ጦርነቱ ላይ የሚከተለውን ገጠመ።

ዐድዋ ሥላሴን ጣልያን አረከሰው፣
ገበየሁ በሞቴ ተሻግረህ ቀድሰው።
አሳኔ ከበሩ ሲወድቅ ማጅር፣
እንደ ግራኝ ሁሉ በ7 ዓረር።

ባልቻ በመትረየስ ነጥሎ ሲጥል፣
አባተ በመድፉ አምሳ ሲገድል፣
የጉጃሙ ንጉሥ ግፋ በለው ሲል።
እቴጌ ጣይቱ እቴጌ ብርሃን፣
ዳዊት ዘርግታ ስምዐኒ ስትል፤
ባስበዙቅ ተጨንቆ ውሃ ውሃ ሲል፣
ዳኛው ስጠው አለ ሠላሳ በርሜል።

## ባላገርና ፖለቲካ . . . (ከገጽ 40 የዞረ)

ነገር ግን ሁኔታውን እንዲሰልልና እንዲያጣራ ሹሞቹ አንድ የአካባቢውን አዛውንት ይልካሉ። አዛውንቱ ከስፍራው ሲደርሱ የአገሬው ባላገር ልጅ አዋቂው፣ ሴት ወንዱ ወጥቶ ክሊኒኩን አፈራርሰው ጨርሰዋል። ወፍጮውን ቀጥቅጠው ሰባብረው አጠናቀዋል። መሠረተ ትምህርት የሚማሩበትንና የሚሰበሰቡበትን አዳራሽ ይዘው ይንዱታል። ገሚሱ ጣራውን ይነቅላል፣ ገሚሱ ግርግዳውን ያፈርሳል፣ ገሚሱ የመሰረት ድንጋዩን ይፈነቅላል፣ ገሚሱ ደግሞ ፍራሹን እንደቅርጫ ስጋ በመደብ በመደብ እያደረገ ያከፋፍላል። የጎበዝ አለቆችና ሽማግሌዎች ፈንጠር ብለው ቆመው ሁኔታውን በዕርጋታ እየተመለከቱ ያስተባብራሉ። ነገሩን እንዲያጣሩ የተላኩት አዛውንት ፈራ ተባ እያሉ ቀስ ብለው ወደ ጎበዝ አለቆችና ወደ ሽማግሌዎቹ ጠጋ ብለው ሰላምታ ከሰጡ በኋላ

"ምነው ጎበዝ?" አሉ።

"ምን አጠፋን ጌታው? እኛው ሰራነው እኛው አፈረስነው" ሲሉ ሽማግሌዎቹ ይመልሳሉ።

"የት ልትሰበሰቡ ነው አዳራሹን የምታፈርሱት" ይላሉ አዛውንቱ መልሰው

"ግዴለም ከደብር እንሰበሰባለን" ይላሉ የጎበዝ አለቆችና ሽማግሌዎች። ነገሩን እንዲሰልሉ ባለስልጣኖች የላኩዋቸው መሆኑን ተረድተዋል። ገብቶአቸዋል። በኋላም ያፈራረሱትን ሁሉ አዙረው ለአዛውንቱ ያሳዩዋቸውና:-

"እንግዲህ ለእኛም ይላኩልን። ለኢሠፓውም ለአውራጃውም ይንገሩልን። እኛው እንደሰራነው እኛው አፍርሰነዋል። ክሊኒኩም ፈርሷል፣ ወፍጮ ቤቱም ተነቅሏል፣ አዳራሹም ተንዷል፣ የተቀሩትንም ሰሞኑን እናነሳለን። ስለዚህ የሚያስጎበኙት፣ የሚገመግሙት እንዳች የለምና እንዳይደርሱብን።

ለስብሳቦሽ ከፈለጉን የሚካኤል ዕለት ከደብር ተሰብስበን እንቆያችኋለን። ብሏል አገሬው ብለው ይንገሩልን።" በማለት አዛውንቱን መልሰው ለባለስልጣኖቹ ይልኳቸዋል። ባላገር ስብሰባን ስብሳቦሽ ብሎ ነው የሚጠራው። የአካባቢው ቤተክርስቲያንን ሚካኤል ከሆነ በዚያ ዕለት አገሬው ስራ አይሰራም። ከፈለጋችሁን የሚካኤል ዕለት ከደብር ታገኙናላችሁ ማለቱም ስራ የማይኖረን ያን ዕለት ነው ማለቱ ነው። day-off መሆኑ ነው።
በዚህ ሁሉ መሃል እየገፋ ያለውን የወያኔ ጦርና በመተከል አካባቢ ወጣ ገባ እያለ ጥቃት የሚያደርሰውን የኢሕአፓ ሰራዊት ባላገሩ እንዲመክት የመንግስት ባለስልጣኖች ላይ ታች ይላሉ። ስለአገር መደፈር፣ ስለነፃነት መገሰስ ይሰብካሉ። ባላገሩ ደግሞ በዚች አጋጣሚ ጠመንጃ እንዲሰጠው መሳሪያ እስታጥቁን እንጂ ግድየለም እያለ ባለስልጣኖችን ያሞኛቸዋል።

መንግስት ለጥቅሙ የጎበዝ አለቆችን ለማስጠጋት ሞከረ። ባላገርም የመንግስት ሹምም ሁለቱም በየልባቸው ለሚያቁት ጥቅም ተቀራረቡ። ግራ የገባው ሹመኛ መጋዘን እየከፈተ መሳሪያ ያድላል፣ ጥይት ያከፋፍላል፣ ወያኔ እልፎ እንዳይመጣ በየቀበሌያችሁ በጎበዝ አለቃ ገድባችሁ ያዙ እያለ ይወተውታል። ጠጉረ-ልውጥ ሰው ከታዬ ይዘው ማንነቱን እንዲያጣሩ ይመክራል። ያስጠነቅቃል። ባላገር ደግሞ ተማምሎ "መንግስትና አልጋ እየፈረሰ ነውና ከብትህንና ድጅህን ጠብቅ" ተባብሏል። የመንግስት ሹሞች የሚያድሉትን መሳሪያ እጁ ካስገባ በኋላ እንዲህ ይል ነበር።

ደርግም ብሎ ነበር ኢሕአዴግን ምቱ፣
ጀኔራልም አሉ ወያኔን መክቱ፣
ኢሠፓም አዘዘ ፀጉረ ልውጥ ምቱ፣
ታድያ ምን ያደርጋል
ፈራች ጠረጠረች እምቢ አለች ልቢቱ።

በማለት የባላገሩ ልብ ከመንግስት ጋር አለመሆኑን ግልጽ አደርጓል።

በተለይም ጦርነት ይካሄድባቸው በነበሩት የወሎና የጎንደር አውራጃዎች ውስጥ ገና ጦርነቱ ሳይጀምር ባለስልጣኖችና የጦር አዛዦች ሰራዊቱንና ሕዝቡን ጥለው ይሸሹ ስለነበር ባላገሩ :-

አረ እነ ኢሠፓ መላም የሌላቸው፣
አረ እነ ጀኔራል መላም የሌላቸው፣
እነ ውል የለሽ፣
አንድ ጥይት ሲጮህ ይላሉ እንሽሽ።

በማለት ባላገሩ የመንግስት ሹሞች የሚሉትን አምኖ ከእነሱ ጎን ቆሞ እንደማይዋጋ ገለጠላቸዋል። ይልቁንም ሲበደል ያልተመለከቱት አቤት ብሎ ያልፈረዱለት የመንግስት ሹማምንት የጦርነትን ጭንቅ የጥይትን ስቃይ እንዲቀምሱት:-

የመንጌ አማካሪዎች
ኢሕዲሪ ኢሠፓ የምትባሉቱ፣
ኮሚሣር፣ ኮሎኔል፣ ሻለቃ፣
ጀኔራል የምትባሉቱ፣
እነ እንቁላል ቁርሱ
እነ ዶሮ ምሳው፣ እነ በግ እራቱ፣
እነ ብር ትራሱ፣ እነ ፍሪዳ እረዱ፣
እነ ውስኪ ቅዱ፣ እነ ጮማ አምጡ፣
ጥይቷንም ቅመሷት እንደጮማይቱ፣ እንደመጠጢቱ

በማለት የሚመኙላቸውን ያሳውቃቸው ጀመር። የደርግ የመጨረሻው ዘመን ተቃረበ።

---

(ባላገሩ በደርግ መንግሥት በወያኔና አሁን በሥልጣን ላይ ባለው የሽግግር መንግሥት ላይ ያለውን በተከታታይነት እናቀርባለን)




# እስፖርት



## የዘንድሮው የእግር ኳስ ውድድርና ዝግጅቱ

እንዳምናውም እንደካቻምናውም ዘንድሮም ኢትዮጵያውያንን በሰሜን አሜሪካ በአንድ ቦታ ለጥቂት ቀናት የሚያገናኘው የእግር ኳስ ጨዋታ በአትላንታው ቡድን ሻምፒዮናነት ቨርጂኒያ በሚገኘው አሌግዛንደሪያ ከተማ ተጠናቋል። ከJune 26 እስከ July 4 1994 ድረስ በተከናወነው በዚህ ዝግጅት ላይ በአጠቃላይ ከ20,000 ኢትዮጵያውያን በላይ እንደተገኙ ይገመታል።

ከየቦታው የመጣው ኢትዮጵያዊ የአሌግዛንደሪያንና የዲ ሲን ከተሞች አጥለቅልቆት ከተማዎቹ ለጥቂት ቀናት የኢትዮጵያ ከተማ መስለው ታይተው ነበር። ብዙ ጥረት የሚጠይቀውን ይህን ዝግጅት በማቀነባበር የሜሪላንዱ እግር ኳስ ክለብና የሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያውያን እግር ኳስ ፌዴሬሽን ሊመሰገኑና ሊደነቁ ይገባል። ለረዥም ዘመናት ያልተገናኙ ጓደኞሞችና ዘመዳሞች በማገናኘት፤ የአገር የወገን ናፍቆት ናፍቆት ላለበት ስደተኛው ኢትዮጵያዊ ለአፍታም ቢሆን የአገሩን ትዝታ በዓይነ ህሊናው እንዲቃኘውና እንዲጽናና በማድረግ በኩል ይህ ዓመታዊ ዝግጅት የሚጫወተው ሚና በቀላሉ የሚገመት አይደለም። የብዙ ጎሣዎች አገር የሆነችው ኢትዮጵያ ህዝቦቿ በጋራ በሰላምና በፍቅር አንድ ላይ ተሰባስበው ሊኖሩ የሚችሉ መሆናቸውን ለዓለም ህዝብ የምያሳይበት አጋጣሚ ስለሚሰጠው በሰሜን አሜሪካ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ሁሉ በናፍቆቶ የሚጠብቀው ዝግጅት ነው።


ከእግር ኳስ ጨዋታው አንስቶ በሜዳው አካባቢ የሚሸጡት ባህላዊ ዕቃዎችና ምግቦች ጨምሮ እስከ ዝግጅቱ ማክተሚያ ምሽት የሚዘጋጀው የባህልና የሙዚቃ ምሽት ድረስ የሚከናወኑት ተግባራት በየመልካቸው ለዚህ ወገኑና አገሩ ለሚናፍቀው ህዝብ ትልቅ ትርጉም አላቸው። የአገርንና የህዝብን አንድነት የሚያንጸባርቁ ቲ ሸርቶች፤ የተለያዩ የሙዚቃ ካሴቶች፣ ቪዲዮዎች፣ በቆሎና በለጋ ቅቤ ያበደ የጉራጌ ክትፎ፤ የመርካቶውን ትዝታ የሚቀሰቅሰው ፓስቴ፤ የተለያዩ ልብሶች፤ መጽሀፎች፣መጽሄቶች፣ ወዘተ በዚህ ዝግጅት ላይ ለሺያጭ ቀርበዋል። ብዙ ጓዷኞሞችና ዘመዳሞች ተገናኝተዋል።


እንግዲህ ይህን ታላቅ ዝግጅት እያደነቅን፣ አስተባባሪዎቹን ላደረጉት አስተዋጽዖ እያመሰገንን ከተለያዩ ሰዎች ስለዝግጅቱ የተሰጡትን አስተያየቶች እናቀርባለን። ፌዴሬሽኑም በበኩሉ ያለውን አስተያየት እንዲሰጠን እንጋብዛለን። እኛም የምንለውን ከፌዴሬሽኑ መልስ ጋር (ከላከልን) በሚቀጥለው እትም እናቀርባለን።

በደብዳቤና በስልክ የደረሱንን አስትያየቶች አሳጥረን ድግግሞሹን ቀንሰን እናቀርባለን።



ሻምፕዮናው የአትላንታው ቡድን





# ከተላኩልን አስተያየቶች በአጭሩ

✉ ዓላማው ወደር የማይገኝለት በመሆኑ ፌዴሬሽኑን አመሰግናለሁ። አንዳንድ ስህተቶች ቢኖሩ እነኚያን ለማረም ፌዴሬሽኑ ይትጋ። ለዚህ ደግሞ ብዙ ሰው ያሳትፍ።

አልማዝ ከዲ ሲ

*

✉ በየዓመቱ የሚገኘው ገቢ ብዙ ነው ይባላል። ለምን ዓይነት በጎ ተግባር እንደዋለ ወይም እንደሚውል የሚገልጽልን ይኖሮ ይሆን? በየጊዜው ገንዘብ ያዥ የነበሩ እየያዙ ይጠፋሉ ይባላል? ነገሩ እንዴት ነው? ባገሩ ህግ የለም ወይስ "ሌብነቱ" ህጋዊ ሆኖ ነው? ተሰረቀ ሲባልስ ተሰራቂው ማን ነው? እኔ አልገባኝም?

በላይ አ. (ዲ ሲ)

*

✉ ለዘንድሮው ሻምፒዮና ለአትላንታው ቡድን የተሰጠው ዋንጫ ትክክለኛው አይደለም። "The best coach of the year" የሚል ነው ይባላል። ምነው? ዋናው ዋንጫ የት ሄደ?

ጣሰው (ከአትላንታ)

*

✉ በሜዳው አካባቢ የሚታየው የተለያዩ ሸቀጣሸቀጦች ሽያጭ ዓላማው ጥሩ ሆኖ ሳለ ነጋዴዎቹ በተለይ የምግብ ሻጮቹ ዓይን ያወጣ ዘረፋ ነው ያካናወኑት። ይህን ህዝብ እንዝረፍ ብለው የተነሱ ይመስላል። ምነው ፌዴሬሽኑ ቁጥጥር ማድረግ አቃተው ወይስ ከዘረፋው ተካፋይ ነው?

ገረመው አ. (ከቦስተን)

*

✉ በዘንድሮው ዝግጅት በምሽቱ የሙዚቃ ፕሮግራም ላይ የታየው ሁኔታ አሳዝኖኛል። 1ኛ. ብዙ መቀመጫዎች reserved ተብለዋል። ለማን? እንዴት? ገንዘብ ተከፍሎ በሚገባ ዝግጅት ላይ ይህን ማድረግ ህጋዊ ነወይ? 2ኛ የእነ ጥላሁን ገሠሠ ጉዳይ በብዙዎቻችን አጠያያቂ ሆኗል። ማነው ተጠያቂው ዘግይተው ለመምጣታቸው? ለመሆኑ የተጫወቱት በባሮ ባንድ መሣሪያ መሆኑን ያላወቅን መሰላችሁ? የእነ ጥላሁን አመጣጥ እንደመሰለኝ ለመጫወት አልነበረም፤ ለማጋፈጥ ዓይነት ይመስላል? የፌዴሬሽኑ ሰዎች ደግሞ ሌላ ይነግሩናል? ዘፋኞቹስ ደጋግመው "እኛ ተጠያቂ አይደለንም" እያሉ ማውራታቸው አጠራጥሮኛል፤ አንድ ነገር ያለ ይመስላል። የፌዴሬሽኑ ሰዎች ደግሞ ጥላሁን ሊመጣ እንደማይችል ነገሩን። ሁለቱ "ኃያላን" ወፍ አደረጉን ልበል? እኔ እንቆቅልሹን የሚፈታልኝ እፈልጋለሁ።

የቺካጎዎቹ ባሮዎች ነገሩን ለማረጋጋት የከፈሉትን መስዋዕት አውቀናል፤ ከቺካጎ ስለሆንኩ አዳላህ ባትሉኝ ስለጥረታቸው ላመስግን። በሉ መልስ እሻለሁ።

ገነት (ኪቺካጎ)

*

✉ ፌዴሬሽኑ በጥረቱ ይመሰገናል። ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው እንዲሉ ከውጪ ሆነን ስህተቶችን ብቻ በማጋነን ማውራቱ አይበጀንም። ተጠቃሚዎች የሆን ሁሉ ደግ ደጉንም የምናይበት ዓይናችን ይከፈት። ፌዴሬሽኑም ካለፉ ስህተቶች የመማር ባህል ያዳብር።

አስፋው (ኤል ኤ)

*

✉ አንድ ነገር ሰምቼ በጣም ገርሞኛል። የቶምቦላው ነገር ነው። ኸረ ለመሆኑ ቶምቦላ ሲወጣ እንዲህ ነወይ? መኪናዎቹስ ለማን እንደደረሱ አይገለጽም ወይ? የሰማሁት እውነት ከሆነ ቲኬቱን ይዤ ፍርድ ቤት መሄዴ ነው። ለቶምቦላው የታዩት መኪናዎች የውሸት ናቸው ይባላል። እንዲያውም የሚባለው የኪራይ መኪናዎች (rent car) እንደሆኑ ነው። ይህ ትልቅ ወንጀል ነው። እንግዲህ ህጋዊ በሆነ መንገድ ከመጠየቁ በፊት መኪኖቹ የተገዙበትን ደረሰኞች፤ የተሸላሚዎቹ ስምና አድራሻ ስልክ ቁጥር ጨምሮ እንዲደርሰኝ እጠይቃለሁ። ይህም በየመጽሄቱ ለህዝብ እንዲቀርብ መደረግ አለበት። እንደመሰለኝ ፌዴሬሺኑ ሃላፊነት አለበት። ይህ የሆነው በሱ ዝግጅት ላይ ነውና።

ግርማ (ከ□ርጂኒያ)

*

✉ ፌዴሬሽኑ የግል ድርጅት ነወይስ ምንድነው?

ወ.ማ.

ፌዴሬሽኑም በበኩሉ ያለውን አስተያየት እንዲሰጠን እንጋብዛለን። እኛም የምንለውን ከፌዴሬሽኑ መልስ ጋር (ከላከልን) በሚቀጥለው እትም እናቀርባለን።



# ቢስቁም ባይስቁም



## አሽሙር አንድ ለአንድ

አንድ ሰው ምሳውን በተልባ በልቶ ወደ ስራው ለመሄድ ደፋ ደፋ ይላል። ሰውየው ለስራ ተጣድፎ ኖሮ ምሳውን የበላበትን አፉን ሳይታጠብና ሳያጠራርግ ስለነበር ተልባው እንዳለ ጥርሱ ላይ ቀርቷል። በመንገድ ላይ ያገኘው አንድ አፈ ጠማማ ሰው ይህን ጥርሱ ላይ የተቸመቸመ ተልባውን ተመልክቶ በዚህ ሊሰድበው ፈለገና "ሰውዬ ተልባ ስንት ስንት ነው?" ይለዋል በአሽሙር። ለምሳው የበላው ተልባ አንዱ ጋ ታይቶበት እየተሰደበ መሆኑ ገባውና ሰውየውን በአፈ ጠማማነቱ ሊሰድበው ፈልጎ "በጠማማ ጣሳ አንዳንድ ነው" ብሎ መለሰለት ይባላል።

*     *     *

አንድ እንቅርታምና አንድ መላጣ ሰው መንገድ ላይ ተገናኝተው ሰላምታ እየተለዋወጡ እያለ መላጣው ሰው እንቅርታሙን ሰው በእንቅርቱ ሊሰድበው ብሎ "ይህን የቋጠርከውን እህል የት ትዘራዋለህ?" ይለዋል። በእንቅርታምነቱ መሰደቡ የገባው ሰውዬ በመላጣነቱ መልሶ ሊሰድበው ፈልጎ "እዚያ አውላላ ሜዳ ላይ" ብሎ መለሰለት ይባላል።

*     *     *

ሁለት ባልንጀራሞች ነበሩ። አንደኛው እከካም ሌላኛው ደግሞ ሆዱ የሚጮህ ነበር። እከካሙ እያሳከከው በአስር ጣቶቹ ይፎክታል። ሆዱ የሚጮኽው ደግሞ ሆዱ እየተንጓጓ እንደ ሐምሌ ክረምት ይጮኽበታል። አንድ ቀን ሆዱ የሚጮኽበት እከካሙን ጓደኛውን በእከካምነቱ ሊሰድበው ብሎ "ይህን የቆፈርከውን መቼ ነው የምትዘራው?" ይለዋል። እከካሙም መሰደቡ ገብቶት "ይኼ የሚንጓጓው ዝናብ ሲጥል ነው" ብሎ መለሰለት ይባላል።

*     *     *

አንድ ሽበታምና አንድ ራሰ በራ (መላጣ) ሰው በመንገድ ላይ ተገናኝተው ስለሰፈር፣ ስለእርሻ፣ ስለአዝመራ፣ ስለገበያው ሲጠያየቁ ይቆዩና ራሰ በራው ሰውዬ ሽበታሙን ለመሳደብ ፈልገው "ዛሬ በዋለው ገበያ ግራጫ በቅሎ በስንት ትሸጣለች?" ብለው በአሽሙር ይሰድቡታል። በሽበቱ መሰደቡ የገባው ሽበታሙ ሰውዬ በመላጣነቱ ሊሰድበው ብሎ "ገጣባ ካልሆነች ደህና ዋጋ ታወጣለች" አለው ይባላል።

*     *     *

ፀጉራቸው የሸበተ አንድ አዛውንትና ራሰ መላጣ ሰው መንገድ ላይ ተገናኝተው ወደ ገበያ ሲሄዱ እያለ ራሰ መላጣው ሰው ሽበቶውን አዛውንት "አባቴ ጥጥ ተሸክመው ወዴት ይሄዳሉ?" ሲል ይጠይቃቸዋል። ነገሩ የገባቸው አዛውንትም "መዳመጫ ፍለጋ ነው" ብለው አሎሎ ራስነቱን ነገሩት ይባላል።

*     *     *

# ጨዋታና ሰንጠረዥ ?

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | ■ 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | ■ 10 |
| 11 | 12 | 13 | 14 | ■ 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 21 | 22 | ■ 23 | ■ 24 | 25 | 26 | 27 | ■ 28 | 29 | 30 |
| 31 | 32 | 33 | ■ 34 | 35 | 36 | 37 | ■ 38 | 39 | 40 |
| 41 | ■ 42 | 43 | 44 | ■ 45 | 46 | 47 | 48 | 49 | 50 |
| 51 | 52 | 53 | ■ 54 | 55 | 56 | ■ 57 | 58 | 59 | ■ 60 |
| ■ 61 | 62 | 63 | 64 | 65 | 66 | 67 | ■ 68 | 69 | 70 |
| 71 | 72 | 73 | ■ 74 | ■ 75 | 76 | 77 | 78 | ■ 79 | 80 |
| 81 | ■ 82 | ■ 83 | 84 | 85 | 86 | 87 | 88 | 89 | 90 |
| 91 | 92 | 93 | 94 | 95 | 96 | ■ 97 | 98 | 99 | 100 |

## ወደ ጎን

1. walkway
6. Male
11. we are satisfied
16. in life
21. he swallowed
24. ላብ ____
29. edge
31. criticism
35. to help
39. kind
43. graduation
47. pile
51. short
55. malaria
58. about
62. post graduate
69. boring
71. open
76. estate (agricultural)
84. father's defence
91. carefully
98. let her have fear

## ወደ ታች

1. go early in the morning
2. she kicked
3. bee
4. get cured
6. he borrowed
8. see
9. she will compete
10. heart beat
25. I will not object
33. chauvenism
48. hole
52. plan
56. ጠበንጃው --------
67. words
70. serious
71. boarder
78. cat
84. whose
85. he said
89. high

# የላንዳፍታ መጽሔት ደምበኛ ይሁኑ

ለ6 ተከታታይ እትሞች

| | | |
|---|---|---|
| U.S. | $16.00 | (including postage & handling) |
| Canada | $22.00 | (including postage & handling) |
| Europe & Asia | $30.00 | (including postage & handling) |

**የሚላክሎት በመጀመሪያ ደረጃ ፓስታ አገልግሎት ነው።**
**በአካባቢዎ ገበያ ላይ ከመዋሉ በፊት ይደርስዎታል።**

## የላንዳፍታ መጽሔት የደምበኝነት ቅጽ LANDAFTA SUBSCRIPTION FORM

NAME ______________________________

ADDRESS ______________________________

CITY ________________ STATE ________ ZIP ________________

PHONE ( _______ ) ________________

<u>ያለፉትን እትሞች</u> ማዘዝ ከፈለጉ ይህንኑ ይጥቀሱ
ክፍያው ከነመላኪያው ለእያንዳንዱ እትም $ 2.50 ነው።

ለጓደኛዎ በሽልማት መልክ ለመላክ ከፈለጉ ከዚህ በታች ያለውን ይሙሉ።
Please, send my gift subscription to the following person.

NAME ______________________________

ADDRESS ______________________________

CITY ________________ STATE ________ ZIP ________________

PHONE ( _______ ) ________________

እባክዎን ክፍያዎን በመኒ ኦርደር ወይም በቸክ በአድራሻችን ይላኩ።
*Please, send money order or check payable to LANDAFTA.*

LANDAFTA
P.O.BOX 49301
ATLANTA, GA 30359

# ADVERTISE ON LANDAFTA

# በላንዳፍታ ላይ ድርጅቶን ያስተዋውቁ

| | |
|---|---|
| 1/4 page 3.5" x 4.75 " | 1/8 page 3.5" x 2.25 " |
| 1/2 page 7.25" x 4.75 " | |

**ADVERTISMENT ORDER FORM**

I would like to place an advertisment on LANDAFTA.

Name: ____________________

Address: ____________________

City: ____________________

St. ___ Zip: ____________

Phone: ____________________

PLEASE, MARK THE SPACE BELOW TO INDICATE YOUR CHIOCE LIKE THIS (X)

## SINGLE ISSUE RATES

| | |
|---|---|
| ◯ BACK COVER | $200.00 |
| FULL PAGE | |
| ◯ INSIDE COVERS | $175.00 |
| ◯ INSIDE PAGES | $140.00 |
| ◯ HALF PAGE | $90.00 |
| ◯ 1/4 PAGE | $65.00 |
| ◯ 1/8 PAGE | $50.00 |

## TWO CONSECUTIVE ISSUES RATE

| | |
|---|---|
| ◯ BACK COVER | $350.00 |
| FULL PAGE | |
| ◯ INSIDE COVERS | $300.00 |
| ◯ INSIDE PAGES | $250.00 |
| ◯ HALF PAGE | $150.00 |
| ◯ 1/4 PAGE | $110.00 |
| ◯ 1/8 PAGE | $90.00 |

ላንዳፍታ


Enclosed, please find: 1. A copy of the advertisment to be placed.
2. A check for the amount marked above.

Please, send a copy of the proof before printing. ☐

I Want my ad Translated in Amharic ☐
(no extra fee - please indicate words or phrases to be translated)

For Information, Please Call Advertisment Department:
Publisher at: Phone/Fax (404)728-9122

Please, Send check or money order payable to LANDAFTA along with your order.
LANDAFTA, P.O.Box 49301, Atlanta GA 30359



# MRA'G TRAVEL

## ሚራዥ የጉዞ ወኪል

*International - Business - Leisure - Cruise*


ለአለም አቀፍና
ለአገር ወሰጥ ጉዞዎ አለንልዎ!

ገነት ፈቀደ
ፕሬዚዳንት
Genet Fekede
*President*

Excellent Service!
Special Fare!
Group Fare!

አስተማማኝ ጉዞ ወደ

አዲስ አበባ
አስመራ
ጆሀንስ በርግ
ቴላቪቭ
ኢየሩሳሌም
ፍራንክፈርት
ለንደን



92 Piedmont Ave N.E
Atlanta, GA. 30303
(404)577-4404 Fax (404)222-9305




# ካሊፎርኒያ ማርት
# በአትላንታ

# CALIFORNIA MART
## IN ATLANTA

2080 CHESHIRE BRIDGE ROAD
ATLANTA, GA 30324
(404)320-6747

**የተለያዩ የምግብ ሸቀጦች መደብር**

| | |
|---|---|
| በርበሬ | እንጀራ |
| ሚጥሚጣ | ጤፍ |
| ቅንጨ | ጌሾ |
| ቡላ ዱቄት | ቡና |
| መከለሻ | እጣን |
| ምስር | የተነጠረ ቅቤ |
| ሽሮ | ተልባ |
| አዋዜ | ልዩ ልዩ ቅመማ ቅመሞች |

*በተጨማሪ ከትፎ ጥብስ እና ጎረድ ጎረድ እናዘጋጃለን።*

ይደውሉልን ወይም ይጎብኙን !!

*MAIL ORDER AVAILABLE*
*Please, Call for arrangements*